ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

6ኛ ክፍል



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

6ኛ ክፍል

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

ISBN ቁጥር -

ዋጋ ብር -

የጥንቃቄ መልዕክት

ተማሪዎች!

ይህን የተማሪ መጽሐፍ በጥንቃቄ ያዙ!

ይህ መማሪያ መጽሐፍ በቀጣይ ዓመት የናንተ ወንድሞችና እህቶች የሚማሩበት የትምህርትቤታችሁ ንብረት ነው! መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ፤

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክና በአሮጌ ጋዜጣ ወይም በካኪ ወረቀት ሸፍኑ፤
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ ደረቅና ንጹህ በሆነ ቦታ አስቀምጡት፤
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ እርጥበት የሌለውና ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ፤
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ፤
5. መጽሐፉን እያነበባችሁ እያላችሁ ንባባችሁን አቋርጣችሁ እንደገና ለማንበብ ስትፈልጉ ምልክት ማድረጊያ ብጣሽ ወረቀት ወይም ካርድ ተጠቀሙ፤
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ስእሎችን ወይም ገጾችን አትቅደዱ፤
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ ጠግኑት፤
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ፤
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ። ደህንነቱን አረጋግጣችሁ ተቀበሉ።
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትቀበሉ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጣጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)።

ማሳሰቢያ፤ እነዚህ መመሪያዎች ሳይተገበሩ ቀርተው በመጽሐፉ ላይ አንዳች ጉዳት ከደረሰ በወጣው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ያደርጋል።

ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

6ኛ ክፍል

አዘጋጆች

እሸቱ ታደሰ

ደስታ ይትባረክ

አርታኢዎች

አታላይ መስፍን

ደምሌ አባተ

ቡድን መሪ

አሰፋ ሰማው ሰማው

ዲዛይነር

አትርሳው ጥግይሁን ወረቀት

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተመደበ በጀት በአብክመ ትምህርት ቢሮና በምሁራን መማክርት ጉባዔ ትብብር ነው።

የመጽሐፉ ሕጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም. አብክመ ትምህርት ቢሮ ነው።

ምሁራን መማክርት ጉባዔ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

ማውጫ

መግቢያ v

ምዕራፍ 1

የሥነ ጥበባት ምንነት

1. የሥነ ጥበባት ምንነት 2
1.1 ንድፍ (Drawing) 3
1.1.1 የንድፍ ተግባር 6
1.2. አብይና ንዑስ ቅኝቶች፣ የድምጽ ቃና እና የቁልፍ አመልካች ምልክቶች 13
1.2.1 አብይ ቅኝት (Major Scale) 14
1.2.2 ንዑስ ቅኝት (minor scale) 18
1.2.3 የድምፅ ቃና (pitch) 20
1.2.4 የቁልፍ አመልካች ምልክቶች 23
1.5. የቴያትር እና የፊልም ጥበብ 26
1.5.1 የቴያትር ጥበብ 26
1.5.2. የፊልም ጥበብ 26
1.5.3 የቴያትር እና የፊልም ሰራ ተሳታፊዎች 27

ምዕራፍ 2

የፈጠራ ችሎታን መግለጽ

2.1. ምትን፣ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ድምጾችን ማንበብ 33
2.1.1 የምት ምንነት 34
2.1.2 ከፍተኛና ዝቅተኛ የድምፅ ቃናዎችን መዘመር 38
2.2 ድርሰት (Composition) 42
2.3 የቁሳቁስ ቅንብር ቀለም ቅብ 43
2.3.1 የቁሳቁስ ቅንብር ቀለም ቅብ አሰራር 49
2.4 ማያያዝና መገጣጠም (Assembling) 52
2.5 የስቴንስል ህትመት 53
2.6 ኪነ ጽህፈት (Calligraphy) 55
2.7 በቴያትር፣ ፊልም እና ፎቶ ግራፍ ሀሳብና ስሜታችንን መግለጽ 57

ምዕራፍ 3

የሀገራችንን ታሪክ በሥነ ጥበባት መተረክና መግለጽ

3.1 በእይታዊ ጥበባት የሀገራችንን ታሪክ መተረክና መግለፅ 65
3.1.1 ስዕላዊ መግለጫ (Illustration) 66
3.1.2 ፎቶ ግራፍን በመጠቀም የሀገራችንን ታሪክ መግለጽና መተረክ 67
3.1.3 በቴያትር የሀገራችንን ታሪክ መተረክና መግለፅ 68

3.2 የሀገራችንን ታሪክ በሙዚቃ መተረክ 68
3.2.1 በፉከራና ቀረርቶ ታሪክን መተረክ.....70
3.2.2 በባህላዊ እስክስታዎች ታሪክን መተረክ 72
3.2.3 በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ታሪክን መተረክ 77

ምዕራፍ 4

ሀገር በቀል እውቀቶችን ማድነቅ

4.1 ሀገር በቀል እውቀቶቻችን በእይታዊ ጥበባት ማድነቅ..... 86
4.1.1 ሀገር በቀል የስነ ጥበብ ስራዎችን በንድፍ መግለጽ 86
4.1.2 ሀገር በቀል የስነ ጥበባት ስራዎችን በወረቀት ሞዛይክ መግለጽ 87
4.2 ሀገር በቀል እውቀቶችን በቴያትር፣ በፊልምና ፎቶ ግራፍ መግለጽ..... 89
4.3 ሀገር በቀል እውቀቶችን በሙዚቃ ማድነቅ..... 91
4.3.1 የሽመና ጥበብን በሙዚቃ ማድነቅ 92
4.3.2 መዝሙር አሉ ባለሙያዎች.....93
4.3.3 ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ማድነቅ .....
.....95

ምዕራፍ 5

ሥነ ጥበባት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያላቸው ዝምድና

5.1 የእይታዊ ጥበባት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ዝምድና 100
5.1.1 እይታዊ ጥበባት እና ቅርሶቻችን.....104
5.1.2 እይታዊ ጥበባት እና አንዳንድ ማህበራዊ ርዕሰ ጉዳዮች 105
5.2 ቴያትር ፊልም፣ ፎቶ ግራፍ እና ማህበራዊ ርዕሰ ጉዳዮች 107
5.3 ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ትስስር..... 108
5.3.1 መዝሙር እውቀት ያብብ 110
5.3.2 መዝሙር የታሪክ ቅርሳችን 110
5.3.3 መዝሙር፦ ጠንቃቃ ተማሪ.....111

መግቢያ

ሥርዓተ ትምህርቱን ማዘጋጀት ለምን አስፈለገ?

ከሥርዓተ-ትምህርቱ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ጥናት እና ምርምሮች ተካሂደዋል። ከእነዚህም አንዱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በስፋት የተካሄደው የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት ዋናው ነው። ይህ እና ሌሎችም ተመሳሳይ ርእሶች ዙሪያ የተካሄዱት ጥናትና ምርምሮች ሥርዓተ ትምህርቱ በይዘት የታጨቀ፣ በትምህርት አይነቶች ብዛት የተወጠረ፣ በአብዛኛው ይዘት ማስታዎስን ትኩረት ያደረገ፣ ከተማሪዎችና ከማህበረሰቡ ህይወትና ኑሮ፣ ምርታማነት እንዲሁም ከሀገር በቀል እውቀት ጋር ያልተቆራኘ፣ ተማሪዎች ተገቢውን ግብረገባዊ እውቀትና ክህሎት እንዲላበሱ ያላደረገ፣ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ እና ልዩ ፍላጎትና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ ከማስተናግድ አኳያ ክፍተት ያለበት መሆኑ ተመላክቷል። በተጨማሪም ስርዓተ ትምህርቱ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚጠይቀውን እውቀትና ክህሎት ማለትም ለመማር መማርን፣ በጥልቀት ማሰብና ችግር ፈችነትን፣ የፈጠራ አስተሳሰብና አዳዲስ ግኝቶች ማፍለቅን፣ ተግባቦትን፣ ትብብርን፣ መሪነትና ውሳኔ ሰጭነትን፣ የቴክኖሎጂ እውቀትን እና የባህል ማንነትና አለማቀፋዊ ዜግነትን ማስጨበጥ የማይችል መሆኑን በማመላከት የሥርዓተ-ትምህርት መሻሻል እና ለውጥ እንዲካሄድ የሚያመላክቱ ምክረ-ሃሳቦችን ሰንዝረዋል።

ይህንን መነሻ በማድረግም ሰፊ የውይይት እና የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተው ህብረተሰቡ እንዲወያይ በማድረግ የለውጥ መርሃ ግብሮች ተቀርፀው ወደ ትግበራ ተገብቷል። ከእነዚህ የለውጥ መርሃ ግብሮች ውስጥ አንዱ አዲስ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት መቅረጽ ሲሆን ቀደም ሲል የነበሩትን ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የሥርዓተ-ትምህርት ለውጥ ዝግጅት ተድርጓል።

በዚህም መሠረት አዲሱን የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በመጀመሪያ ለመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት የሚያግዙ ሰነዶች ማለትም የተማሪው የባህሪ ገጽታ፣ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ፣ የይዘት ፍሰት፣ ተፈላጊ የመማር ብቃት እና መርሃ-ትምህርቶች እንደ ሀገር ተዘጋጅተዋል። በእነዚህ ሰነዶች መነሻነትም በክልላችን የመጀመሪያ ደረጃ(ከ1ኛ-6ኛ) እና የመካከለኛ ደረጃ(7ኛና 8ኛ) ክፍሎች የየትምህርት አይነቶች የተማሪዎች መማሪያ እና የመምህራን ማስተማሪያ መጽሐፍት ተዘጋጅተዋል።

የመጻሕፍት አተገባበር

መጽሐፉ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ከሚያውቁትና ከአካባቢያቸው ይዘውት ከሚመጡት ተሞክሮና እውቀት በመነሳት ተግባር ተኮር እና አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲማሩ ሆኖ ስለተዘጋጀ ተማሪዎች ትምህርቱን በጥልቀት ይገነዘቡታል ወይም ይረዱታል ተብሎ ይታመናል። ተማሪዎችና መምህራን አካባቢያቸውን እና ያካበቱትን ዕውቀትና ተሞክሮ መሰረት በማድረግ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ተማሪዎቻችን ይዘቶችን መማር ብቻ ሳይሆን የመማር ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ይጠበቃል። በመሆኑም መምህራን ለይዘቱ ተስማሚ ተብለው የተጠቆሙ የማስተማሪያ እና መማሪያ ዘዴዎችን በአግባቡ በመተግበርና ሌሎች ተገቢ ዘዴዎችን ተጨባጭ ሁኔታንና የተማሪዎችን አቅምና ፍላጎት መሰረት አድርጎ በመምረጥ ተማሪተኮር /አሳታፊ አድርገው የመማር ማስተማሩን ተግባር መፈጸም የሚጠበቅባቸው ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ መጽሐፍቱን ከእጃቸው ሳይለዩ ትምህርቱን መከታተል ይኖርባቸዋል።

ውድ ተማሪዎቻችን!

መጽሐፉን በጥንቃቄ በመያዝ በአግባቡ መጠቀም አለባችሁ። በማንኛውም አገርና ሁኔታ መማር የትውልድን የወደፊት ሁኔታ ይወስናል። መማር ለማንኛውም ማህበራዊ፣ ሰብዓዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሰረት ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተግባራት፣ ይዘቶችና ጥያቄዎች በአግባቡ በመስራትና በማጥናት ጥልቀት ያለው ክህሎትን እና ግንዛቤን ማዳበር ይገባችኋል።

ውድ ወላጆች/ አሳዳጊዎች!

የተማሪዎችን መማር የተሳለጠ ለማድረግ የመማሪያ መጻሕፍት ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ተማሪዎች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዘው እንዲጠቀሙ ማድረግ ይኖርባችኋል። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች መጽሐፉን ት/ቤት ይዘው እንዲሄዱ ማበረታታት፣ ከመምህሮቻቸው የሚሰጡ ተግባራትን በትክክል እንዲፈጽሙና እንዲያጠኑ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ትምህርት ቤት በመሄድ ከመምህራን ጋር በመገናኘት ስለ ልጅዎ የመማር ዕውቀትና የባህሪ ለውጥ በመጠየቅ ክፍተቱን በመለየት ምክር በመሥጠት ማስተካከል ይጠበቅባችኋል። በመሆኑም ትምህርት የሁሉም ነገር መሰረት መሆኑን በመገንዘብ መማርን ከመንግስት ስራ መያዝ ጋር ብቻ ሳታቆራኙት/ሳያያይዙት ልጆችን ሁልጊዜ ወደትምህርት ቤት መላክ አለባችሁ።

ምዕራፍ 1

የሥነ ጥበባት ምንነት

የምዕራፉ ዓላማዎች፡

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የሥነ ጥበባት ምንነትን ትገነዘባላችሁ።
- ንድፍ ለእይታዊ ጥበባት ስራዎች መሰረታዊ ክህሎት መሆኑን ታውቃላችሁ።
- ንድፍን በመጠቀም ልዩልዩ ስዕሎችን መስራት ትችላላችሁ።
- የዓብይና የንዑስ ቅኝትን የድምጽ ቃናዎችን መለየት ትችላላችሁ።
- ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የድምጽ ቃናዎችን ትለያላችሁ።
- የቁልፍ አመልካቾችን በመጠቀም ጂ እና ኤፍ ክሌፎች ላይ ዓብይና ንዑስ ቅኝቶችን መገንባት ትችላላችሁ።
- የቴያትር እና የፊልምን ምንነትን ትገነዘባላችሁ።

መግቢያ

ተማሪዎች ይህ ምዕራፍ አራት ዋና ዋና ይዘቶች ላይ ያተኩራል። የመጀመሪያው የስነ ጥበባት ምንነትን የሚያሰተምር ነው። ሥነ ጥበባት ክውን እና እይታዊ ጥበባት የሚባሉ ዘርፎች አሉት። ክውን ጥበባት የምንላቸው፣ ቴያትር፣ ድራማ፣ ሙዚቃ፣ ዳንስ እና የመሳሰሉት ናቸው። የእይታዊ ጥበባት ደግሞ ቀለም ቅብ፣ ቅርጽ፣ ንድፍ፣ ዲዛይን፣ ፎቶ ግራፍ የመሳሰሉት ናቸው። በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለ ንድፍ ምንነት እና ንድፍ ለቀለም ቅብ፣ ለቅርጽ እና ለሌሎች የእይታዊ ጥበባት ዘርፎች መሰረት እንደሆነ የሚያስተምር ነው።

በሦስተኛው ክፍል ደግሞ ስለ ቅኝት ምንነት፣ ስለ ድምጽ ቃና እና ስለ ቁልፍ አመልካች ምልክቶች የሚያስተምር ነው። ቅኝት የድምጾች በቅደም ተከተል መደርደር ሲሆን አብይና ንዑስ የሚባሉ ቅኝቶች አሉ። የድምጽ ቃና ደግሞ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ቃናዎች አሉት። የቁልፍ አመልካች ምልክቶ ሻርፕና ፍላት የሚባሉ መሆናቸውን ያስተምረናል። በአራተኛው ክፍል የቴያትር እና የፊልም ጥበብን ምንነት የምንማርበት ሲሆን ስለ ድርሰት አዘገጃጀት፣ ትወና እና ተዋንያን ያስተምረናል።

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የምታስተውሏቸው የቀለም ቅብ ስዕሎች፣ የቅርጽ ስራዎች፣ የአደባባይ ሀውልቶች፣ ፎቶግራፎች፣ እና የማስታወቂያ ስዕሎች በማስታወስ ጠቀሜታቸውን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የምታዳምጡትና የምትጫወቱት ባህላዊ ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣ ቀረርቶ፣ እና ሽለላ ከሙዚቃ እና ዳንስ ጋር ያላቸውን ልዩነት በንጽጽር ተናገሩ።
3. ተማሪዎች ቴያትርና ፊልም ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ? በአካባቢያችን ቴያትርና ፊልም ቤቶች ቢቋቋሙ በማህበረሰቡ ባህል እና የአኗኗር ዘይቤ ላይ የሚያመጡት አወንታዊ ለውጥ ምን ይመስሏችኋል?

1. የሥነ ጥበባት ምንነት

የሥነ ጥበብ ምንነት በተለያዩ ዘመናት እና ማህበረሰባዊ ባህል ውስጥ የተለያየ ትርጉም ያለው ነው። የሥነ ጥበብ ትርጉም በአንድ ዓረፍተ ነገር ብቻ የተወሰነ አይደለም። ሥነ ጥበብ የፈጠራ እና ክህሎት ልምምድ ውጤት ነው ብለን መግለጽ እንችላለን። ነገሮችን ሆን ብሎ የማደራጀት ተግባር ሲሆን ሀሳብና ስሜትን የመግለጫ መንገድ ነው። የጥበብ ባለሙያው ማለትም ሠዓሊው፣ ሙዚቀኛው እና የቴያትር ደራሲው ሀሳብና ስሜቱን የሚገልጽበት የፈጠራ ስራ ነው። ሥነ ጥበብ ክውን እና እይታዊ ጥበባት ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ክውን ጥበባት የምንላቸው ቴያትር፣ ድራማ፣ እስክስታ፣ ሙዚቃ የመሳሰሉት ናቸው። እይታዊ ጥበባት የሚባሉት ደግሞ ቀለም ቅብ፣ ቅርጽ፣ ንድፍ፣ ዲዛይን፣ ፎቶግራፍ፣ ኪነ ህንጻ፣ ህትመት የመሳሰሉት ናቸው። የሥነ ጥበብ ስራዎች ሥነ

ውበታዊ ፋይዳ ያላቸው ሲሆን በማህበረሰባዊ የእድገት ለውጥ ውስጥ ትልቅ ድርሻ አላቸው።

በሀገራችን ዘመናዊ የቴያትር፣ የእይታዊ ጥበባት እና የሙዚቃ ትምህርት ቤቶች መስፋፋት የሥነ ጥበብ ትምህርት እድገት ላይ ከፍተኛ ሚና የተጫወተ ሲሆን እነዚህ ሥነ ጥበባዊ ስራዎች ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር፦

- ለእለት ከእለት የሰውልጅ ፍጆታ ወይም አገልግሎት የሚውሉ
- ሀሳብና ስሜትን ለመግለጽ የሚውሉ
- ለጌጥነት የሚውሉዐና ሥነ ውበታዊ ፋይዳ ያላቸው የሰው ልጅ የፈጠራ ስራዎች ናቸው።

1.1 ንድፍ (Drawing)

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. የቀለም ቅብ እና ሌሎች የእይታዊ ጥበብ ተግባራትን ለመስራት አሠፈላጊ ተግባር ምን ይመስላችኋል?
2. በእርሳስ፣ በከሰል እና በቾክ /ጠመኔ/ ወረቀት ላይ ስዕል የመስራት ተግባር ለሌሎች የእይታዊ ጥበብ ተግባራት ያለው ጠቀሜታ ምንድ ነው?



ስዕል 1 የቁሳቁስ ቅንብር ንድፍ

ንድፍ ለሁሉም የእይታዊ ጥበብ ስራዎች መሰረት ነው። ረቂቅ የሆነ ስሜትን ለመግለጽ እና በአካባቢያችን የምናስተውላቸውን ነገሮች ለመሳል፣ እና ለመቅረጽ የሚያስችለን የጥበብ ተግባር ነው። ንድፍ በእርሳስ፣ በብዕር፣ በጠመኔ፣ በከሰል፣ እና በባለቀለም እርሳሶች ወዘተ ወረቀት፣ ካርቶን ወይም ሌላ ሰሌዳ ላይ ምልክት እና የቶን ደረጃዎችን በማኖር ስዕል የማስገኘት ሂደት ነው።

የተግባር ስራ

- እርሳስና የስዕል ደብተራችሁን በመጠቀም በክፍላችሁ ውስጥ ያሉ ነገሮችን በመንደፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።
- በሰራችሁት ላይ እርስ በርስ አስተያየት በመለዋወጥ አድናቆትና ሂስ ስጡ።



ስዕል 2 የእርሳስ ንድፍ

ንድፍ እንደ ተሟላ ድርሰት ሠዓሊው ሀሳቡን፣ ስሜቱን እና ምልከታውን በሰሌዳ ላይ የሚያሰፍርበት /የሚሰልበት/ ነው። ንድፍ እንደ መነሻ ዲዛይን በመሆን አንድ የተሟላ ነገር ለማስገኘት የሚያስችል ስዕላዊ እቅድ ሆኖ ሊያገለግለን ይችላል።

ንድፍ የነገሮችን መልክ፣ ቅርጽ እና ሁኔታ ለማጥናት በእርሳስ (እርሳስን ሊተኩ በሚችሉ የስዕል መሳሪያዎች)የምናደርገው ስዕል የመስራት ሂደት ነው።



ስዕል 3 የእርሳስ ንድፍ ድርሰት

እነዚህ ከላይ የተቀመጡት ንድፎች የሰዓሊያኑ ድርሰቶች ናቸው። በራሳቸው የሰዓሊያኑን ሀሳብና ስሜት እንዲወክሉ ሆነው የተሰናዱ ናቸው። ይህም ንድፍ ሀሳብና ስሜትን መግለጫ አንዱ የእይታዊ ጥበብ ዘርፍ መሆኑን ያስረዳል።

እንደ ሌሎቹ የእይታዊ ጥበባት ዘርፎች ንድፍ ፈጠራዊ ስራዎቻችንን ለተመልካች ለማቅረብ የሚያስችለን አንዱ ዘርፍ ነው። በእርሳስ፣ በከሰል እና በጠመኔ የተሰሩ የንድፍ ስራዎችን በማሳባሰብ ለእይታ ማቅረብ እንችላለን።



ስዕል 4 ንድፍ ልዩ ልዩ ነሮችን ለማዘጋጀት ወይም ለማምረት የሚያስችል / ዲዛይን/

እነዚህ ንድፎች የልብስን እና የማሽን ዲዛይንን የሚያሳዩ ሲሆን በዋናነት እንደ እቅድ የሚያገለግሉ ንድፎች ናቸው። ለምሳሌ አንድ የጨጨአልባሳት ፋሽን ዲዛይነር የአልባሳት ንድፍ ያዘጋጃል። ስዕላዊ የልብስ ዲዛይን እንደ እቅድ ወረቀት ላይ ያዘጋጃል። አንድ መሀንዲስም ቤት መስራት የሚጀምረው የተሟላ የቤት ንድፍ ወረቀት ላይ መንደፍና ዲዛይኑን ማዘጋጀት ሲችል ነው። ስለዚህ ንድፍ አንድ ነገር ለመስራትም ሆነ ለማዘጋጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።



ስዕል 5 በቀላል መስመሮች የሚደረግ የንድፍ ጥናት

ዋናውን ገጸ ባህሪ በሚገባ ለመረዳትና ውክልና ለመስጠት የሚረዳን የንድፍ ልምምድ ነው። አንድን ነገር በተደጋጋሚ በንድፍ ማጥናት የተስተካከለ እና የተሻለ ውክልናን በስዕላችን ውስጥ ለማምጣት ይረዳናል። በርካታ ታላላቅ ሰዓሊያን ከዋና የድርሰት ስራቸው በፊት የንድፍ ጥናት ልምምድ በማድረግ ውጤታማ ስራዎችን ማበርከት ችለዋል።

1.1.1 የንድፍ ተግባር

ንድፍ በቀላሉ በእርሳስና ወረቀት መስመር ከማኖር እና ከመሞነጫጨር ይጀመራል። የመሞነጫጨር ሂደቱ እየዳበረ እና እየተገራ ሲሄድ የንድፍ ክህሎታችን ያድጋል። ንድፍ በጥናት እና በተደጋጋሚ ልምምድ የሚዳብር ነው። አንድ ሰው በንድፍ የነገሮችን የሚወክልበት አቅም ካዳበረ ሌሎቹን የእይታዊ ጥበብ ዘርፎች በቀላሉ መከወን እና ማደራጀት ይችላል። ለዚያም ነው የንድፍ ክህሎት በእይታዊ ጥበብ ትምህርት ውስጥ መሰረታዊ ተደርጎ የሚወሰደው።

ለንድፍ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች

ለንድፍ ስራ በዋናነት እርሳስ፣ የስዕል ወረቀት፣ ላጲስ፣ መቅረጫ እና የስዕል ማስደገፊያ ያስፈልጉናል።

እርሳስ፦ ለንድፍ ስራ አስፈላጊ ከሆኑት መሳሪያዎች መካከል አንዱ ሲሆን በቀላሉ ስዕል ለመስራት የተመቸ ነው። እርሳስ ጠንካራ፣ መካከለኛ እና ለስላሳ ደረጃ አለው። ከመስመር ጀምሮ ብርሃና ጥላ፣ ቴክስቸር እና የቦታዎችን ርቀት እና ጥልቀት በስዕላችን ውስጥ ለማስቀመጥ የተመቸ ነው። የእርሳሱ መጠን ደግሞ ቀጭን እና ወፍራም ሆኖ ሊዘጋጅ ይችላል። “HB” እርሳስ በሰዓሊያን

የተለመደ እና አዘውትረን የምንጠቀመው የእርሳስ አይነት ሲሆን ከ"B" እስከ "12B" እና ከ"H" እስከ "7H" ድረስ ስያሜ ያላቸው የእርሳስ አይነቶች አሉ። ከሰል፣ ጠመኔ እና ሌሎች ባለቀለም እርሳሶችም ንድፍ ለመስራት የሚያስፈልጉ ናቸው።

ወረቀት፦ የስዕል ወረቀት የተለያየ መጠንና ውፍረት አለው። ውፍረቱ በግራም የሚለያይ ሲሆን መጠኑ ደግሞ በስያሜ ይለያያል። ትልቁ የወረቀት መጠን "A0" ሲሆን ትንሹ ደግሞ "A8" የወረቀት መጠን ነው። በስዕል ስራ የተለመዱት የወረቀት መጠኖች ከ"A1" እስከ "A5" ድረስ ያሉት የወረቀት መጠኖች ናቸው። "A1" የወረቀት መጠን 8 የ"A4" ወረቀቶችን መጠንን የሚያክል ሲሆን "A4" ለጽህፈት የምንጠቀምበት የወረቀት መጠን ነው።

ላጲስ፦ በእርሳስ የምንሰራውን ስዕል ለማጥፋት የምንጠቀምበት የእርሳስ ማጥፊያ ነው።

መቅረጫ፦ ስዕል ለመስራት የምንጠቀምበትን እርሳስ ለመቅረጽ የሚያስችለን ስለታማ ነገር ሲሆን በጥንቃቄ ልንጠቀምበት ይገባል።

የስዕል ማስደገፊያ፦ ስዕል የምንሰራበትን ወረቀት የሚደግፍል ሲሆን የተሻለ የእጅ እንቅስቃሴ ወረቀቱ ላይ ለማሳረፍ ይረዳላናል። እንደየ ወረቀቱ መጠን የተለያየ መጠን ኖሮት ይዘጋጃል። የስዕል ማስደገፊያ ቋሚ ወይም በቀላሉ በእጅ የሚያዝ ሊሆን ይችላል።





ስዕል 6 የንድፍ እርሳስ አይነቶችና ላጲስ እና የወረቀት መጠን





ስዕል 7 ቋሚ የስዕል ማስደገፊያ (ኢዝል) እና የእርሳስ መቅረጫ

የእርሳስ አያያዝ፦ የንድፍ ስራ ለመስራት የእርሳስ አያያዝ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል። እርሳሳችንን የምንይዝበት ሁኔታ ነጻ የሆነ የእጅ እንቅስቃሴ እንዲኖረን እና በነጻነት መስመሮችን ለማስመር ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ከዚህ በታች የተቀመጡት ስዕሎች እርሳሳችንን በምን መልኩ መያዝ እንዳለብን የሚጠቁሙ ናቸው። ተማሪዎች በስዕሉ መሰረት የእርሳስ አያያዛችሁን አስተካክሉ።



ስዕል 8 ለንድፍ ስራ የተመቸ የእርሳስ አያያዝ



ስዕል 9 ንድፍ ለቅርጽ ስራ



ስዕል 10 ንድፍ ለቀለም ቅብ መሰረት ነው

ንድፍ ለቅርጽ ስራ አስፈላጊ እንደሆነ ምሳሌ የሚሆነን ሲሆን በተደጋጋሚ የምናደርገው የእርሳስ ስዕል ልምምድ እና ጥናት ስዕል የመስራት ክህሎታችንን ያሳድግልናል። ንድፍ ስንሰራ በገጸባህሪው ላይ የሚያርፈውን ብርሃን በማስተዋል በእርሳስ ቅብ በመቀባት ወደ ፎርም ደረጃ ማሳደግ ይችላል። ይህም በነገሩ ላይ የሚያርፈው የብርሃን መጠን፣ የሸካራነትና ልስላሴ ደረጃ፣ በአካሉ ላይ የሚፈጠረውን የጥላ እና የፍካት ደረጃ በመገንዘብ የቅብ ተግባርን ያከናውናል። የንድፍ ጥናት ሌሎቹን የእይታዊ ጥበባት ዘርፎች ለመስራት መሰረታዊ እና ከፍተኛ ሚና ያለው ነው።

የእርሳስ ቅብ ዘዴ እና የብርሃንና ጥላ አቀማመጥ

ንድፍ በምንሰራበት ጊዜ በነገሩ ላይ የሚያርፈውን ብርሃንና ጥላ በስዕላችን ውስጥ ለመስራት ከብርሃን ወደ ጥላ የፍካት ደረጃውን ጠብቀን የምንቀባ

ሲሆን የነገሩን ሸካራነትና ልስላሴ የሚገልጽ እንዲሆን መጠንቀቅ ይኖርብናል። የተለያዩ የብርሃን ደረጃዎች አሉ።



ስዕል 11 ፍካት እና የብርሃንና ጥላ ደረጃ

ፍካት፡- የእርሳስ ቅብ በምንሰራበት ጊዜ ከንጣት እስከ ጥቁረት ያለው ደረጃ የፍካት ልዩነት ይባላል።



ስዕል 12 ከንጣት እስከ ጥቁረት ያለው ደረጃ

የንድፍ ተግባር ልምምድ

ከዚህ በታች የቀረቡትን የቁሳቁስ ንድፍ በደብተራችሁ ተለማመዱ





የሰው ምስል ከደረት በላይ መስራት መለማመድ

ሀ)	ለ)	ሐ)	መ)
			
			

የተግባር ስራ

✍ ከላይ የሰው ምስል ከደረት በላይ መስራት በሚለው ርዕስ ስር ከፊደል ሀ እስከ መ የተቀመጡትን የሴት እና የወንድ ስዕሎች በደብተራችሁ ላይ በመለማመድ ለመምህራችሁ አሳዩ።

በቀላል መስመሮች የሰውን እንቅስቃሴ በንድፍ ማጥናት



የተግባር ስራ

✍ ተማሪዎች በስዕል ደብተራችሁ ላይ የሰውን እንቅስቃሴ በቀላል መስመር ጥናት ልምምድ በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አሳዩ።

1.2. አብይና ንዑስ ቅኝቶች፣ የድምጽ ቃና እና የቁልፍ አመልካች ምልክቶች

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

✍ የጂ እና የኤፍ ቁልፎችን የመስመርና ክፍት ቦታ ስሞች በደብተራችሁ ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።

ቅኝት፦ የድምፆች በስርዓትና በቅደም ተከተል መደርደር ወይም የድምፆች መሰላል ነው። ቅኝት የድምፆች መሰላል ነው ስንል ከአንድ ድምፅ ተነስተን ወደ ላይ መውጣትና ወደ ታች መውረድን ያመለክታል። በአንድ መሰላል መወጣጫዎች መካከል ያለውን ርቀት ደረጃ ብለን እንደምንጠራው ሁሉ በሁለት ተከታታይ የሙዚቃ ድምፆች መካከል ያለውን የድምፅ ንዝረት ደግሞ የድምጽ ርቀት (Intervale) ብለን እንጠራዋለን።



ስዕል 13 ሰባቱ የሙዚቃ ድምጾች

በአገራችን ኢትዮጵያ በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ መንገድ ተዘጋጅተው የምንሰማቸው ሙዚቃዎች በአምስት ድምፆች የተመሰረቱ ሲሆኑ መነሻቸውም ሰባቱ ዓለማቀፍ የሙዚቃ ድምፆች ናቸው። በቅኝት አመሰራረት የባለ ሰባት ድምፅ ድረርድር ዲያቶኒክ ቅኝት ይባላል። የባለ አምስት ድምፅ ድርድር ደግሞ ፔንታቶኒክ ቅኝት ይባላል። የዲያቶኒክ ቅኝት ዓይነቶች ሁለት ናቸው። እነሱም-

1. አብይ ቅኝት (Major Scale)
2. ንዑስ ቅኝት (Minor Scale)

1.2.1 አብይ ቅኝት (Major Scale)

አብይ ቅኝት ዋናው የቅኝት መሰረት ነው። አብይ ቅኝትን እንደመነሻነት በመጠቀም ሌሎች ቅኝቶችን እንመሰርታለን። አብይ ቅኝት ሲመሠረት አንድ ሙሉና ግማሽ የድምፅ ደረጃዎች አሉት። በሁለት ድምፆች መካከል ያለውን የድምፅ ንዝረት ደግሞ ርቀት (Intervale) ይባላል። በማንኛውም አብይ ቅኝት (ሜጀር ስኬል) ግማሽ የድምፅ ርቀት የምናገኘው ከ3 ወደ 4 እና ከ7 ወደ 8 ብቻ ሲሆን ሌሎቹ የድምፅ ደረጃዎች ደግሞ አንድ ሙሉ የድምፅ ርቀት አላቸው። የአንድ የቅኝት 8ኛ ድምፅ ኦክታቭ ይባላል። Cን መነሻ አድርገን አብይ ቅኝት ስንመሰርት ምንም ሻርፕም ሆነ ፍላት አንጠቀምም። ሌሎች ድምፆችን መነሻ አድርገን አብይ ቅኝት ለመገንባት ግን የቁልፍ አመልካች ምልክቶችን መጠቀም ያስፈልጋል።

የአብይ ቅኝት አመሰራረት

ምሳሌ፡- 1 የሲ ዓብይ ቅኝት (C Major scale) አገነባብ በጂ ቁልፍ





የሲ ቅኝት የድምፅ ርቀት

ምሳሌ፡- 2



የሲ ዓብይ ቅኝት (C Major scale) አገነባብ በኤፍ ቁልፍ

ምሳሌ፡ 3



የኤፍ አብይ ቅኝት (F Major scale) አገነባብ በጂ ቁልፍ

ምሳሌ፡ 4



የኤፍ አብይ ቅኝት (F Major scale) አገነባብ በኤፍ ቁልፍ

ምሳሌ፡ 5



መልመጃ 1.1

ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች የአብይ ቅኝት አመሰራረትን መሰረት አድርጋችሁ ርቀቱን አንድ ሙሉ ወይም ግማሽ በማለት ፃፉ።

1. ከጂ እስከ ኤ----------ርቀት አለው።
2. ከኤ እስከ ቢ----------ርቀት አለው።
3. ከቢ እስከ ሲ----------ርቀት አለው።
4. ከሲ እስከ ዲ----------ርቀት አላው።
5. ከዲ እስከ ኢ----------ርቀት አለው።
6. ከኢ እስክ ኤፍ----------ርቀት አለው።
7. ከጂ እስከ ኤፍ ----------ርቀት አለው።
8. ከኤ እስከ ጂ ----------ርቀት አለው።

መልመጃ 1.2

1. ጂ ቁልፍን በመጠቀም E አብይ ቅኝትን (E Major scale) በሙሉ ኖታ ደርድሩ።



2. ኤፍ ቁልፍን በመጠቀም E አብይ ቅኝትን በግማሽ ኖታ ደርድራችሁ አሳዩ።



3. ጂ ቁልፍን በመጠቀም A አብይ ቅኝትን (A Major scale) በሩብ ኖታ ደርድሩ።



4. የኤፍ ቁልፍን በመጠቀም A አብይ ቅኝትን በአንድ ስምንተኛ ኖታ ደርድራችሁ አሳዩ።



5. ቢ ፍላት ቅኝትን በጂ ቁልፍ ደርድራችሁ አሳዩ።

6. ኢ ፍላት ቅኝትን በኤፍ ቁልፍ ደርድራችሁ አሳዩ።

7. ጂ ቅኝትን በኤፍ ቁልፍ ደርድራችሁ አሳዩ።

8. ዲ ቅኝትን በጂ ቁልፍ ደርድራችሁ አሳዩ።

9. ኤፍ ሻርፕ ቅኝትን በጂ ቁልፍ ደርድራችሁ አሳዩ።

1.2.2 ንዑስ ቅኝት (minor scale)

ንዑስ ቅኝቶች ሲሰሙ ለስለስ ያለ የድምፅ ቃና ወይም ለዛ ያላቸው የቅኝት አይነቶች ናቸው። ንዑስ ቅኝቶች ካላቸው የድምጽ ባህርያት በመነሳት በሶስት ዋናዋና ክፍሎች ይከፈላሉ። እነርሱም፡ ናቹራል ንዑስ ቅኝት፣ ሀርሞኒክ ንዑስ ቅኝት እና ሜሎዲክ ንዑስ ቅኝት ናቸው። በዚህ የክፍል ደረጃ ስለ ናቹራል ንዑስ ቅኝት ምንነትና አገነባብ እንማራለን።

ሀ) ናቹራል ንዑስ ቅኝት (ተፈጥሯዊ ንዑስ ቅኝት)

ናቹራል ንዑስ ቅኝት የአብይ ቅኝትን ባህሪ የሚወርስ የቅኝት አይነት ነው። ናቹራል ንዑስ ቅኝት ለስለስ ያለ የድምፅ ቃና ወይም ለዛ አለው። ናቹራል ንዑስ ቅኝት ሲገነባ ከ2 ወደ 3 እና ከ5 ወደ 6 ግማሽ የድምፅ ርቀት አለው። ቀሪዎቹ የድምፅ ደረጃዎች ደግሞ አንድ ሙሉ ርቀት አላቸው። የንዑስ ቅኝት አመሰራረት እንደ አብይ ቅኝት 7ቱን የሙዚቃ ድምፆች ተጠቅመን የምንመሰርተው ቅኝት ነው።

ናቹራል ንዑስ ቅኝት ከአብይ ቅኝቱ ወደ ኋላ ሶስት ድምፅ ቆጥረን እናገኘዋለን። ከሲ አብይ ቅኝት ተነስተን ናቹራል ንዑስ ቅኝቶችን በሚከተለው መንገድ እንገነባለን።

C D E F G A B C ከሚለው አብይ ቅኝት ናቹራል ንዑስ ቅኝትን ለማግኘት ወደ ኋላ ሶስት ስንቆጥር።

C D E F G A B C
3 2 1

የምናገኘው A ነው። የA ንዑስ ቅኝት ድርድርም A B C D E F G A ይሆናል።

ኤ ናቹራል ንዑስ ቅኝት (A ናቹራል ማይነር ስኬል) በጂ ቁልፍ



ዲ ናቹራል ንዑስ ቅኝት (D natula minor scale)



መልመጃ 1.3

1. ጂ ቁልፍን በመጠቀም e ናቹራል ንዑስ ቅኝትን በሙሉ ኖታ ደርድራችሁ አሳዩ።



2. ኤፍ ቁልፍን በመጠቀም e ናቹራል ንዑስ ቅኝትን በግማሽ ኖታ ደርድራችሁ አሳዩ።



3. ጂ ቁልፍን በመጠቀም ኤ ናቹራል ንዑስ ቅኝትን በሙሉ ኖታ ደርድራችሁ አሳዩ።



4. ኤፍ ቁልፍን በመጠቀም ኤፍ ናቹራል ንዑስ ቅኝትን በሩብ ኖታ ደርድራችሁ አሳዩ።



1.2.3 የድምፅ ቃና (pitch)

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

ተማሪዎች አንድ የምታውቁትን ዜማ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማዜም አሰሙና እናንተ ያላችሁ የድምፅ ቃና ወፍራም፣ ወይም ቀጭን መሆኑን ተናገሩ።

በወፍራምና በቀጭን ድምፅ የሚገለፅ የድምፅ ለዛ ቃና (pitch) ይባላል። በጂ ቁልፍ መስመሮችና ክፍት ቦታዎች ላይ የተፃፉ ድምፆች ከፍተኛ የድምፅ ቃና (high pitch) ይባላሉ። በኤፍ ቁልፍ መስመሮችና ክፍት ቦታዎች ላይ የተፃፉት ድምፆች ደግሞ ዝቅተኛ የድምፅ ቃና (low pitch) ናቸው። ከፍተኛ ድምፅ ማለት ቀጭን ድምፅ ሲሆን ዝቅተኛ ድምፅ ደግሞ ወፍራም ድምፅ ነው።

ምሳሌ፡- 1 ከፍተኛ የድምፅ ቃና (high pitch)



ዝቅተኛ የድምፅ ቃና (low pitch)

ምሳሌ፡- 2

ከፍተኛ የድምፅ ቃና (high pitch)



ዝቅተኛ የድምፅ ቃና

መልመጃ 1.4

1. እንደየ ድምፅ ባህሪያችሁ በቡድን ተከፋፈሉና

   ሀ) አንደኛው ቡድን በጂ ቁልፍ ላይ የተፃፉ ዜማዎችን ይዘምር፣

   ለ) ሁለተኛው ቡድን ደግሞ በኤፍ ቁልፍ የተፃፉ ዜማዎችን ይዘምር። ሁለቱም ቡድን ከዘመሩ በኋላ በሁለቱ ቡድኖች አዘማመር መካከል ያለውን የድምፅ ቃና ልዩነት ለመምህራችሁ ተናገሩ።



መልመጃ 1.5

ሀ) በሚከተሉት ስታፎች የተጻፉ ድምጾችን ግማሽና ሩብ ኖታን በመጠቀም ዘምሩ

1. ከC እስከ F (C D E F) ያሉ ድምፆችን በሩብ ኖታ የጊዜ ርዝማኔ ዘምሩ።



2. ከG እስከ C (G A B C) ያሉ ድምፆችን በግማሽ ኖታ ዘምሩ።



3. ከ G እስከ C (G A B C) ያሉ ድምፆችን በግመሽ ኖታ የጊዜ ርዝማኔ እየወጣችሁና እየወረዳችሁ ዘምሩ።



4. ከዚህ በታች ስታፍ ላይ የተፃፉ ዜማዎችን በግልና በቡድን ዘምራችሁ አሰሙ።

1



2



1.2.4 የቁልፍ አመልካች ምልክቶች

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ቁልፍ ምንድን ነው? ስንት አይነት ቁልፎችን ታውቃላችሁ?
2. የቁልፍ አመልካች ማለት ምን ማለት ነው?

የቁልፍ አመልካች ምልክቶች የምንላቸው ሻርፕና ፍላት ናቸው። ሻርፕና ፍላት በጂ እና በኤፍ ቁልፎች ላይ የምንገነባውን አብይም ሆነ በንዑስ ቅኝቶች ከአንዱ ወደ ሌላው ያለውን ርቀት ጠብቀን እንድንገነባ የሚያደርጉ የሙዚቃ ምልክቶች ናቸው። እነዚህም ምልክቶች በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ ከቁልፍ ቀጥሎ በአቀማመጥ ቅደም ተከተላቸው ይፃፋሉ።

ሻርፕ፦ አንድን ድምፅ ከነበረው ድምፅ ላይ በግማሽ ድምፅ እንዲጨምር ወይም እንዲቀጥን የሚያደርግ የሙዚቃ ምልክት ነው። ምልክቱም # ነው።

ፍላት፦ አንድን የሙዚቃ ድምፅ ከነበረው ድምፅ ላይ በግማሽ ድምፅ እንዲቀንስ ወይም እንዲወፍር የሚያደርግ ሲሆን ምልክቱም ይህ ♭ ነው።

ምሳሌ፦ 1

የጂ ቅኝት (G majore) የቁልፍ አመልካች በጂ ቁልፍ



በጂ ቁልፍ የጂ አብይ ቅኝት የቁልፍ አመልካች ምልክት አቀማመጥና የኖታዎች አደራደር



በጂ ቁልፍ የኤፍ ቅኝት (F majore) የቁልፍ አመልካች አቀማመጥ።



በጂ ቁልፍ የኤፍ ቅኝት የቁልፍ አመልካች አቀማመጥና የኖታዎች አደራደር።



በኤፍ ቁልፍ የጂ ቅኝት (G majore) የቁልፍ አመልካች አቀማመጥ



በኤፍ ቁልፍ የኤፍ ቅኝት (F majore) የቁልፍ አመልካች አቀማመጥ



መልመጃ 1.6

ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተሰጡት ስታፎች ላይ የቁልፍ አመልካቾችን ፃፉ።

1) የዲ ዓብይ ቅኝትን (D Major scale) የቁልፍ አመልካቾች በጂ እና በኤፍ ቁልፍ ትክክለኛ የአቀማመጥ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቃችሁ ፃፉ።



2) የኢ ፍላት ዓብይ ቅኝትን (E ♭ Major scale) የቁልፍ አመልካቾች በጂ እና በኤፍ ቁልፍ ትክክለኛ የአቀማመጥ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቃችሁ ፃፉ።



3) የኤ ፍላት ዓብይ ቅኝትን (A ♭ Major scale) የቁልፍ አመልካቾች በጂ እና በኤፍ ቁልፍ ትክክለኛ የአቀማመጥ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቃችሁ ፃፉ።



4) የኤ ዓብይ ቅኝትን (A Major scale) የቁልፍ አመልካቾችን በጂ እና በኤፍ ቁልፍ ፃፉ።



1.5. የቴያትር እና የፊልም ጥበብ

1.5.1 የቴያትር ጥበብ

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪች ከዚህ በፊት የተማራችሁትን የቴያትር ምንነት በማስታወስ ለመምህራችሁ ግለጹ።

3. ሰዎች ወደ ቴያትር ቤት የሚሄዱት ለምን ይመስላችኋል?

ቴያትር የሚለው ቃል "ትያትሮን" ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን የመመልከቻ ስፍራ ማለት ነው። ቀደም ባሉት ጊዜያት ተዋንያን የሰው ልጆችን የህይወት ተሞክሮ እና ሁኔታ የሚያሳዩ አዝናኝ ተውኔቶችን በተለያዩ ቦታዎች በቤተ መቅደስ አካባቢዎች፣ በገብያ ስፍራ፣ በመንገድ ዳር፣ በህዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች፣ በታላላቅ አዳራሾች እና በክፍት ስፍራዎች ላይ ለህዝቡ ያሳዩ ነበር። ቴያትር የማሳያ ህንጻ ሳይሆን ተዋንያኑ ተውኔቱን ለተመልካቹ የሚያቀርቡበት ስፍራ፣ ጊዜ እና ሁኔታን የሚያመላክት ነው።

ቴያትር ከማዝናናት በተጨማሪ ማህበረሰቡን ለማንቃት፣ ለማስተማር፣ ለማነሳሳት እና ወደ ተሻለ የአኗኗር ባህል ለማሻገር የሚዘጋጅ የጥበብ ዘርፍ ነው። የጥበብ ባለሙያው ደግሞ የማህበረሰብ መሀንዲስ ተድርጎ ይታያል። ቴያትር ለዘመናት ተወዳጅ ሆኖ የዘለቀ ነው። የአልባሳት፣ የተዋንያን፣ የመድረክ ዝግጅት፣ የሙዚቃ፣ የዳንስ፣ እና የተመልካቹ ሁኔታ ትልቅ ሚና አላቸው። ቴያትር ከሌሎቹ የሥነ ጥበብ ዘርፎች በተለየ በህብረትና በጋራ መስራትን የሚፈልግ ነው።

1.5.2. የፊልም ጥበብ

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ስለ ፊልም ጥበብ ምንነት ለጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ ግለጹ

2. ተማሪዎች የፊልም ስራ ለመስራት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ

ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የፎቶ ግራፍ፣ የድምጽ እና የእይታዊ ፈጠራዎች ማደግና መዘመንን ተከትሎ የድራማ እና የቴያትርን የቦታ፣ የጊዜ፣ እና የተደራሽነት ውስንነቶችን በመሻገር የምስል እና ድምጽ ቴክኖሎጅን በመጠቀም መሰራት የጀመረ ጥበብ ነው። በፎቶ ግራፍ ቴክኖሎጂ ተከታታይ የምስል ድግግሞሽን በማብዛት ተንቀሳቃሽ ምስልን ማስገኘት መቻሉ ለፊልም ጥበብ መፈጠር ዋነኛ ምክንያት ሆኗል። ይህም አንድ በእንቅስቃሴ ላይ ያለን ነገር በተከታታይ የጊዜ ርዝማኔ ተደጋጋሚ ፎቶ ግራፎችን ማንሳት ብንችል ተንቀሳቃሽ ምስል(ቪድዮ) ማግኘት እንችላለን። ቆየት ባሉት ጊዜያት የተከታታይ ምስል ሰሌዳዎችን በማሽከርከር የፊልም ጥበብ ለእይታ ይቀርብ ነበር። የፊልም ጥበብ በካሜራ ቴክኖሎጂ እና በአርትኦት ስራ በእጅጉ የሚታገዝ ሲሆን የካሜራ፣ የድምጽ እና የአርትኦት ቴክኖሎጂ ማደግ ለፊልም ጥበብ የምስል የአቀራረብ እና የትረካ መንገዱ መሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ቴያትርም ይሁን ፊልም የደራሲ፣ የአዘጋጅ፣ የተዋናይ እና የትወና ክፍሎች አሏቸው።

1.5.3 የቴያትር እና የፊልም ሰራ ተሳታፊዎች

ተዋናይ

ተዋናይ ቴያትሩን የሚገልጽ ዋናውና ጎልቶ የሚታወቀው የቴያትር ክፍል ነው። ገጸ ባህሪውን ወክሎ መድረክ ላይ የመጫወትና ለተመልካቹ መተወን ማለት ነው። የገጸ ባህሪውን አካል፣ ድምጽ፣ እንቅስቃሴ፣ ስሜት፣ ነፍስ እና ሁኔታ በመዋስ መድረክ ላይ መጫወት ማለት ነው። ቴያትር ያለ ተዋናይ እውን አይሆንም። የተሰጠውን ገጸ ባህሪ ወክሎ መድረክ ላይ የሚጫወት ሲሆን ምናባዊ ገጸ ባህሪውን ለተመልካች የሚገልጽና ሰውኛ ባህሪን የሚያላብስ ነው። ወደ ፊልም ጥበብ ስናመጣው ደግሞ ከመድረክ ላይ አቀራረብ በተለየ ገጸ ባህሪው በሚኖርበት አካባቢ እና መቼት ተወስኖ የመጫወት እና የመተወን ተግባር ነው።



ስዕል 14 ተዋንያን በቴያትር መድረክ ላይ

አዘጋጅ

የቴያትር አዘጋጅ አጠቃላይ የቴያትሩን የተውኔት ክፍሎች እና የቴያትሩን የዝግጅት ሂደት የሚያዋህድ አካል ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። የቴያትሩ አዘጋጅ ለቴያትሩ ድርሰት ህይወት በመስጠት ለተመልካች እንዲቀርብ ያስችላል። አዘጋጁ በተደጋጋሚ ልምምድ ክህሎቱን ሊያዳብር ይችላል። ወይም ደግሞ ከቴያትር እና ፊልም ጥበባት ትምህርት ቤቶች በሚያገኘው እወቀትና ክህሎት ጎበዝ አዘጋጅ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም ተዋንያኑን የመመልመል፣ ድርሰቱን የማስጠናት፣ ዝግጅቱን የመምራት እና ለስኬታማ የቴያትር ስራ አስፈላጊና ዋና ዋና የሆኑ ተግባራትን ያከናውናል።

ደራሲ

የቴያትሩ መሀንዲስ እና ፈጣሪ ነው። የቴያትሩን ድርሰት በተለያዩ አቀራረብ በመድረስ ዝግጁ የሚያደርግ ነው። ታሪኩን፣ ገጸ ባህሪውን፣ መቼቱን፣ ግጭቱን፣ ሴራውን፣ እና ትልሙን በመወሰን ድርሰቱን የሚያዘጋጅ ነው።

ተመልካች

ቴያትሩን በቴያትር ማሳያ ስፍራ ተመልክቶ የሚከታተለው ተመልካች ወይም ታዳሚ ይባላል። በአንዳንድ ቴያትሮች ላይ ተመልካቹ በራሱ የቴያትሩ አካል እንዲሆን በማሰብ የሚሰሩ ቴያትሮች አሉ። በፊልም ጥበብ ደግሞ በሲኒማ ቤቶች በመገኘት መታደም ወይም መመልከት የሚቻል ሲሆን በልዩ ልዩ ዘመናዊ ቁሶች አማካኝነት በቤት ውስጥ ፊልም መመልከት ይቻላል።

ማጠቃለያ

☑ ንድፍ ለሥነ ጥበብ ተግባራት መሰረታዊ ክህሎት ነው። ንድፍ እርሳስ ከሰል እና ቾክ የመሳሰሉ መሳሪያዎችን በመጠቀም መስመሮችን እና የቶን ደረጃዎችን ወረቀት ላይ በማስቀመጥ ስዕል የመሰራት ተግባር ነው። ንድፍ ለቀለም ቅብ፣ ለቅርጽ እና ለሌሎች የሥነ ጥበብ ስራዎች በጣም ጠቃሚ ነው። ንድፍ ሀሳብና ስሜትን ለመግለጽ፣ የነገሮችን ስዕላዊ እቅድ ለማዘጋጀትና ለማጥናት ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

☑ ቅኝት የድምፆች መሰላል ወይም ድምፆች በቅደም ተከተል መደርደር እንደሆነ፣ ቅኝት አብይና ንዑስ ብለን በሁለት እንደምንከፍለው፣ ዲያቶኒክ ባለ ሰባት ድምፅ እና ፔንታቶኒክ ባለ አምስት ድምፅ ቅኝት ተብሎ እንደሚጠራ አይተናል። ንዑስ ቅኝት ናቹራል ንዑስ ቅኝት፣ ሃርሞኒክ ንዑስ ቅኝትና ሜሎዲክ ንዑስ ቅኝት ተብለው በሶስት ይከፈላሉ። ሌላው በዚህ ክፍል ያየነው የድምፅ ቃና ነው። የድምፅ ቃና ማለት የድምፆች ከፍታና ዝቅታ ሲሆን ጂ ቁልፍ ላይ ያሉ ድምፆች ከፍተኛ የድምፅ ቃና ሲሆኑ በኤፍ ቁልፍ ላይ ያሉ ድምፆች ደግሞ ዝቅተኛ የድምፅ ቃና ናቸው። የቁልፍ አመልካች ምልክቶች ሁለት ናቸው። እነሱም ሻርፕና ፍላት ሲሆኑ ሻርፕ አንድን የሙዚቃ ድምፅ በግማሽ እንደሚጨምር ወይም እንደሚያቀጥን ሲያደርግ ፍላት ደግሞ አንድን ድምፅ በግማሽ እንዲወፍር ወይም እንዲቀንስ ያደርጋል። ምልክቶቹም የሻርፕ ምልክት ይህ # ሲሆን የፍላት ምልክት ደግሞ ♭ ነው።

☑ ህዝብን ለማዝናናት እና ለማስተማር የተለያዩ ተውኔቶች መድረክ ላይ ለእይታ የሚቀርቡበት የቴያትር ጥበብ ረጅም እድሜን ያስቆጠረ ሲሆን ትያትሮን ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ነው። ቴያትር ከማዝናናት በተጨማሪ ማህበረሰቡን ለማንቃት፣ ለማስተማር፣ ለማነሳሳት እና ወደ ተሻለ

የአኗኗር ባህል ለማሻገር የሚዘጋጅ የጥበብ ዘርፍ ነው። ደራሲ፣ ተዋንያን፣ አዘጋጅ እና መድረክ የትያትር ዋና አካላቶች ናቸው።

☑ የፊልም ጥበብ የቴያትርን የቦታ፣ የጊዜ፣ እና የተደራሽነት ውስንነቶችን በመሻገር የምስል እና ድምጽ ቴክኖሎጅን በመጠቀም መሰራት የጀመረ ጥበብ ነው። በፎቶ ግራፍ ቴክኖሎጂ ተከታታይ ድግግሞሽን በማብዛት ተንቀሳቃሽ ምስልን ማስገኘት መቻሉ ለፊልም ጥበብ መፈጠት ዋነኛ ምክንያት ሆኗል። ቆየት ባሉት ጊዜያት የተከታታይ ምስል ሰሌዳዎችን በማሽከርከር የፊልም ጥበብ ለእይታ ይቀርብ ነበር። የፊልም ጥበብ በካሜራ ቴክኖሎጂ እና በአርትኦት ስራ በእጅጉ የሚታገዝ ነው። የፊልም ጥበብ እንደ ቴያትር ሁሉ ደራሲ፣ አዘጋጅ፣ እና ተዋናይ የሚኖሩት ሲሆን በሚጠቀመው መሳሪያ፣ በዝግጅት፣ በአርትኦት እና በአቀራረብ ወዘተ የተለየ ነው።

የምዘና ጥያቄ አንድ

ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የቀረቡትን ጥያቄዎች "✓" ምልክት በማድረግ ራሳችሁን መዝኑ

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	የሥነ ጥበብን ምንነት መግንዘብ ችያለሁ		
2	ለንድፍ ስራ አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን መለየት ችያለሁ		
3	የቴየትር ምንነትን ማብራራት እችላለሁ		
4	የፊልም ምንነትን ማብራራት እችላለሁ		
5	የፎቶ ግራፍን ምንነት መግንዘብ ችያለሁ		

የምዘና ጥያቄ ሁለት

ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የቀረቡትን ጥያቄዎች "✓" ምልክት በማድረግ ራሳችሁን መዝኑ።

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	ቅኝት የድምፆች መሰላል መሆኑን ተገንዝቢያለሁ		
2	ቅኝት አብይና ንዑስ ተብሎ በሁለት እንደሚከፈል አውቄያለሁ		

3	የተለያዩ ድምፆችን መነሻ በማድረግ አብይ ቅኝትን መገንባት ችያለሁ		
4	የተለያዩ ድምፆችን መነሻ በማድረግ ንዑስ ቅኝትን መገንባት ችያለሁ		
5	በተለያዩ ድምፆች መነሻነት የተገነቡ አብይ ቅኝቶችን መዘመር ችያለሁ።		
6	በተለያዩ ድምፆች መነሻነት የተገነቡ ንዑስ ቅኝቶችን መዘመር ችያለሁ።		
7	የከፍተኛና ዝቅተኛ የድምፅ ቃናዎችን ልዩነትና አንድነት ለይቻለሁ		
8	ከፍተኛ የድምፅ ቃና ጂ ቁልፍ ላይ፣ ዝቅተኛ የድምፅ ቃና ኤፍ ቁልፍ ላይ እንደሚነበቡ ተገንዝቢያለሁ		
9	በአካባቢየ የሚዘፈኑ ዘፈኖች ቅኝት የተመሰረቱ መሆኑን አውቂያለሁ		
10	የቁልፍ አመልካች ምልክቶች የድምፅ ቀያሪ ምልክቶች እንደሆኑ ተረድቻለሁ		
11	ሻርፕ አንድ ድምፅ ካለው ድምፅ ላይ በግማሽ እንደሚያቀጥን አውቂያለሁ		
12	ፍላት አንድ ድምፅ ካለው ድምፅ ላይ በግማሽ እንደሚያወፍር አውቂያለሁ		

የክፍለ ትምህርት አንድ ማጠቃለያ መልመጃዎች

ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ሙዚቃ ከስነ-ጥበብ ዘርፎች አንዱ የሆነው የፈጠራ ስራ በመሆኑ ነው።
2. የቁልፍ አመልካች ምልክቶች አገልግሎት የሙዚቃ ድምፅን ማወፈርና ማቅጠን ነው።
3. የድምፅ ቃና የምንለው የድምፆች መወፈርና መቅጠን ነው።
4. በጂ እና በኤፍ ቁልፎች መካከል የድምፅ ቃና ልዩነት የለም።

5. የቁልፍ አመልካቾች አብይ ቅኝት ላይ እንጂ ንዑስ ቅኝት ላይ አገልግሎት የላቸውም።

ለ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ።

6. C D E F G A B ይህ የቅኝት ድርድር ምን ይባላል?

7. ሶስት የፈለጋችሁትን ቅኝት /ስኬል/ መነሻ በማድረግ የዓብይ ቅኝት የድምፅ ርቀት (interval) ሰርታችሁ አሳዩ።

8. ባለ አምስት የድምፅ ድርድር ምን ተብሎ ይጠራል?

9. የፍላት እና የሻርፕ አገልግሎት ምንድን ነው? አብራሩ።

10. ንዑስ ቅኝቶች በስንት ይከፈላሉ? ስማቸውን ፃፍ።

11. D፣ E፣ B♭አብይ ቅኝቶችን ጂ እና ኤፍ ቁልፎች ላይ ሰርታችሁ አሳዩ።

12. የንድፍን ምንነት አብራርታችሁ ጻፉ።

13. ንድፍ ለመስራት የሚጠቅሙን መሳሪያዎችን ዘርዝሩ።

14. የቀለም ቅብ እና የቅርጽ ስራ ለመስራት ንድፍ ያለውን ጠቀሜታ አብራሩ።

15. የንድፍ ጥናት ልምምድ ያለውን ጠቀሜታ ግለፁ።

16. በቴያትር ውስጥ የተዋንያን ዋና ድርሻ ምን እንደሆነ አብራርታችሁ ጻፉ።

17. የቴያትር ዋና አካላት ከሚባሉት መካከል ሁለቱን ጻፉ።

18. ቴያትርና ፊልም የሚመሳሰሉበትን ዋና ዋና ጉዳዮች ዘርዝሩ።

19. ለፊልም ጥበብ ማደግና መስፋፋት አወንታዊ አስተዋጽኦ ያበረከቱትን ነገሮች ዘርዝሩ።

20. የፊልም ጥበብ ከቴያትር የሚለይበትን ምክንያት ግለጹ።

21. ከቴያትር ጠቀሜታ መካከል ዋና ዋናዎቹን ጻፉ።

ምዕራፍ 2

የፈጠራ ችሎታን መግለጽ

2.1. ምትን፣ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ድምጾችን ማንበብ

የምዕራፉ ዓላማዎች፡

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- በጂና በኤፍ ቁልፎች የተፃፉ ከፍተኛና ዝቅተኛ የድምፅ ቃናዎችን ማንበብ ትችላላችሁ፣
- ከስታፍ ውጭ በተለያዩ የጊዜ አመልካቾች የተፃፉ ምቶችን ማንበብ ትችላላችሁ፣
- በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ የተፃፉ ቀላል ዜማዎችን ማንበብ (መጫወት) ትችላላችሁ፣
- በከፍተኛና በዝቅተኛ የድምፅ ቃና የተለያዩ ዜማዎችን መዘመር ትችላላችሁ፣
- የድርሰት፣ የቁሳቁስ ቅንብር ቀለም ቅብ፣ የስቴንስል ህትመት፣ የማገጣጠም ቅርጽ መስራት እና የኪነ ጽህፈት የፈጠራ ችሎታችሁን መግለጽ ትችላላችሁ

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ምት ምንድን ነው? ስለ ምት ምንነት ታውቃላችሁ? የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. በየአካባቢያችሁ ዘፈንና እስክስታ ለማድመቅ የምትጠቀሙት ሙዚቃዊ መሳሪያ ከበሮ አመታት ምት እንደሚባል ታውቃላችሁ? እስኪ የምታውቁትን የከበሮ አመታት ለክፍል ጓደኞቻችሁ መትታችሁ አሳዩ።

2.1.1 የምት ምንነት

ምት ማለት ከጊዜ ጋር የሚደረግ የእንቅስቃሴ ተግባር ነው። በሙዚቃ ውስጥ በጣም መሰረታዊ የሚባለው ነገር ምትን ወይም ሪትምን ማንበብ ነው። በተለያዩ ክብረ በዓላት፣ በሰርግና በሌሎች ዝግጅቶች አንድ ዘፈን ሲዘፈን ዘፈኑን ለማድመቅ የምንጠቀመውን አታሞ፣ ድቤ፣ ወይም ሌላ ሙዚቃ መሳሪያ የምንመታው፣ በእጃችን የምናጨበጭበው ምት ይባላል። የከበሮ ምት፣ የዲስኮ ስዓት እንቅስቃሴና የልባችን ትርታ ሁሉም ተግባራት ከጊዜ ጋር የሚከናወን እንቅስቃሴ ነው። እያንዳንዱ ተግባር የሚወስደው የጊዜ ርዝማኔ የጊዜ ዋጋ እንለዋለን። የምት አካሔድ ፍጥነት የሚገለፅበት ደግሞ ቴምፖ (Tempo) ይባላል። ምትን ማንበብ ስታፍ ላይ ወይም ከስታፍ ውጭ በተሰጠው የጊዜ አመልካች ምልክት መሰረት የኖታዎቹን እና የዕረፍት ምልክቶችን የጊዜ ዋጋቸውን ጠብቀን የምንጫወተው የምት ልምምድ ምትን እያዩ ማንበብ ይባላል። ምትና ዜማን እያዩ የማንበብ ችሎታን ለማሻሻል የሚከተሉትን 3 መንገዶች መጠቀም ያስፈልጋል።

1. የምት አካሄዱን ዘግየት አድርጎ መለማመድ
2. በየ ባሩ ከፋፍሎ መለማመድ
3. የተለማመዳችሁትን በመቅረፀ ድምፅ ቀድቶ መስማት።

ምትን እያየን በምናነብበት ጊዜ በታይ የተያያዙ ኖታዎችን ልናገኝ እንችላለን። ታይ ማለት ሁለት ኖታዎችን አንድ ላይ የሚያያይዝ የሙዚቃ ምልክት ነው። ኖታዎችን በምናነብበት ጊዜ ባለ ነጥብ ኖታዎች ካሉ የኖታውን የጊዜ ዋጋ ግማሽ ጨምረን እናነባለን። ይህ ማለት ግማሽ ኖታ 2 ምት አለው ነጥብ ከተጨመረለት 3 ምት ሳናቆራርጥ እንጫወታለን። ምትንም ሆነ ዜማዎችን በምናነብበት ጊዜ እንደ ከበሮ፣ ፀናፅል፣ አታሞ፣ ድቤ የመሳሰሉ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን መጠቀም በጣም ተመራጭ ነው።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ኖታዎች በስዕሉ ላይ የተመለከተውን ፀናፅል በመጠቀም በመጀመሪያ በግል ያለ ሙዚቃ መሳሪያ ከተለማመዳችሁ በኋላ ቀጥሎ በቡድን በቡድን እየሆናችሁ አንብቡ።



ስዕል 15 ጸናፅል የምት ማስጠበቂያ

መልመጃ 2.1

ሀ) የሚከተሉትን ኖታዎች ከኖታዎቹ ስር የተጻፉ ፊደላትን በመጥራት የኖታዎችን የጊዜ ዋጋ ጠብቃችሁ አንብቡ።

1. ♩ ♩ ♩ ♩ ♩ ♩ ♩
   ሀ ሁ ሂ ሃ ሄ ህ ሆ

2 ♪ ♪ ♪ ♪ ♪ ♪ ♪
   አ ቡ ጊ ዳ ሄ ው ዞ

3 ♩ ♪ ♩ ♪ ♩
   ዶ - ሬ - ዶ - ሬ - ዶ

4 ♩ ♩ ♩ ♩ ♩ ♩ ♩ ♩ ♪
   ዶ ዶ ሬ ሬ ዶ ዶ ሬ ሬ ዶ

1



ደ - ኖ - ችን እ ናል ማ

2



ለ) ከዚህ በታች ከስታፍ ውጭ የተፃፉትን ኖታዎች የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጠቀም መጀመሪያ በግል ቀጥሎ በቡድን ተጫወቱ።



ተማሪዎች በስታፍ ላይ የተፃፉ ዜማዎችንና ከስታፍ ውጭ የተፃፉ ምቶችን በምታነቡበት ወይም በምትለማመዱበት ጊዜ በቃል ሸምድዳችሁ ማንበብ የለባችሁም። አነባበቡም አይንን ከኖታዎቹና ከዕረፍት ምልክቶቹ በማድረግ መለማመድ አለባችሁ።

ሐ) ከዚህ በታች በታይ የተያዙና ባለ ነጥብ ኖታዎችን የጊዜ ዋጋቸውን ጠብቃችሁ በምት የሙዚቃ መሳሪያ ታግዛችሁ አንብቡ።



ስዕል 16 የምት ማስጠበቂያ አታሞ



መ) በሚቀጥለው ቁልፍ ላይ በግማሽ ኖታ የተፃፉ ድምፆችን ዶ ሬ ሚ ፋ ሶል ላ የሚባሉ ፊደትን በምት የሙዚቃ መሳሪያ ታግዛችሁ አንብቡ።



ስዕል 17 የምት ማስጠበቂያ አታሞ



ዶ ሬ ሚ ፋ ሶል ላ ሲ ዶ ዶ ሲ ላ ሶል ፋ ሚ ዴ ዶ

1. በሚቀጥለው ቁልፍ ላይ የተፃፉ ድምፆችን የራሳችሁን ፊደል በመተካት አንብቡ።



2.1.2 ከፍተኛና ዝቅተኛ የድምፅ ቃናዎችን መዘመር

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ከምትሰሟቸው ድምፆች ቀጭን ድምፅ የወንድ ነው ወይስ የሴት? መምህራችሁ የሚያሰሟችሁን ድምፅ ቀጭን ወይም ወፍራም በማለት መልስ።

በምዕራፍ አንድ ትምህርታችሁ የድምፅ ቃና የድምፆች ከፍታና ዝቅታ መሆኑን ተምራችኋል። ከፍተኛ የድምፅ ቃና በጂ ቁልፎች ላይ የሚፃፉ ሲሆኑ ዝቅተኛ የድምፅ ቃና ደግሞ በኤፍ ቁልፍ እንደሚፃፉ አይታችኋል። በስታፍ ላይ የተፃፉ ኖታዎችን እና የእረፍት ምልክቶችን የተሰጣቸውን የጊዜ ዋጋ ጠብቆና ከምት ጋር አዋህዶ ማንበብ ዜማን እያዩ ማንበብ ይባላል። አሁን ደግሞ

የሚከተሉትን የድምፅ ቃናዎች በተግባር በመዘመር ትማራላችሁ።



ስዕል 18 ከፍተኛ የድምጽ አወጣጥ

መልመጃ 2.2

1. ከኖታዎቹ ስር የተፃፉትን ፊደላት በመጠቀም ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ዘምሩ።



ዶ ሚ ዶ ሚ ሶል ሚ ሚ ዶ ዶ ሚ ሚ ሶል ዶ ሶል ሚ ዶ



ሚ ሶል ሚ ዶ ሚ ዶ ሚ ሶል ዶ ሚ ሶል ዶ ሚ ዶ ሚ ሚ

2. ከዚህ በታች ጂ ቁልፍ ላይ የተፃፈውን ዜማ የጊዜ ቆይታቸውን ጠብቃችሁ በከፍተኛ የድምፅ ቃና ዘምሩ።



ስዕል 19 የምት ማስጠበቂያ



3. ከዚህ በታች የተፃፈውን ዜማ የ“ሀ” ፊደል ዝርያዎችን በመጥራት ዘምሩ።



ስዕል 20 የምት ማስጠበቂያ



ሀ ሁ ሂ ሁ ሂ ሀ ሀ ሁ ሂ ሁ ሂ ሀ ሁ ሂ ሁሂ ሀ ሁ ሂ ሁሂ ሀ

4) የታሪክ ቅርሳችን በሚል ግጥም የተዛፈውን ዜማ በከፍተኛ የድምፅ ቃና በግልና በቡድን ዘምሩ።



የ ታ ሪክ ቅርሳ ችን መ ለ ያ ሀ ብ ታችን ናቸውሀ ብ ቶ ቻችን እን ጠ ብቅሁላችን

መልመጃ 2.3

1. ከዚህ በታች በኤፍ ቁልፍ ላይ የተዛፈውን ዜማ በዝቅተኛ የድምፅ ቃና አንብቡ። በትክክል ከተጫወታችሁ በኋላ ምን የሚል ዜማ እንደሰጣችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።



ደ ደደ ደደ ደ ደ ደደ ደደ ደ ደደ ደደ ደ ደ ደደ ደደ ደ

2. በኤፍ ቁልፍ የተዛፈውን ዜማ “ላ” የሚለውን ፊደል በመያዝ በዝቅተኛ የድምፅ ቃና አንብቡ።



2.2 ድርሰት (Composition)

ድርሰት ሰዓሊው በምናቡ ያዘጋጀው ሀሳብ ወይም ወደ ተመልካች ለማድረስ፣ ለመናገር የፈለገው ስሜት አደረጃጀት ወይም ሰዓሊው የእይታዊ ጥበባት አናስሮችን ለውስጣዊ ስሜቱ ተገዥ አድርጎ ያሰናዳው የተሟላ ስነ ጥበባዊ ስራ ነው። አንድ ድርሰት አይነ ግብ (subject)፣ ፎርም (Form) እና ይዘት (Content) አለው። አይነ ግብ በአንድ ድርሰት ስራ ውስጥ ወደ አይናችን ቀድሞ የሚገባው ነገር ሲሆን ፎርም ደግሞ በድርሰቱ ውስጥ የስነ ጥበብ አናስሮችና የዲዛይን ህጎች ሁላፊ እና አደረጃጀትን የሚመለከት ነው። ይዘት ደግሞ የድርሰቱ አጠቃላይ መልእክት እና ሀሳብ ነው። ድርሰት በንድፍ፣ በቀለም ቅብ፣ በቅርጽ፣ በህትመት፣ እና በልዩ ልዩ የእይታዊ ጥበባት አሰራሮች ሊቀርብ ይችላል።

በስዕል ስራ ውስጥ ድርሰትን በሁለት መልኩ ልንመለከተው እንችላለን። አንደኛው በምስል የተሰራ ወይም በድርሰቱ ውስጥ ምስል የምናገኝበት ሲሆን ሁለተኛ ረቂቅ ወይም ምስል አልባ ሆኖ ሰዓሊው መናገር የሚፈልገውን ሀሳብ ብቻ ይዞ የሚሰራ ነው። በአንድ ድርሰት ውስጥ ሶስት ክፍሎችን ልናገኝ እንችላለን። የመጀመሪያው ገጸ ባህሪው ያለበት ክፍል (Middleground) ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከገጸ ባህሪው ኋላ ያለው ክፍል (Background) ሶስተኛው ክፍል ደግሞ ከገጸ ባህሪው ፊት ያለው (Foreground) ክፍል ነው።



ስዕል 21 በድርሰት ውስጥ ያሉ ክፍሎች

ድርሰት በሁለት አይነት የፍሬም ቅርጽ መስራት የተለመደ ሲሆን ከዘመናዊ የእይታዊ ጥበባት እንቅስቃሴ ወይም ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ በብዛት ከፍሬም ውጭም የሚዘጋጁ የእይታዊ ጥበባት ድርሰቶች በብዛት እየተለመዱ መጥተዋል። አግድም አቀማመጥ ወደ ጎን የሚረዝም (Landscape) ሲሆን በብዛት የመልክዓ ምድር ስዕሎችን የሚሰሩ ሰዓሊያን የሚጠቀሙት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከታች ወደ ላይ የሚረዝም ሲሆን የከተማ እና የሰው ምስል ከደረት በላይ (Portrait, Cityscape) ድርሰቶችን ለመስራት እንጠቀምበታለን።



ስዕል 22 አግዳሚ (Landscape) እና ቋሚ (Portrait, Cityscape) የድርሰት አቀማመጥ

2.3 የቁሳቁስ ቅንብር ቀለም ቅብ

ቀለም ቅብ ስንል ተግባሩን (መቀባቱን) እና ውጤቱን (ስራውን) ማለታችን ነው። ቀለም ቅብ ቀለሞችን በተገቢው መንገድ በተፈለገው ስፍራ ላይ የመቀባት፣ የመርጨት ወይም የማስቀመጥ ተግባር ነው። የቁሳቁስ ቅንብር ቀለም ቅብ ስንል በአካባቢያን የምናገኛቸውን ልዩልዩ ቀላል ቁሶች ህብር ባለው ቅንጅትና ድርሰት በማስቀመጥ የቅብ ጥናት ማድረግ ወይም መሳል ማለት ነው።





ስዕል 23 የቁሳቁስ ቅንብር ንድፍ ምሳሌ

ቀለም፦ ከብርሃን ጨረሮች የምናገኛቸው ቀለማት የስፔክትረም ቀለማት ይባላሉ። ለምሳሌ የቀስተደመና ወይም የቀለማት ህብርን ወስደን ማየት እንችላለን። የስፔክትረም ቀለማት ቀይ፣ ብርቱካናማ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ፣ ሰማያዊ፣ ሰማያዊ ወይንጠጅና ወይንጠጅ ናቸው። የቀለም መገኛው የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ብርሃን ነው። እያንዳንዱ የብርሃን ጨረር በጎነሶስት ፕሪዝም ውስጥ ተሰብሮ ሲያልፍ እነዚህን ህብረ ቀለማት መገንዘብ እንችላልን።



ስዕል 24 የስፔክተረም ቀለማት ከብርሃን እንዴት እንደሚገኙ የሚያመላክት

ብርሃን ሲኖር በቅጡ እያንዳንዱን ነገር መመልከት እንችላለን፣ ብርሃን ከሌለ ደግሞ ሁሉም ነገር ጨለማ ይሆናል። በብርሃን እና በምናየው ነገር መካከል ትልቅ ትስስር አለ። ቀለም የሰዓሊው ስሜት መወከያ ሀሳብ ማሳረፊያ ሲሆን ነገሮችን ለመወከል የሚያስችለን የእይታ ጥበብ አናስር ነው። ቀለማት የነገሮች መልክ፣ መለያ፣ መገለጫ ሲሆኑ፤ የተለያየ ትርጉምና ውክልና አላቸው።

የቀለማት ጥናት፦ መስራች (የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት) ቀይ፣ ቢጫ፣ እና ሰማያዊ ናቸው። የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት በእኩል መጠን ሲቀላቀሉ ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ያስገኛሉ። እነዚህም ብርቱካናማ፣ ወይነጠጅ እና አረንጓዴ ናቸው። መስራች ቀለማት ከሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ጋር በእኩል መጠን ሲቀላቀሉ የምናገኛቸው ቀለማት ሶስተኛ ደረጃ ቀለማት ይባላሉ። ቀላ ያለ ብርቱካናማ፣ ቀላ ያለ ወይነጠጅ፣ ቢጫማ ብርቱካን፣ ቢጫማ አረንጓዴ፣ እና ሰማያዊ ወይነጠጅ ሶስተኛ ደረጃ ቀለማት ይባላሉ።



ስዕል 25 የመጀመሪያ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ እና ሶስተኛ ደረጃ ቀለማት

የቀለማት ቻርት፦ የቀለማት ቻርት ቀይ፣ ቢጫ፣ ሰማያዊ፣ ቀለማትን መሰረት በማድረግ ቀለማት ባላቸው የባህሪ እና የመልክ ዝምድና መሰረት ተደርድረው የሚቀመጡበት ሰሌዳ ሲሆን፣ በቀለማት መካከል ያለውን ዝምድና ያሳየናል። እያንዳንዱ ቀለም ያለውን የባህሪ ዝምድና፣ ተመሳሳይነት፣ ተወራራሽነት እና ተጻራሪነት ለመረዳትም ያስችለናል።

የተግባር ስራ

✍ ከታች ያለውን የቀለም ቻርት ስዕል ምሳሌ በማድረግ በውሃ ቀለም የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማትን እርስ በርስ እያቀላቀላችሁ የቀለም ቻርት ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።



ስዕል 26 በልዩ ልዩ ዲዛይን የተዘጋጁ የቀለም ቻርቶች

ፍካት (value) የቀለማት ንፅፅራዊ የሆነ የብርሃናማነት እና የጥቁረት ዋጋ ወይም ደረጃ ነው።



ስዕል 27 የቀለማት የፍካት ደረጃ

የተግባር ስራ

- ተማሪዎች ከላይ ባለው የፍካት ምሳሌ መሰረት የውሃ ቀለምን በመጠቀም የቀለማትን የፍካት ደረጃ በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ።
- የአሰራር ቅደም ተከተል መጀመሪያ፦ የውሃ ቀለም፣ ብሩሽ፣ የቀለም መበጥበጫ ንጹህ ውሃ፣ ንጹህ ጨርቅ፣ እርሳስና ላጲስ፣ ወፍራም የስዕል ወረቀት እና የስዕል ማስደገፊያ አዘጋጁ፤ሁለተኛ፦ በወፍራም ወረቀት ላይ በክብ ወይም በአራት ማዕዘን ዘጠኝ ተከታታይ ዲዛይኖችን በእርሳስ ንድፍ ስሩ፤ ሶስተኛ፦ ቀለማቱን በውሃ በተለያየ መጠን በማቅጠን በወፍራም ወረቀት ንድፉ ላይ በብሩሽ በመጠቀም የፍካት ደረጃቸውን ጠብቆ መቀባት፣ ሲደርቅ ጠብቃችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

የቀለማት ባህሪ፦ ቀለማት እንደሚኖራቸው መልክ ተሰማሚ ከሆነ ስሜት ጋር የሚተሳሰሩ ሲሆን የሞቃት እና የመቀዝቀዝ ስሜት አላቸው። ሞቃት ቀለማት ከእሳት እና ከፀሐይ ጋር የሚዛመዱ ሲሆን የደስተኝነት እና የጋለ ስሜትን ይገልፃሉ። ቀዝቃዛ ቀለማት ደግሞ ከውሃ ከእፅዋትና ከሰማይ ጋር የሚዛመዱ ሲሆን መከፋትን እና ጨለምተኝነትን የሚገልፁ ናቸው።



ስዕል 28 ስለ ሞቃትና ቀዝቃዛ ቀለማት

በቀለም ቻርት ላይ የራሱ የሆነ የሞገድ ርዝመት ያለው እያንዳንዱ ቀለም ብቸኛ ቀለም አንድ ቀለም (monochromatic) ይባላል። በቀለም ቻርት ላይ ትይዩ ሆነው የሚቀመጡ ሁለት ብቸኛ ቀለማት ተፃራሪ (complimentary colors) ቀለማት ይባላሉ። እነዚህ ተፃራሪ ቀለማት ቢቀላቀሉ ገለልተኛ የሆነ ቀለምን ከማስገኘት ውጭ ቢጫና ቀይ ተቀላቅለው ብርቱካናማን እንደሚሰጠን አይነት በቀለም ቻርት ላይ የሚቀመጥ ቀለም አያስገኙም። ተወራራሽ ቀለማት (Analogous) በቀለማት ቻርት ላይ የሚዛመዱና ተወራራሽነት ያላቸው ቀለማት ናቸው።



ስዕል 29 አንድ ቀለም፣ ተጻራሪ ቀለማት፣ እና ተወራራሽ ቀለማት

የቀለም ቅብ መስሪያዎች

የቀለም ቅብ መስሪያዎች ስንል ቀለም ቅብ ለመስራት የምንጠቀማቸው መሳሪያዎች ማለታችን ሲሆን በዋናነት ቀለም፣ ወረቀት ወይም ሸራ፣ የቀለም መቀቢያ ብሩሽ፣ የስዕል ማስደገፊያ፣ የቀለም ማቅጠኛ፣ እና መጠራረጊያ ጨርቅ ሊያስፈልጉን ይችላል።

የዘይት ቀለም (Oil) የዘይት ቀለም ስንል ቀለማትን በዘይት እንዲሟሙና እንዲበጠበጡ አድርጎ በማዘጋጀት ለቀለም ቅብ ስራ የምንጠቀምበት ነው። የዘይት ቀለም በዘይት የሚበጠበጥ ቢሆንም ከሌሎቹ ቀለም አንጻር ቶሎ የሚደርቅ ቀለም አይደለም።

ፓስቴል ቀለም (Pastel) በእርሳስ ወይም በእንጨት መልክ የሚዘጋጅ ቀለም ሲሆን ዱቄት ቀለም ላይ ማጣበቂያ በመቀላቀል የሚዘጋጅ ሲሆን ይዘቱ ከሌሎቹ ቀለማት ጋር ልዩነት አይኖረውም። ካጠቃቀም ልዩነት ውጭ።

አክሬሊክ ቀለም (Acrylic) በጣም ቶሎ የሚደርቅ የቀለም አይነት ነው። በውሃ እና በዘይት እዲሟሟ ተደርጎ የሚዘጋጅ ሲሆን በተለያዩ ዓይነት ብሩሾች እና ማንኪያዎች በመቀባት እንጠቀምበታለን።

የውሃ ቀለም (watercolor) እንደ አክሬሊክ እና ዘይት ቀለም ዓይነት ሲሆን በውሃ የሚበጠበጥ ቀለም ነው። የውሃ ቀለም በወረቀት፣ እና ሌሎች ተስማሚ በሆኑ ነገሮች ላይ ልንጠቀምበት እንችላለን።

የስዕል ማስደገፊያ /ኢዝል/ ሰዓሊው በተመቸ ሁኔታ ሆኖ እንዲሰራ ለማስደገፊያነት የሚጠቀምበት ሲሆን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ሆኖ ከቀላል እስከ ትልቅ ሊዘጋጅ ይችላል።

ብሩሽ ቀለማትን ለመቀባት የምንጠቀምበት መሳሪያ ሲሆን እንደየቀለም አይነቱ የተለያየ ሆኖ ይዘጋጃል። የውሃ ቀለም ብሩሽ እና የዘይት ቀለም ብሩሽ በቀለም ቅብ የተለመዱ የብሩሽ አይነቶች ናቸው።

የቀለም ማቀላቀያ ሳህን (ፓሌት) ይህ ሳህን ልዩ ልዩ ቀለማት ለማቀላቀል የሚጠቅመን ሲሆን በብሩሽ እየቆነጠርን ለመቀባት ይረዳናል።

ቀለም ማቅጠኛ፦ ቀለማትን ለማቅጠን የሚጠቅመን ሲሆን የውሃ ቀለም ከሆነ ውሃን ለማቅጠኛ እንጠቀማለን። የዘይት ቀለም ከሆነ ደግሞ ዘይት እንደ

ማቅጠኛ እንጠቀማልን።




ስዕል 30 የውሃ ቀለም፣ የዘይት ቀለም





ስዕል 31 የቀለም መቀላቀያ ሳህን፣ ብሩሽ እና ቋሚ የስዕል ማስደገፊያ (ኢዝል)

2.3.1 የቁሳቁስ ቅንብር ቀለም ቅብ አሰራር

የቁሳቁስ ቅንብር ንድፍ ከመስራታችን በፊት የንድፍ ልምምድ በተደጋጋሚ ማድረግ እና ጥሩ የንድፍ ስራ ችሎታን ማዳበር ለሁሉም የእይታዊ ጥበብ ተግባራት መሰረት ነው። ከዚህ በታች የተቀመጡትን ቅደም ተከተሎች በትክክል በመለማመድና በመፈጸም የቁሳቁስ ቅንብር ንድፍ መስራት ትለማመዳላችሁ።

አስፈላጊ መሳሪያዎች

✍ ወፍራም የስዕል ወረቀት፣ የውሃ ቀለም፣ የቀለም ማቀላቀያ ሳህን፣ ንፁህ ውሃ፣ የጨርቅ ቁራጭ፣ እርሳስ፣ የእርሳስ ማጥፊያ፣ መቅረጫ፣ የስዕል ማስደገፊያ ቦርድ፣ ሞዴል የቁሳቁስ ቅንብር ንድፍ አስፈላጊ ናቸው።

የአሰራር ቅደም ተከተል

✍ በመጀመሪያ ሞዴል ቁሳቁሶችን አቀናብሮ ምቹ በሆነ ቦታ ማስቀመጥ፣

የስዕል ማስደገፊያውን በመጠቀም በወፍራም ወረቀት ላይ ሞዴል የቁሳቁስ ቅንብሩን በስሱ በእርሳስ መንደፍ፣ አስፈላጊ የሆኑ ቀለማትን በስዕል መቀላቀያ ሰሃኑ ላይ ማፍሰስ የውሃ ቀለም ከብርሃናማው በመጀመር ሲደርቅ እየጠበቁ በብሩሽ እየቆነጠሩ ንድፉ ላይ በመቀባት መለማመድ

በውሃ ቀለም የቁሳቁስ ቅንብር ቀለም ቅብ ልምምድ

ሀ) የቁሳቁስ ቅንብር ሞዴል ማዘጋጀት



ለ) ሞዴሉን መንደፍ



ሐ) ሞዴሉን በውሃ ቀለም ቀስበቀስ መቀባት መ) ሞዴሉን በውሃ ቀለም ቀብቶ ማጠናቀቅ





መልመጃ 2.4

1) ከታች የተቀመጡትን የቁሳቁስ ስዕሎች በቀለም ቅብ ስሩ።

ሀ)





ለ)







ሐ)





2.4 ማያያዝና መገጣጠም (Assembling)

ይህ ስነ ጥበባዊ አሰራር በዋናነት በልጅነታችን በሸቦ በአገዳ እና በመሳሰሉ ቀላል ቁሳቁሶች የምናዘጋጃቸውን መጫወቻዎች የሚያስታውሰን ነው። በማያያዝ፣ በመገጣጠም፣ በመስፋት እና አቀናጅቶ በመጠቀም የተለያዩ ቁሶችን አንድ ወጥ ወደ ሆነ ስነ ጥበባዊ ስራ ማምጣት ወይም ማዘጋጀት ማለት ነው። በዓለማችን የወዳደቁና ግልጋሎታቸውን የጨረሱ ቁሳቁሶችን እንደገና በመገጣጠም የተለየ መልእክትና ውክልና በመስጠት ስነ ጥበባዊ ስራዎችን የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች በርካታ ናቸው። ይህ የቅርጽ አሰራር ስልት ከሶስቱ አንጻር ያለገደብ በርካታ ቁሳቁሶችን በጋራ ወይም በተናጠል ለመጠቀም የተመቸ ነው።



ስዕል 32 መኪና፣ ወፍ እና ድመት

የማያያዝና መገጣጠም (Assembling) አሰራር እና አስፈላጊ መሳሪያዎች

አስፈላጊ መሳሪያዎች

- ልዩ ልዩ ሸቦ ቁርጥራጮች፣ የካርቶን እና ባለቀላም ወረቀቶች፣
- የጨርቅ ቁርጥራጮች፣ የፕላስቲክ ቁሳቁሶች፣
- የአገዳ ስብርባሪዎች፣ የእንጨት ቁርጥራጮች፣
- ገመድ፣ ሸቦ ወይም ሌላ ማያያዣ የሆነ ነገር፣ እና ሌሎች መሰል ቁሳቁሶችን መጠቀም እንችላለን

አሰራር

- መስራት የምንፈልገውን ነገር መለየትና አስፈላጊ ቁሳቁሶችን መወሰን
- ልንሰራው እንደፈለግነው በቅደም ተከተል ማያያዝና መገጣጠም

✍ ለሰራነው ስነ ጥበባዊ ስራ ተገቢን ትኩረት በመስጠት ማስቀመጥ

የተግባር ስራ

✍ በአካባቢያችሁ ያሉ ቀላል እና አገልግሎታችሁን የጨረሱ ቁሳቁሶችን በመጠቀም እንሰሳትን እና ሌሎች መገልገያ ቁሶችን በመገጣጠምና በማያያዝ የቅርጽ ሰራዎች አዘጋጅታችሁ ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።

✍ በማገጣጠምና በማያያዝ ቅርጽ የመስራት ዘዴ መማራችን የሚኖረውን ጠቀሜታ ለጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ ተናገሩ።

✍ ስለ ስራችሁ ገለጻ በማድረግ ከጓደኞቻችሁ ጋር የሂስና አድናቆት ውይይት አካሂዱ።

2.5 የስቴንስል ህትመት

የስቴንስል ህትመት ከህትመት አሰራሮች መካከል አንዱ ሲሆን ሊታተም የተፈለገውን ነገር ከወረቀት ላይ ወይም ሌላ ሰሌዳ ላይ ቆርጦ በማውጣት ሙሉ በሙሉ ቀለም እንዲያሳልፍ አድርጎ በማዘጋጀት የማተም ሂደት ነው።

ሀ) በስቴንስል ተቀርፆ የተዘጋጀ ለ) በስቴንስል ህትመት የታተመ ስዕል



ስዕል 33 ወደላይ ቀርፆ የማውጣት ህትመት ስራዎች

የአሰራር ቅደም ተከተል እና አስፈላጊ መሳሪያዎች

አስፈላጊ መሳሪያዎች

- ወረቀት፣ መቀስ፣ መቁረጫ
- የህትመት ቀለም፣ ወይም ስፕሬይ ቀለም፣ ስፖንጅ፣ ጨርቅ
- ምስል ተቀባይ ወረቀት፣ ሌሎች ምቹ የሆኑ ሰሌዳዎች

የአሰራር ቅደም ተከተል

- መጀመሪያ እንዲታተም የምንፈልገውን ነገር መወሰን እና ምስል ተሸካሚው ላይ መንደፍ
- መቁረጫውን በመጠቀም እንዲታተም የሚፈለገው ነገር ቆርጦ ማውጣት እና ቀሪውን ክፍል ማዘጋጀት
- የተቀረጸውን ክፍል ምስል ተቀባይ ወረቀት ላይ ማስቀመጥ
- ስፕሬይ ቀለም መንፋት፣
- የህትመት ቀለም ከሆነ በስፖንጅ ወይም በጨርቅ ከላይ መቀባት



ስዕል 34 የስቴንስል ህትመት

የተግባር ስራ

✍ ተማሪዎች ወፍራም ወረቀት ላይ ፊደላትን በመንደፍ በመቁረጫ ቀርፃችሁ የስቴንስል ህትመት ስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

2.6 ኪነ ጽህፈት (Calligraphy)

ኪነ ጽሑፍ የእጅ ጽሁፍ ጥበብ ማለት ነው። የፊደላትን መልክ መሻሻል የምናሳይበት መልኩን የአቀራረቡን ቅርጽ፣ አቋሙን፣ በነጠላ፣ በብርሃን እና ጥላ፣ በቀለም በማስጌጥ የምናሳይበት የግራፊክስ ጥበብ ዘርፍ ነው። በፊደሎች አቀማመጥ፣ ቅርጽ እና አፃፃፍ ላይ የሚያተኩር የግሪፊክስ ዘርፍ ነው። ኪነ ጽሁፍ ፊደሎችን መፃፍ ወይም መጠቀም ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የፊደሎቹን አጣጣል ውፍረት እና ርዝማኔ ቅርፅ የብርሃንና ጥላ አወደደቃቸውን በማጥናት እና በማሻሻል ዛሬ የምንጠቀምበትን የፊደል ቅርጽ እንድናገኝ አስችሎናል። የኪነ ጽሑፍ ጥበብ የፊደላትን ውበት ቅርፅ ቃላትን ስንፅፍ ሊሠጡት ከሚችሉት ትርጉም ጋር በማስተሳሰር ሠዎች በእይታ እንዲግባቡ ወይም ፊደላትን ቀላል እና ውስብስብ ማራኪና የሚያነቃቃ በማድረግ በእይታ እንድንግባባ የሚያስችለን የግራፊክስ ጥበብ ዘርፍ ነው።

የአማርኛ ፊደላትን በቀላሉ በነጠላ፣ በብርሃን እና ጥላ ጽሁፍን መጻፍ እንችላለን። ሰዓሊ ይገዙ ብስራት ከመደበኛው አጻጻፍ ውጭ ወንዴ ልዩ ልዩ የተጌጡ ፊደላቶችን በማዘጋጀት በጥቅም ላይ ያዋሉ ሲሆን በተለያዩ የሀረግ ስራዎች እንዲያሸበርቁ አድርገው ሰርተዋቸዋል።

ሀ) የነጠላ ፊደላት አጣጣል በአንድ መጻፊያ ፊደላትን አሳምሮ የመጻፍ ተግባር ነው።



ለ) ፊደላትን በብርሃንና ጥላ አሳምሮ መጻፍ





ሐ) በሰዓሊ ይገዙ ብስራት የተዘጋጁ ልዩ ልዩ የፊደላት አጣጣል በከፊል



በቅጠሎች የተጌጡ ፊደላት በከፊል



የተግባር ስራ

- በስዕል ደብተራችሁ ላይ ፊደላትን በነጠላ አጣጣል በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ
- ሁለት መጻፊያዎችን በማሰር ወይም በመደረብ ፊደላትን ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ
- ስማችሁን በልዩ ልዩ ጌጠኛ ፊደላት በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ
- ፊደላትን በመጻፍ ብርሃንና ጥላ በመስራት ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ
- ሰላም የሚለውን ጽሁፍ ደብተራችሁ ላይ በትልቁ በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ

2.7 በቴያትር፣ ፊልም እና ፎቶ ግራፍ ሀሳብና ስሜታችንን መግለጽ

ቴያትር ሀሳብና ስሜታችንን ለመግለጽ የሚያስችለን የሥነ ጥበብ ዘርፍ ነው። መጽሐፍት ብዙ ነገር ላይ ያተኩራሉ። ሙዚቃ ድምጽ ላይ ያተኩራል። ቀለም ቅብ ቀለማት እና የእይታ ጥበብ አናስሮች ላይ ያተኩራል። ቴያትር ግን ሰው እና የሰው ልጅ ላይ ብቻ ያተኩራል። የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች በተለያየ ጊዜና መድረክ ለተመልካች የሚቀርቡ ቢሆንም ዋናው ትኩረት ሰው ነው። ቴያትር በቡድን የሚሰራ እና ለታዳምያን የሚቀርብ ነው። ከሌሎቹ የሥነ ጥበብ ዘርፎች በተሻለ የቡድን ስራ እና ቅንጅት እንዲሁም ምልከታ የሚጎላበት ነው። የቡድን ቅንጅቱ እና አሳታፊነቱ ወደ ታዳሚያን የሚተላለፍ ሲሆን ታዳሚያኑ ከተመልካችነት በተጨማሪ ቴያትሩ አካል ሆነው ውሀደት ይፈጥራሉ።



ስዕል 35 ህጻናት ተዋንያን የቴያትር ስራ በማሳየት ላይ

ከቴያትር መድረክ ጀርባ ያሉት ተዋንያን፣ ደራሲ፣ አዘጋጅ፣ የመድረክ ዲዛይነር እና ከሌሎች ተሳታፊ አካላት በተጨማሪ የቴያትሩ ታዳሚዎች በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው። ቴያትር የተለያዩ ማህበረሰባዊ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት ወደ መድረክ ያመጣቸዋል። ማህበረሰቡን በማስተማር በመተቸት በማነቃቃት እና ወደ ተሻለ ማህበረሰባዊ እድገት ለማድረስ ትልቅ ሚና አለው።

በቴያትር ውስጥ ልጆችና ህጻናት ተሳትፎ የሚያደርጉ ሲሆን ከታላላቅ ቴያትር ቤቶች በተጨማሪ የህጻናትና ወጣቶች ቴያትር ቤት በሀገራችም ይሁን በሌሎች ሀገራት ተቋቁመው ህጻናት ከመዝናናት እና ራስን ከማስደሰት በተጨማሪ አስተማሪ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮችን በመድረስ፣ በማዘጋጀት፣ በመተወን፣ በመድረክ ዝግጅት፣ በሙዚቃና ዳንስ፣ በአልባሳት ዲዛይን እና በተመልካችነት በቴያትር ውስጥ በቀጥታ ይሳተፋሉ።

የፊልም ጥበብ ምንም እንኳን በካሜራ ቴክኖሎጂ፣ በአርትኦት፣ በተሳታፊ ብዛት፣ በአልባሳትና በቀረጻ ቦታ በክፍል ውስጥ ለመስራት የሚያስቸግር ቢሆንም በቀላሉ ቡድን ከጓደኞቻችን ጋር በመሆን አጫጭር ቀረጻዎችን በሞባይል ካሜራ በመቅረጽ ክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችን ስሜቶቻችንን እና የፈጠራ ስራችንን ማጋራት እንችላለን።

ፎቶ ግራፍ በተከታታይና በአንድ ጊዜ በምናደርገው የፎቶ ማንሳት ተግባር የሁኔታዎችን ልዩነት እና መልዕክት መግለጽ ያስችለናል። ወቅቶችን፣ ክብረ በዓላትን፣ ሰርግ፣ የትምህርት ቤት ቆይታን፣ ጨዋታችንን፣ የገብያ ስፍራን፣ እጽዋት፣ መልክዓ ምድር ገጽ እና ሌሎች በርካታ ክንውኖችን በፎቶ ግራፍ በማንሳት መልዕክት ማስተላለፍና ስሜትን መግለጽ ይቻላል። ፎቶ ግራፍ እንደ ቴያትር መድረክ ላይ የሚተወን አይደለም። ያነሳናቸውን ፎቶ ግራፎች በማሰባሰብ የፎቶ ግራፍ አውደ ርዕይ ማሳየት ግን እንችላለን። ለተመልካቹ ማድረስ የምንፈልገውን ሀሳብና ስሜት ለማስተላለፍ እንጠቀምበታለን።



ስዕል 36 የፎቶ ግራፍ አውደ ርዕይ

የተግባር ስራ

- ከታተሙ የቴያትር ድርሰት መጽሐፍት ወይም በቪድዮ የተቀረጹ የቴያትር ስራዎችን ምሳሌ በማድረግ በቡድን በመሆን አንድ አጭር የቴያትር ክፍል በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ ለመምህራችሁ አሳዩ።
- የሞባይል ካሜራ በመጠቀም በጥንድ እና በቡድን ሆናችሁ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ አጭር ቀረጻ በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።
- በአዘጋጃችሁት አጭር ቪዲዮ ለማሳየት ወይም ለመግለጽ የፈለጋችሁትን ስሜትና ሀሳብ ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።
- የሞባይል ካሜራ በመጠቀም በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የምትመለከቱትን ነገር ፎቶ በማንሳት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ማስተላለፍ የፈለጋችሁትን ሀሳብና ስሜት ተናገሩ።

የምዕራፉ ማጠቃለያ

☑ ድርሰት ሰዓሊው በምናቡ ያዘጋጀው ሀሳብ ወይም ወደ ተመልካች ለማድረስ፣ ለመናገር የፈለገው ስሜት አደረጃጀት ወይም ሰዓሊው የስነ ጥበብ አናስሮችን ለውስጣዊ ስሜቱ ተገዥ አድርጎ ያሰናዳው የተሟላ ስነ ጥበባዊ ስራ ነው። በሁሉም የእይታዊ ጥበባት ስራዎች ውስጥ ድርሰት ትልቅ ስፍራ አለው።

☑ የቁሰቁቀስ ቅንብር ቀለም ቅብ ተግባር በዋናነት የተለመሰ የስዕል ትኩረት ሲሆን ቁሳቁሶቹን እና በቁሶቹ ላይ የሚያርፈውን ብርሃን በማጥናት አስፈላጊ ተግባር ነው። ይህን ተግባር ለማከናወን ቀለም እና የቀለምን የአደበላለቅ ጥናት ማወቅ መሰረታዊ ትምህርት ነው። በመቀጠልም ትኩረት ሰጥቶ የተግባር ልምምድ ማድረግ የተሻለ የቁሳቁስ ቀለም ቅብ ስራ ለመስራት ያስችላል።

☑ ማገጣጠምና ማያያዝ ከቅርጽ የአሰራር ክፍሎች አንዱ ሲሆን በአካባቢያችን ያለ ቁሳቁሶችን ያለ ገደብ በግብዓትነት እንድንጠቀም እና ለተሻለ ሀሳብና ስሜት መገለጫ እንድናውለው ያስችለናል። በተለይም አገልግሎታቸውን ጨርሰው በቆሻሻ መልክ የሚጣሉ ቁሶችን እንደገና ለመጠቀምና አዲስ ማንነት በመስጠት ሀሳባዊ ውክልናን ለመፍጠር ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

☑ የስቴንስል ህትመት ከህትመት አሰራሮች አንዱ ሲሆን ልዩልዩ ስዕሎችን እና ዲዛይኖችን በህትመት ለማዘጋጀት የተመቸ አሰራር ነው። በዋናነት እንዲታተም የተፈለገውን ነገር ቅርጽ ቆርጦ በማውጣት በቀሪው ክፍል ቀለም እንዲያልፍበት በማድረግ የሚታተው አሰራር ነው። ኪነ ጽህፈት የእጅ ጽሁፍ ጥበብ ሲሆን ፊደላትን አሳምሮ መጻፍ ማለት ነው።

☑ ቴያትር ፊልም እና ፎቶ ግራፍ የክውን ጥበባት አካል ሲሆኑ ስሜታችንን ለመግለጽ እና ለማስተላለፍ እንጠቀምባቸዋለን። ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት ማህበረሰቡን ለማስተማር ለማዝናናት እና ወደ ፊት ለማራመድ ትልቅ ድርሻ አላቸው።

☑ በምዕራፍ ሁለት ትምህርታችሁ በሙዚቃ ውስጥ ምትን ወይም ሪትምን ማንበብ በጣም መሰረታዊ ነገር እንደሆነ፣ ምትን ከዜማ ውጭና ከዜማ ጋር ልናነበው እንደምንችል፣ ከዜማ ውጭ የምንለው ስታፍ አልባ የኖታዎችንና የእረፍት ምልክቶቻቸውን የጊዜ ዋጋ ጠብቀን እያየን የምንጫወት ከሆነ

ነው።

☑ ዜማን ማንበብ የምንለው ደግሞ ስታፍ ላይ ባሉ መስመሮችና ክፍት ቦታዎች ላይ የተፃፉትን ኖታዎች ድምፃቸውንና የጊዜ ዋጋቸውን ጠብቀን ስንጨወት ዜማን ማንበብ ይባላል። ሌላው በዚህ ክፍል የተማራችሁት ስለ ከፍተኛና ዝቅተኛ የድምፅ ቃናዎች ቃናዎች ነው። ከፍተኛ የድምፅ ቃናዎች የምንላቸው ጮኸ ብለን እንድንጫወት የሚያደርጉ በጂ ቁልፍ ላይ የተፃፉ ዜማዎች ሲሆኑ የሴትች ቀጭን ድምፅ ለከፍተኛ የድምፅ ቃና ምሳሌዎች ናቸው። ዝቅተኛ የድምፅ ቃናዎች የምንላቸው ደግሞ ብዙውን ጊዜ በወፍራም የወንዶች ድምፅ የሚወከሉና ኤፍ ቁልፍ ላይ የተፃፉ ዜማዎች ናቸው።

የምዘና ሰንጠረዥ አንድ

ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የቀረቡትን ጥያቄዎች በ ✓ ምልክት በማድረግ ራሳችሁን መዝኑ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	የድርሰትን ምንነት ተገንዝቤያለሁ		
2	የቁሳቁስ ቅንብር ቀለም ቅብ ለመስራት አስፈላጊ የሆኑ ቅደም ተከተሎችን መለየት ችያለሁ		
3	በማያያዝና በመገጣጠም ቅርጽ እንዴት እንደሚሰራ መለየት ችያለሁ		
4	የስቴንስል ህትመት እንዴት እንደሚሰራ መናገር እችላለሁ		
5	የአማረኛ ፊደላትን ኪነ ጽህፈት በልዩ ልዩ መልኩ መስራት እችላለሁ		
6	በፊልም በቴያትር እና በፎቶ ግራፍ ስሜቴን መግለጽ ችያለሁ		

የምዘና ሰንጠረዥ ሁለት

ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የቀረቡትን ጥያቄዎች በ✓ምልክት በማድረግ ራሳችሁን መዝኑ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
10	በፊልም በቴያትር እና በፎቶ ግራፍ ስሜቴን መግለጽ ችያለሁ		
11	በሙዚቃ ውስጥ በጣም መሰረታዊ የሚባለው ምት መሆኑን ተገንዝቢያለሁ		
12	ከስታፍ ውጭ ያሉ ኖታዎችን የምት አካሔዱን ጠብቆ መጫወት ምትታዊ የእይታ ንባብ እንደሚባል አውቂያለሁ		
13	እይታ ንባብ ዜማን እና ምትን ማንበብ እንደሆ አውቂያለሁ		
14	ምትንም ሆነ ዜማዎችን ለማንበብ የምት ማስጠበቂያ የሙዚቃ መሳሪያ መጠቀም እንደሚገባ ተረድቻለ		
15	በስታፍ ላይ የተፃፉ ምቶችንና ዜማዎችን አቀናጅቸ ማንበብ ችያለሁ		
16	ቅኝቶችን በተለያዩ ሚጀር ስኬሎች ለመገንባት ከሲ ቅኝት ውጭ ድንገተኛ ምልክትን እንደሚጠቀሙ አውቂአለሁ		
17	የከፍተኛና ዝቅተኛ የድምፅ ቃናዎችን ልዩነትና አንድነት ለይቻለሁ		
18	ከፍተኛ የድምፅ ቃና ጂ ቁልፍ ላይ፣ ዝቅተኛ የድምፅ ቃና ኤፍ ቁልፍ ላይ እንደሚፃፉ ተገንዝቢያለሁ		
19	የቁልፍ አመልካች ምልክቶች የድምፅ ቀያሪ ምልክቶች እንደሆኑ ተረድቻለሁ		
20	ሻርፕ አንድ ድምፅ ካለው ድምፅ ላይ በግማሽ እንደሚያቀጥንና ፍላት ደግሞ ግማሽ እንደሚያወፍር ተገንዝቢያለሁ		

የማጠቃለያ መልመጃዎች

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ በማንበብ መልሱን ስጡ።

   1. የድርሰትን ምንነት አብራርታችሁ ጻፉ።
   2. የቀለምን ምንነት እና መገኛውን ግለጹ።
   3. የቁሳቁስ ቅንብር ቀለም ቅብ ለመስራት የምንጠቀማቸውን ቁሳቁሶች ዘርዝሩ።
   4. በመጽሐፉ ውስጥ የቀለም ቅብ መሳሪያዎች ተብለው ከተዘረዘሩት ሁለቱን ጥቀሱ።
   5. ለስቴንስል ህትመት ስራ አስፈላጊ ከሆኑ መሳሪያዎች መካከል ሶስቱን ተናገሩ።
   6. ማያያዝና መገጣጠም የቅርጽ ስራ የሚኖረውን ጠቀሜታ አብራርታችሁ ተናገሩ።

2. የሚከተሉትን ምታዊ የዕይታ ንባቦች በፈለጋችሁት የምት የሙዚቃ መሳሪያ ታግዛችሁ ተጫውታችሁ አሰሙ።

10



11



12



4. ከዚህ በታች ስታፍ ላይ የተጻፉ ዜማዎችን በግልና በቡድን ዘምራችሁ አሰሙ።

1



2



3



ምዕራፍ 3

የሀገራችንን ታሪክ በሥነ ጥበባት መተረክና መግለጽ

የምዕራፉ ዓላማዎች፡

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- በእይታዊ ጥበባት የሀገራችሁን ታሪክ መተረክ እና መግለጽ ትችላላችሁ፤
- ስዕላዊ መግለጫ በመስራት የሀገራችሁን ታሪክ ትገልጻላችሁ፤
- ቴያትር ፊልም እና ፎቶ ግራፍን በመጠቀም የሀገራችሁን ታሪክ መግለጽ ትችላላችሁ፤
- ፉከራና ቀረርቶን በመጠቀም የጀግኖች አባት አርበኞችን ታሪክ መተረክ ትችላላችሁ፤
- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የታሪክ አንድ አካል መሆናቸውን ትገነዘባላችሁ፤
- በሙዚቃ ታሪክንና ጀግንነትን መተረክና ማስተላለፍ እንደሚቻል ታውቃላችሁ፤

3.1 በእይታዊ ጥበባት የሀገራችንን ታሪክ መተረክና መግለፅ

እይታዊ ጥበባት የሀገራችንን ታሪክ ለማስታወስና ለማስተማር ትልቅ አስተዋጽኦ ያላቸው ሲሆን እይታዊ ጥበባት የምንላቸው ቀለም ቅብ፣ ስዕላዊ መግለጫ፣ ቅርጽ፣ እና ሌሎች አሰራሮች ታሪካችንን ለትውልድ ለማስተላለፍና ለማስተማር ትልቅ ሚና አላቸው። በዚህ ክፍል ስዕላዊ መግለጫን በመጠቀም እንዴት የሀገራችንን ታሪክ መተረክና መግለጽ እንደምንችል እንማራለን።

3.1.1 ስዕላዊ መግለጫ (Illustration)

ስዕላዊ መግለጫ በጽሑፍ የቀረበን ታሪክ ፤ ድርሰት ፤ዘገባ ፤ተረት፤ ወዘተ በስዕል መግለፅ ማለት ነው። ከተለያዩ የሰነ-ጽሑፍ ስራዎች በመነሳት (ከመጽሐፍት፣ ከትረካ፣ ከጋዜጣ፣ ከተረት ወዘተ) ለስነ ጽሁፉ ገላጭ ስዕል በማዘጋጀት መተረክ እና መግለጽ ማለት ነው። የአሰራር ቅደም ተከተሉን ከተመለከትን በኋላ የሀገራችንን ታሪክ በስዕል የሚተርክ ስዕላዊ መግለጫ እናዘጋጃለን።

የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችና የአሰራር ቅደም ተከተል

- የውሃ ቀለም፣ ብሩሽ፣ እርሳስ፣ ብዕር፣ ወፍራም ወረቀት፣ ከመፍጸፍት፣ ከተረት እና ከሌሎች መረጃዎች የተገኙ ታሪኮች

የአሰራር ቅደም ተከተል

- በመጀመሪያ ስዕላዊ መግለጫ የሚሰራለትን የታሪክ ክፍል መለየት
- የለየነውን ታሪክ ለስዕል ትረካ እንዲመች አድርጎ በዋና ዋና ክፍሎች መከፋፈል
- የዋና ዋና ክፍሎቹን ታሪክ መሰረት በማድረግ የስዕል ትረካ ንድፍ መንደፍ
- የውሃ ቀለም ወይም ብዕር በመጠቀም ንድፉን ብርሃንና ጥላ እየሰጡ በቅብ ማሳመር
- ከስዕል ትረካው ጎን ታሪኩን በቆንጆ የእጅ ጽሁፍ መጻፍ

የተግባር ስራ

- ተማሪዎች በቡድን በመሆን መምህራችሁ በክፍል ውስጥ በሰጡሩ ከሚነግሯችሁ የኢትዮ ጵያ አርበኞች ታሪክ በመነሳት የኢለስትሬሽን ስራ በእርሳስ እና በውሃ ቀለም በማዘጋጀት ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።
- በአካባቢያችሁ የቀለም ቅብ፣ የቅርጽ፣ የአደባባይ ሀውልት እና ረጅም እድሜ ያላቸው የኪነ ህንጻ ስራዎች ካሉ እነሱን በማስታወስ የሀገራችንን ታሪክ በመተረክና በመግለጽ በኩል ያላቸውን በጎ አስተዋጽኦ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በዝርዝር ተናገሩ።

3.1.2 ፎቶ ግራፍን በመጠቀም የሀገራችንን ታሪክ መግለጽና መተረክ

ፎቶ ግራፍ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ አካባቢ የተጀመረ የእይታዊ ጥበባት ዘርፍ ሲሆን በዋናነት አንድን ነገር በአንድ ቅጽበት ከሁኔታው ጋር አስተሳስሮ መግለጽ የሚችል ነው። በየእለቱ የምንነሳው እንያንዳንዱ ፎቶ ግራፍ ጊዜውንና ሁኔታውን መዝግቦ የማስቀረት ትልቅ አቅም አለው። ይህ አቅም ፎቶ ግራፍን ለታሪካችን መግለጫነት እና መተረኪያነት እንድንጠቀመው ያስችለናል።

ፎቶ ግራፍ እንደ ሌሎቹ የስነ ጥበባት ስራዎች የዘመን ምስክር ማስታወሻ እና ምልክት ይሆናል። የፎቶ ግራፍ ቴክኖሎጂ እያደገ መጥቶ ሁላችን የፎቶ ማንሻ ካሜራ በየእጃችን ይዘን እንድንቀሳቀስ ትልቅ እድል ፈጥሮልናል። ይህ ደግሞ እያንዳንዱን አጋጣሚ ዘግቦ ለመሰነድ እና ለትውልድ ለማኖር ትልቅ ሚና ይኖረዋል። በሀገራችን ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ ፎቶ ግራፍ የታሪክ አሻራዎችን ለትውልድ በማስተላለፍ በኩል ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ከአፄ ምኒልክን የስልክ፣ የመኪና፣ የባቡር፣ የትምህርት ቤት፣ የኪነ ህንጻ፣ የህክምና እና ሌሎች የስልጣኔ ጅማሮዎችን ለትውልዱ በምስል ለማሳየት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። ባለንበት ዘመን ደግሞ የፎቶ ግራፍ ካሜራ በልዩ ልዩ መልኩ መሰራት የተቻለ ሲሆን የሞባይል ካሜራ መምጣት በሁሉም እጅ የካሜራ ተደራሽነት እንዲኖር ያስቻለ እና እያንዳንዷን ሁኔታ በፎቶ ግራፍ ለመዘገብ ትልቅ እድል የፈጠረ ነው።





ስዕል 37 አፄ ምኒሊክ የመጀመሪያዋን መኪና ሲጎበኙ እና ስልክ የሚናገሩ ስው ፎቶ

የተግባር ስራ

✍ ልዩ ልዩ ቆየት ያሉ ፎቶ ግራፎችን በክፍል ውስጥ በማምጣት ከፎቶ ግራፉ የተረዳችሁትን ነገር፣ ፎቶ ግራፉ በተነሳበት ጊዜ እና በአሁኑ አኗኗራችን መካከል ያስተዋላችሁትን ልዩነት ለጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አስረዱ

3.1.3 በቴያትር የሀገራችንን ታሪክ መተረክና መግለፅ

ቴያትር የሀገራችንን ታሪክ፣ መቼቱን፣ እና ገጸ ባህሪያቱን መድረክ ላይ በማቅረብ ለተመልካች በማይረሳ መልኩ ለመተረክና ሁኔታውን ለማብራራት በጣም ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ጥንታዊ ስልጣኔ ከታየባቸው ሀገራት አንዷ ናት። የበርካታ ስልጣኔ ባለቤት ስትሆን ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ እና አስደናቂ ባህል ያላቸው ህዝቦች ሀገር ናት።

በሀገራችን በርካታ የቴያትር ስራዎች ታሪካዊ ሀሳብና ሁኔታን መሰረት አድርገው ተሰርተዋል። ህንደኬ፣ የቴዎድሮስ ራዕይ፣ ጣይቱ፣ የቃቄ ውርደወት እና ሌሎች ታሪካዊ የቴያትር ስራዎች በብሔራዊ ቴያትር ቤት፣ በሀገር ፍቅር ቴያትር ቤት እና በሌሎች የቴያትር ማሳያ ስፍራዎች ለተመልካች ቀርበዋል።

የተግባር ስራ

✍ ቤተ መጽሐፍት በመሄድ ከሀገራችን ታላላቅ ተውኔቶች መካከል የአንድ አፍታ ትዕይንት መርጣችሁ የሚያስቃኙትን ታሪክና ዘመን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ

3.2 የሀገራችንን ታሪክ በሙዚቃ መተረክ

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1.በሙዚቃ አማካኝነት ምን ምን ነገሮችን ተምራችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቁትን ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ሙዚቃ ሰዎች ፍልስፍናቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ከሚኖሩበት መልከዓምድራዊ አቀማመጥ፣ ሀይማኖታዊና ባህላዊ ዕሳቤዎች፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ጀግንነትና የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ተመስርተው የሚፈጥሩት ማህበረሰባዊ ሀብት ነው። ሙዚቃ የሀገር ዳር ድንበር እንዲከበር፣ ታሪክ የሰሩ ጀግኖች እንዲታወሱ፣ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። አገራችን ኢትዮጵያ በፋሽሽት ጣሊያን ተወራ በነበረበት ወቅት በድል እንድታጠናቅቅ ሙዚቃ የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል።

ሙዚቃ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተነቃንቆ ወደ አድዋ እንዲዘምት በመሰንቆ፣ በነጋሪት፣ በእምቢልታ፣ በአታሞ፣ በከበሮ፣ በጥሩንባና የመሳሰሉ ሀገር በቀል የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጠቀም በሆታና በእልልታ፣ በሽለላና ቀረርቶ፣ ተነሳስቶ ከጀግኖች አርበኞች ጎን በመሰለፍ ለሀገሩ ክብር የዘማቹን ስሜት በማነቃቃት፣ ጀግኖችን በማወደስና፣ የፈሩትን በማትባት ከፍተኛ ሚና ነበረው።

ሀ) የህዝብን ወኔ ለማነሳሳት የተዘፈኑ ዘፈኖች

አጥንቴም ይከስከስ ደሜም ይፍሰስላት
ሀገሬን ጭራሽ አይደፍራትም ጠላት
የሀገሬ ጀግኖች ሴት ወንዱ ታጠቁ
እንግዲህ ለጠላት አንተኛም ንቁ
ጀግንነት እንደሆን ያባቶቻችን ነው
ህብረታችን ፀንቷል ድል መንሳት የኛ ነው
ስለዚህ አንራራም ግድ የለንም እኛ
ታጥቀን ተነስተናል ሌሊት እንዳንተኛ
አክትሟል አበቃ የናንት ምዕራፋችሁ
የማይሆን ቅዠት ነው ከንቱ ነው ህልማችሁ
ስትቅበዘበዙ አልፋችሁ ከልኩ
ባንድነት ብለናል ሀገሬን አትንኩ (አጥንቴም ይከስከስ ጥላሁን ገሰሰ)

ለ) አድዋ

"የተሰጠኝ ህይወት ዛሬ በነፃነት፣
ሰው ተከፍሎበታል፣ ከደምና ከአጥንት
ስንት ወገን ወደቀ በነፃነት ምድር
ትናገር አድዋ፣ ትናገር አ-ገ-ሬ
እንዴት እንደቆምኩኝ ከፊታችሁ ዛሬ...

የጥቁር ድል አምባ አድዋ- አፍሪካ እምዬ ኢትዮጵያ...!! (በእጅጋየሁ ሽባባው የተዘፈነ ዘፈን)

3.2.1 በፉከራና ቀረርቶ ታሪክን መተረክ

ሽለላ /ቀረርቶ/፦ ከጀግንነት ጋር የሚያያዝ ድምፅን ከፍ በማድረግ በወኔና በቁጭት መልክ ብቻውንና ከፉከራ ጋር የሚዜም በሚዜምበት ጊዜም ግጥሙን ለማሰላሰል ፋታ የሚሰጥ እና ግጥሞቹ ረዘም ባሉ ስንኞች የሚዋቀሩለት ዜማ ነው።

ፉከራ፦ ከቀረርቶ በፈጠነ እና ጥድፊያ በተሞላበት የአዜያዚያም ስልት የሚቀርብ ሲሆን ግጥሞቹም ከቀረርቶ አንጻር ሲወዳደሩ በአጫጭር ስንኞች የተዋቀሩ ናቸው። ሽላዮች ጀግኖች አርበኞች በጦር ሜዳ ላይ የፈፀሙትን ታላቅ ጀብድ እያነሱ በሚያምር ድምፅና ቅላፄ ሲያሞካሹ ፎካሪዎች ደግሞ ጋሻቸውን አንግበው፣ ጎራዴያቸውን ጨረቃ አስመስለው ጦር እየሰበቁ፣ ቁጭ ብድግ እያሉ ቃታ እየፈለቀቁ፣ ወዲያ ወዲህ እየተንጎራደዱ፣ ነጋሪት እያስጎሰሙ፣ ጥሩንባና መለከት እያስነፉ፣ በእልልታና ጭብጨባ እንዲያ በል እያስባለ የጀግኖችን ታሪክ የሚተርክ ነው። ሽለላና ቀረርቶ በኢትዮጵያዊያን ልብ ከፍ ያለ ቦታ ያለው ማህበረሰባዊ ጥበብ ነው። ከዚህ ቀጥሎ የምትመለከቷቸው ፉከራና ቀረርቶዎች ተምሳሌት የሆኑ የሀገር መሪዎችንና ጀግኖች አባት አርበኞችን እያነሱ ደፋርነትን፣ ቆራጥነትን፣ ልበ ሙሉነትን በኢትዮጵያዊያን ልብ ቀርፀውና አትመው ያቆዩ ናቸው።

በፉከራ ታሪክን መናገር

ለአፄ ቴዎድሮስ የተፎከሩ ፉከራዎች

መቼ ሞተና መቼ ተነሳ፣
መቅደላ ያለው የቋራው ካሳ፣
እንግዲህ እኔ ሌላ አላነሳ፣
ከፈረስ ታጠቅ ከጎበዝ ካሳ፣
የቋራው ካሳ ልበልህ እንዴ፣
የለህም ዘመድ ካለ ጎራዴ።



ስዕል 38 አጼ ቴዎድሮ

ስለ አባት አርበኛ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ በሽለላ (በቀረርቶ)

ፊረንጅ ምድር ለቆ ቢሄድ በሰማይ፣
የጎጃሙ አንበሳ ዳመናው ና ቶሎ ዘለቀ በላይ፣
ጣሊያን ፍየል ሆኖ ቅጠል ቅጠል ሲያይ፣
የለምጫኑ አንበሳ ነብር ተመስሎ አረደው በላይ፣
የጎጃሙ ነብር የለምጫኑ አንበሳ፣
አባ ኮስትር በሌ እንደምን ይረሳ፣
ኧረ እንዴት ያለነው የኮስትር ጥይት፣
ግንባር ይባርካል እንደነብስ አባት።



ስዕል 39 አርበኛ በላይ ዘለቀ

ስለ አባት አርበኛ ሌተናል ጀኔራል ኃይሉ ከበደ

በቀረርቶ

አባ መረብ ኃይሌ ኃይሌ አባ ይባስ
አንገቱን የሰጠው እንደ ዮሐንስ
ወለህ ከሚዳው ላይ ገብቶ ሲቀድስ
ቄሱ ታፈረ ነው ዲያቆኑ ሞገስ
አጨደው ከመረው ወቃው እንደ ገብስ።



በፉከራ

ውረድ እንውረድ ውረድ ካለቱ፣
ሰቆጣ በታች ከቁልቁለቱ
ኃይሉ ከበደ ካደሩበቱ፣
የሞተ ይሙት ታልቅስ እናቱ።

ስዕል 40 አርበኛ ሌ/ጀነራል ኃይሉ ከበደ

3.2.2 በባህላዊ እስክስታዎች ታሪክን መተረክ

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች እስክስታ ምንድን ነው? በየትኛው የሰውነት ክፍላችሁ ነው እስክስ የምትሉት?
2. በክፍሉ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ተመሳሳይ እስክስታዎችን የሚመቱ ይመስላኃል?

አገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ በመሆኗ በርካታ ባህሎች አሏት። እነዚህ ባህሎች በሙዚቃ አማካኝነት ይገለፃሉ፣ ይተረካሉ ይተዋወቃሉ። በአገራችን በስፋት ከሚታወቁ ባህሎች ውስጥ የዘመን መለወጫ በዓል፣ የመስቀል በዓል፣ የጥምቀት በዓል፣ የመውሊድ በዓል፣ የአረፋ በዓል፣ የሰርግ፣ የዕርሻ፣ ስራ፣ የለቅሶ ስነ-ስርዓት፣ የሚገኙ ሲሆን በተጨማሪም በርካታ የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የአዘፋፈን ባህልና ስርዓቶች አሉ።

ባህላዊ እስክስታ በተለያዩ አልባሳት ተውቦና አጊጦ ሙዚቃ በፈጠረው ስሜት ተነሳስተን ውስጣዊ ስሜታችን በሰውነት እንቅስቃሴ የምንገልፅበት የባህል አንዱ አካል ነው። በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚኖሩ ሰዎች የተለያዩ የእስክስታ አይነቶችን ይጠቀማሉ። እስክስታዎቹም ከቦታ ቦታ ይለየያሉ። አከዋወኑም ሁለትና ከዚያ በላይ በመሆን የሰዎችን አለባበስ፣ አመጋገብ፣ ፍልስፍና እና ሌሎች ታሪኮችን የሚተርኩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ናቸው።

መልመጃ 3.1

1. በአማራ ክልል ሚዘፈኑ ባህላዊ ሙዚቃዎች አንድ ሙዚቃ ምረጡና በቡድን በቡድን በመሆን ተለማመዱ። ከተለማመዳችሁ በኋላም አልባሳትና ቁሳቁሶችን አሟልታችሁ አቅርቡ። ያቀረባችሁት እስክስታ ስለ ምን የሚተርክ እንደሆነ በአካባቢያችሁ ያሉ ሰዎችን በመጠየቅ መልሱን ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. በወሎ፣ በሸዋና በጎጃም፣ በጎንደር፣ በዋግ ኽምራ፣ እና በኦሮሚያ ልዩ ዞን አካባቢዎች የሚዘወተሩ እስክስታዎችን በቡድን አጥንታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ። አጨዋወታቸውም ከምን ጋር የተገናኘ ታሪክ እንዳላቸው ለጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው።

1. በአማራ ክልል የሚዘወተሩ ባህላዊ እስክስታዎች (ውዝዋዜዎች)

በአማራ ክልል የሚገኙ ባህላዊ እስክስታዎች (ውዝዋዜዎች) በአብዛኛው ከወገብ በላይ ያለን የሰውነት ክፍልና ትከሻን በማወዛወዝ እጅን ከወገብ ላይ በመያዝ፣ እጅን ወደ ታች ለቆ ትንሽ ከፊት በማድረግ ሰውነታቸውን ወደ ፊትና ወደ ኋላ በማድረግ፣ አንገትን ወደ ፊትና ወደ ኋላ በማወዛወዝ፣ አንገትና ትከሻን በማቀናጀት የሚከወኑ ናቸው። በተጨማሪም ወገብና ዳሌን በማሽከርከር፣ እንዲሁም መላ ሰውነትን በማንቀጥቀጥ፣ አንገትን ብቻ በማሽከርከር ሁለትና ከዛ በላይ በመሆን በየ ተራ የሚከወን ሲሆን አልፎ አልፎ የጎጃሙ ምስራቅ ክፍል፣ ወሎ፣ ኦሮሞ ብሔረሰብና ሰሜን ሸዋ በከፊል ደግሞ ክብ በመስራት በርከት ያሉ ሰዎችን በአንድ ጊዜ የሚያሳትፍ የእስክስታ (የውዝዋዜ) አይነት ይጠቀማሉ።






ስልዕ 41 የአማራ ክልል ባህላዊ እስክስታ በከፊል

2. የደቡብ የኢትዮጵያ ባህላዊ እስክስታ፦ የደቡብ ኢትዮጵያ ባህላዊ እስክስታ (ውዝዋዜ) ከቦታ ቦታ የተለያየ ቢሆንም ልዩ ልዩ የባህል ቁሳቁሶችን በተለይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን በመያዝ ዳሌና ወገብን በማወዛወዝና ወደ ላይ በእግራቸው በመዝለል እስክስ ይላሉ። ከዚህ በታች የምታዩት እስክስታ የራሱ የሆነ ታሪካዊ ዳራ አለው።





ስዕል 42 ከደቡብ ክልል ባህላዊ እስክስታዎች በከፊል

መልመጃ 3.2

ሀ) በደቡብ የኢትዮጵያ የሚገኘው የወላይታ ባህላዊ እስክስታ (ውዝዋዜ) ከየትኛው የአማራ ክልል ባህላዊ እስክስታ ጋር ይመሳሰላል? የአጨዋወት ስልቱ የሚነግረን ታሪክ ምንድን ነው?

ለ) እስክስታውን በቡድን በቡድን ሆናችሁ ተለማመዱና የተመሳሰለበትን ክፍል ለይታችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

3. የትግራይ ክልል እስክስታ፦ በሰሜኑ ክፍል ከሚገኙ የእስክስታ አይነቶች አንዱ ደግሞ የትግራይ ባህላዊ እስክስታ ነው። የትግራይ ባህላዊ እስክስታ ክብ ሰርቶ በመሽከርከር አንገትን ከትከሻ ጋር በማቀናጀት የሚከወን ነው።

4. የኦሮሚያ ክልል ባህላዊ እስክስታ፦ የኦሮሚያ ክልል ባህላዊ እስክስታ ከአካባቢ አካባቢ የተለያየ አጠቃቀም አለው። ከሚጫወቷቸው እስክስታዎችም ፎሌና ረገዳ የሚባሉ እስክስታዎች ይገኛሉ። ሴቶቹም ሆነ ወንዶቹ ክብ ሰርተው ወገብ ለወገብ ተያይዘው ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተንቀሳቀሱ እስክስ ይላሉ። ወንዶቹ ከመሬት ወደ ላይ እየዘለሉ፣ በርከት ያሉ ሰዎችን በአንድ ጊዜ በማሳተፍ የሚከወን ነው።



ስዕል 43 ከኦሮሚያ ባህላዊ እስክስታዎች በከፊል

መልመጃ 3.3

1. የኦሮሚያ ክልልን ባህላዊ የሴቶችና የወንዶች እስክስታ በቡድን ተለማምዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማሳየት የእስክስታውን መልዕክት ተናገሩ።

5. ባህላዊ የሴቶች ጨዋታዎች

ሻደይ፣ አሸንድየ፣ ሶለልና እንግጫ ነቀላ

ሻደይ በዋግ ኽምራ፣ አሸንድየ በላስታ ላሊበላ፣ ሶለል በወሎ ራያ ቆቦና እንግጫ ነቀላ በጎጃም በአማራ ክልል ከሚገኑ በርካታ ባህላዊ የሴቶች ጨዋታዎች ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ጨዋታዎች ከነሀሴ 16 ጀምሮ እናቶች ልጃገረዶችና ሴት ህጻናት ብቻ የሚጫወቷቸው ጨዋታዎች ናቸው። ነዚህ ባህላዊ ጨዋታዎች በክልላችን በዚህ መልኩ መከወናቸው ዓለም የሴቶችን መብት በሚገባ ባላስከበረበት ወቅት አገራችን የሴቶች መብት አስከብራ የቆየች ስለ መሆኗ ማሳያዎች ናቸው።





ስዕል 44 አሸንድየ በላስታ ላሊበላ ስዕል 45 ሻደይ በዋግ ኽምራ



ስዕል 46 ሶለል በወሎ ራያ ቆቦ



ስዕል 47 እንግጫ ነቀላ በጎጃም

6. ነፍጀሌ (ተበችሳ)

ነፍጀሌ ወይም ተበችሳ በሰሜን ወሎ፣ በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋ በተወሰኑ አካባቢዎች በኦሮሞ ብሔረሰብ፣ ሰርግ ሊደርስ አስራ አምስት ቀን ሲቀረው በወንዶችና በሴቶች የሚከወን ባህላዊ ጨዋታ ነው። አጨዋወቱ በአካባቢው ማህበረሰብ ከጋብቻ ጋር የተያያዙ ታሪኮችን ይነግረናል።



ስዕል 48 ተበችሳ ወይም ነፍጀሌ

መልመጃ 3.4

1. ተማሪዎች ሻደይን፣ አሸንድየን፣ ሶለልንና እንግጫ ነቀላን ሴቶች ብቻ በቡድን ተከፋፍላችሁ ዜማውንና ግጥሙን በመጠየቅ አጥንታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ቅርቡ።
2. የነፍጀሌን ባህላዊ ጨዋታዎች ወንዶችና ሴቶች በጋራ በመሆን ግጥምና ዜማውን ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ። ታሪኩም ከምን ጋር የተገናኘ እንደሆነ በፅሁፍ አቅርቡ።

3.2.3 በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ታሪክን መተረክ

በአገራችን ኢትዮጵያ በርካታ የሙዚቃ መሳሪያዎች አሉ። ከነዚህም ውስጥ መሰንቆ፣ ክራር፣ ዋሽንት፣ ነጋሪት፣ አታሞ፣ ጥሩንባ፣ ደወል፣ ድቤ፣ ከበሮ፣ ከራቤ፣ መለከት፣ እምቢልታ ሌሎችም ይገኛሉ። እነዚህ የሙዚቃ መሳሪያዎች በአሰራራቸውም ይሁን በአጨዋወታቸው የየራሳቸው የሆነ ታሪክ ያስተላልፋሉ።

ሀ ነጋሪት

ነጋሪት ከምት የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚመደብ ሲሆን በመጠኑ በጣም ትልቅ የሙዚቃ መሳሪያ ነው። ነጋሪት በጦርነት ጊዜ ተዋጊውን ሠራዊት በማጀብና ሰልፈኛውን በማድመቅ፣ ነገሥታቱ ግብር በሚያስገቡበት ጊዜ የተገኘውን ህዝብ ለማዝናኛነትም ያገለግል ነበር። በንጉሱ ዘመን ደግሞ ነጎድጓዶች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ለማጀቢያነት አዋጅ ለመንገር ህዝብን ለመሰብሰብም

ተጠቅመውበታል።



ስዕል 49 የነጋሪት አጎሳሰም

ለ ዋሽንት

ዋሽንት በገጠሩ አካባቢ ዕረኞች እንስሳትን ሲጠብቁ ለእንጉርጉሮ የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን አሁን አሁን ደግሞ በአገራችን ባህላዊ የሙዚቃ ቡድኖች መበራከት በጓላ ለመድረክና ክሊፖች ማጀቢያነት በስፋት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። ተማሪዎች በስዕሉ ከምታዩት የዕረኞች አለባበስና አጨዋወት ምንን ትማራላችሁ?





ስዕል 50 የደጋ እረኞች ዋሽንት አጨዋወት ስዕል 51 የቆላ እረኞች ዋሽንት አጨዋወት

ሐ) መሰንቆ

መሰንቆ በኢትዮጵያ ጥንታዊ ከሚባሉ የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱ ነው። መሰንቆ በድሮ ጊዜ በቤተመንግሥት መኳንንትን ለማስደሰት፣ በጦርነት ጊዜ ወታደሩን ለማነቃቃትና ህዝብን ለመቀስቀስ ይጠቀሙበት ነበር። መሰንቆና መሰንቆ ተጫዋቾች በአማራ ክልል በርካታ አካባቢዎች በስፋት ይገኛሉ። መሰንቆ በልዩ ልዩ ዓለማዊና መንፈሳዊ ክብረ በዓላት ሰዎች ተሰብስበው ደስታቸውንና ሀዘናቸውን የሚገልፁበት በኢትዮጵያ ጥንታዊ ተብለው ከሚመደቡ የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎች መካከል አንዱ ነው።

መ ከበሮ

ከበሮ በዋናነት ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውል ሲሆን በአንዳንድ አካባቢዎች መጠኑን በማሳነስ ለአለማዊ ሙዚቃ ማጀቢያነት ይጠቀሙበታል።



ስዕል 52 የከበሮ አመታት

የምዕራፉ ማጠቃለያ

☑ የእይታዊ ጥበባት ዘርፎች የሰው ልጅ ፈጠራና እውቀት መገለጫዎች ናቸው። ይህ ደግሞ በየዘመናቱ የነበሩትን የማህበረሰብ ክፍሎች የእወቀትና የፈጠራ ደረጃ የሚናገሩ ታሪካዊ አሻራዎች ያደርጋቸዋል። ለምሳሌ የጎንደር ቤተ መንግስትን ወይም የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናትን ስንመለከት የአባቶቻችንን ታሪክ እንረዳለን። እነዚህ ስነ ጥበባዊ ስራዎች በዘመኑ የነበረውን ማህበረሰብ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሀይማኖታዊ ሁኔታ የመናገር አቅም አላቸው።

☑ በሌላ መንገድ ደግሞ ታሪክን በልዩ ልዩ መንገድ መዘገብ የሚቻል ሲሆን ከእይታዊ ጥበባት ስራዎች መካከል አንዱ የሆነው የስዕላዊ መግለጫ አሰራር ታሪክን በስዕል ለመተረክ የሚያስችለን ጥበባዊ አሰራር ነው። ስዕሎችን በቅደም ተከተል በመሳል ታሪካዊ ትረካውን በስዕል መግለጥ ይቻላል።

☑ ፎቶ ግራፍ ታሪክን የመተረክ ትልቅ አቅም አለው። ይሄውም ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን በፎቶ በማነሳት ለመጭው ትውልድ ማቆየት የሚቻል ሲሆን በዘመኑ የነበረውን ማህበረሰባዊ ለውጥና እድገት በማስረጃነት በማኖር ፎቶ ግራፍ ያለፈውን ሁኔታ ለመተረክ ያስችለናል።

☑ ቴያትር በመድረክ ላይ የሚቀርብ ተውኔት እንደመሆኑ ልዩ ልዩ ታሪካዊ ሁኔታዎችን መሰረት አድርጎ ይተወናል። ተዋንያኑም ሆኑ የመድረክ አዘጋጆቹ በትያትሩ ታሪክ የተቀመጠውን ዋና ሀሳብ ለተመልካች ለማድረስ ዘመኑን የሚያስታውስ አልባሳት፣ የገጸ ባህሪያቱ ንግግር እና አጠቃላይ መቼቱ ታሪኩን እንዲወክል ሆኖ ይቀርባል። በአጠቃላይ በእይታዊ ጥበባት እና በክውን ጥበባት የሀገራችንን ታሪክ መተረክ እንችላልን።

☑ ሙዚቃ ክውን ጥበባት በመባል ከሚታወቁት የሙያ ዘርፎች አንዱ ነው። የአንድ ማህበረሰብ ታሪክ፣ ጀብድ፣ ባህል እና ወግ ከሚተላለፍባቸውና ከሚተረክባቸው ስልቶች አንዱ ነው። በዚህ ምዕራፍ በቀረርቶ እና ፉከራ ታሪክን እንዴት ማስተላለፍ እንደሚቻል ተምራችኋል። በአገራችን እጅግ በርካታ የእስክስታ ወይም የጭፈራ አይነቶች ይገኛሉ። እነዚህ እስክስታዎች እንደየ ህዝቡ አኗኗር፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ይዘት ተላብሰው የባህላዊ ጨዋታውን ታሪካዊ አመጣጥ ይተርካሉ።

☑ የሀገራችንም ሆነ የክልላችን የእስክስታ አይነቶች የየማህበረሰቡን ባህል፣ እሴት፣ እንዲሁም ልማድና ወግ ምን እንደሚመስል ይነግሩናል። በአጠቃላይ ሙዚቃ የአንድን አገር ባህል፣ ታሪክ፣ እውቀት፣ አለባበስ ምን እንደሚመስል እንደ ጋዜጠኛ የሚተርክ የክውን ጥበባት ዘርፍ ነው።

የምዘና ጥያቄ አንድ

ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የቀረቡትን ጥያቄዎች በ✓ምልክት በማድረግ ራሳችሁን መዝኑ።

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	እይታዊ ጥበባት የሀገራችንን ታሪክ ለመግለጽና ለመተረክ እንደሚያስችሉን ማወቅ ችያለሁ		
2	በቴያትር የሀገራችንን ታሪክ መተረክ እንደሚቻል ተገንዝቤያለሁ		
3	በፊልም ጥበብ የሀገራችንን ታሪክ መተረክ እንደሚቻል ተረድቻለሁ		
4	በፎቶ ግራፍ ስራ የሀገራችንን ታሪክ መግለጽ ችያለሁ		

የምዘና ጥያቄ ሁለት

ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የቀረቡትን ጥያቄዎች በ ✓ ምልክት በማድረግ ራሳችሁን መዝኑ።

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	ሙዚቃ ታሪክን ከምንነግርባቸው መንገዶች አንዱ እንደሆነ ተገንዝቢያለሁ		
2	በቀረርቶና በፉከራ አማካኝነት ጀግኖች አባቶችና እናቶች በአድዋ ላይ የፈፀሙትን ጀብድ ተገንዝቢያለሁ		
3	ፉከራና ቀረርቶ ከጀግንነት ጋር የተገናኘ ታሪክ እንዳላቸው አውቂያለሁ		
4	ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አንድ ሀገር የራሷ የሆነ የሙዚቃ ጥበብና ታሪክ እንዳላት ማስተማሪያ ጥበብ እንደሆነ አውቂያለሁ		
5	ከአገራችን ታሪክ ጋር የተያያዙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዳሉ ተገንዝቢያለሁ		
6	በአማራ ክልል የተለያዩ የእስክስታ አይነቶች እንዳሉ እና ካሉት የእስክስታ አይነቶች ውስጥ የተወሰኑትን መጫወት ችያለሁ		
7	በደቡብ ክልል የእስክስታ አጨዋወት የተለያዩ የእንስሳት ቆዳዎችን እና ቀንዶችን በመያዝ ወይም በመልበስ እንደሚጫወቱ ተገንዝቢያለሁ		
8	በአገራችን የሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የራሳቸው አሰራር፣ አጨዋወትና ታሪክ እንደሚያስተላልፉ ተረድቻለሁ		
9	ከበሮ ለዝማሬ ቀሳውስት የሚያገለግል የሙዚቃ መሳሪያ መሆኑን ተረድቻለሁ		
10	ሻደይ፣ አሸንድየ፣ ሶለልና እንግጫ ነቀላ በአማራ ክልል የሚገኙ ባህላዊ የሴቶች ጨዋታዎች እንደሆኑ ተረድቻለሁ		

የማጠቃለያ መልመጃዎች

ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ በማንበብ ትክክል የሆኑትን እውነት ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ሙዚቃ እንደ ድርሰት በአንድ ወቅት የተፈፀመን ታሪክ የሚናገር በእስካስታና ከስክስታ ውጭ የሚከወን ማህበረሰባዊ ሃብት ነው።

2. እስክስታ (ውዝዋዜ) ከቦታ ቦታ ይለያይ እንጂ ሰዎች ውስጣዊ ስሜታቸውን በአካላዊ እንቅስቃሴ የሚገልፁበት የባህል አንድ አካል ነው።

3. ባህላዊ ሙዚቃ ሊወራረስና ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊለዋወጥ የማይችል የጥንት ሰዎችን ጥበብና አስተሳሰብ የሚያሳይ ነው።

4. ሁሉም ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ለተመሳሳይ አገልግሎት ይውላሉ።

5. ስለ አባይ የተዘፈኑ ሙዚቃዎች የአሁኑ ዘመን ትውልድ የፈጠራቸው ወደ ፊት የታሪክ አንድ አካል የሚሆኑ ናቸው።

6. እይታዊ ጥበባት የሀገራችንን ታሪክ ለመተረክ እና ለመግለጽ ያስችሉናል

7. የቀለም ቅብ ስራዎች የሀገራችንን ታሪክ ለመተረክና ለመግለጽ አያስችሉንም

8. ቴያትር ተመልካችን ለማዝናናት እና ለማስተማር የሚሰራ ስለሆነ የሀገራችንን ታሪክ ለመተረክ አይጠቅመንም

9. የፊልም ጥበብ የሀገራችንን ታሪክ ለመተረክና ለመግለጽ ልንጠቀምበት እንችላለን

10. የፎቶ ግራፍ ስራ ታሪክን መዘገብና መግለጽ አይችልም

ለ) ከዚህ ቀጥሎ በመርጫ የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል መርጣችሁ አክብቡ።

11. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ታሪክ ነጋሪ የሆነው የሙዚቃ መሳሪያ የቱ ነው።

ሀ) አታሞ ለ) መሰንቆ ሐ) ዋሽንት መ) ሁሉም

12. መሰንቆን፣ ጥሩንባንና፣ አታሞን አካተን የማንጠቀመው በየትኛው የበዓል አይነት ነው?

ሀ) በሰርግ ለ) በጥምቀት ሐ) በመውሊድ በዓል መ) ሀ እና ለ

13. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የሙዚቃ ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ማዝናናት ለ) ታሪክን መንገር
ሐ) ቅርሶችን መጠበቅ መ) ሁሉም

14. ከሚከተሉት ውስጥ በስፋት ዳሌን በማወዛወዝ እስክስ የማይሉት የትኞቹ አካባቢዎች ናቸው?

ሀ) አዊ ለ) ወላይታ ሐ) ጎንደር መ) ሁሉም

15. ጀግኖች አርበኞች በጦር ሜዳ የፈፀሙትን ጀብድ ከአጫጭር ግጥሞች ጋር አዋህዶ የሚተርክ የሙዚቃ አይነት የቱ ነው?

ሀ) ቀረርቶ ለ) ፉከራ ሐ) ሆታና ጭፈራ መ) ሁሉም

ሐ) ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ፃፉ።

16. በአካባቢያችሁ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ሁለት ምረጡና ምን ምን ታሪክ እንደሚያስተላልፉ ትልልቅ ሰዎችን በመጠየቅ ፅፋችሁ አቅርቡ።

17. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ስለ ጀግንነት የተፃፉ የፉከራና ቀረርቶ ግጥሞችን በማጥናት እየሸለላችሁ እና እየፎከራችሁ ለትምህርት ቤታችሁ ማህበረሰብ አቅርቡ።

18. በአካባቢያችሁ የምታገኟቸውን ቆየት ያሉ ፎቶ ግራፎች በማሰባሰብ የሚያስተላልፉትን ታሪካዊ ሁኔታ ለጓደኞቻችሁ አብራሩላቸው

19. ከዚህ በፊት የተመለከታችሁትን ታሪካዊ የቴያትር ስራ በማስታወስ ለጓደኞቻችሁ የታሪኩን ጭብጥ ዘግቡላቸው

20. ከዚህ በፊት በሀገራችን ከተሰሩ ታሪካዊ የፊልም ስራዎች መካከል የምታስታውሱትን ፊልም በመምረጥ ፊልሙ የሚያሳየውን ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው

ምዕራፍ 4

ሀገር በቀል እውቀቶችን ማድነቅ

የምዕራፉ ዓላማዎች፡

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- እይታዊ ጥበባትን በመጠቀም የሀገር በቀል እውቀቶቻችንን ማድነቅ ትችላላችሁ፤
- ንድፍ በመስራት ሀገር በቀል የስነ ጥበባት ሥራዎችን ማድነቅ ትችላላችሁ፤
- የወረቀት ሞዛይክ በመስራት ሀገር በቀል ስነ ጥበባዊ ሥራዎችን ማድነቅ ትችላላችሁ፤
- የቴያትር ጥበብን በመጠቀም ሀገር በቀል እውቀቶችን መግለጽ ትችላላችሁ፤
- የፊልምና የፎቶ ግራፍ ጥበብን በመጠቀም ሀገር በቀል እውቀቶችን ታደንቃላችሁ፤
- አገር በቀል ውቀቶችን የሚያደንቁና ለመማር የሚያነሳሱ የመዝሙር ዜማዎችንና ግጥሞችን ትደርሳላችሁ፣ መዘመር ትችላላችሁ፡
- አገር በቀል አውቀቶችን በእስክስታ ማድነቅ እንደሚቻል ትረዳላችሁ።
- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የአገር በቀል እውቀት ውጤቶች እንደሆኑ ታውቃላችሁ።

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ያሉ የእደ ጥበብ ስራዎች የሀገር በቀል እውቀት አካል ናቸው ብላችሁ ትገምታላችሁ? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ
2. የሀገር በቀል እውቀቶቻችንን ማድነቅ እና መግለጽ የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ይመስሏችኋል? ለመምህራችሁ ተናገሩ
3. ከዚህ በፊት በሀገራችን ከተሰሩ ጥንታዊ የስነ ጥበብ ስራዎች መካከል በስዕል ሰርታችሁ የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ መናገር ትችላላችሁ? ለምንድነው እነሱን መርጣችሁ ስዕል መሳል የፈለጋችሁት?

4.1 ሀገር በቀል እውቀቶቻችን በእይታዊ ጥበባት ማድነቅ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የስልጣኔ ታሪክ ባለቤት ናት። ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ የተሰሩ የተለያዩ ስርዎ መንግስታት የኪነ ህንጻ፣ የኪነ ጽህፈት፣ የጌጣጌጥ፣ የሸክላ እና የቅርጽ ስራዎች በሀገራችን ይገኛሉ። የዋሻ ውስጥ ስዕሎች፣ ህንጻ ፍርስራሾች፣ ኪነ ህንጻ እና ሀውልቶች፣ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት፣ የጎንደር አብያተ መንግስታት፣ የጀጎል ግንብ፣ የጢያ ትክል ድንጋዮች፣ እና ሌሎች የስልጣኔ አሻራዎች በስፋት ይገኛሉ። ትውፊታዊ የሆነው የቤተ ክርስቲያን ስዕሎች አሳሳል ስልት ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ለትውልድ እየተላለፈ ዛሬ ድረስ የቆየ ሲሆን የተጌጡ መጽሐፍት፣ የሀረግ ስራ፣ የግድግዳ ስዕሎች፣ የእንጨት ላይ ቀለም ቅብ ስራዎች እና የኪነ ጽህፈት ስራዎች በዋናነት የሚጠቀሱ የሀገር በቀል ጥበባዊ እውቀቶቻችን ማሳያዎች ናቸው። በተጨማሪም ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዝሃ ባህል፣ ቋንቋ፣ እና ሀይማኖት መገኛ ሀገር ናት።

እነዚህ የስልጣኔ አሻራዎች የሀገራችን የሀገር በቀል እውቀት ውጤቶች እና ማሳያዎች ናቸው። ልንጠብቃቸው፣ ልንከባከባቸው፣ ልናደንቃቸው እና የወደፊት የፈጠራ ስራዎቻችን መነሻ አድርገን ልንጠቀምባቸው ይገባል።

4.1.1 ሀገር በቀል የስነ ጥበብ ስራዎችን በንድፍ መግለጽ

በምዕራፍ አንድ ላይ የማራችኋቸውን የንድፍ አሰራር ዘዴዎች በመጠቀም የሀገራችንን ስነ ጥበባዊ ስራዎች በመንደፍ ለመምህራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ በማሳየት አድናቆታችሁን ትገልጻላችሁ።

ለአሰራር የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች

- ወፍራም እና ስስ የንድፍ ወረቀት፣
- እርሳስ፣ ላጲስ፣
- የስዕል ማስደገፊያ ሰሌዳ
- የእርሳስ መቅረጫ ወይም መቁረጫ

የአሰራር ቅደም ተከተል

- መስራት የፈለግነውን ነገር በስዕል ወረቀት ላይ በማስተዋል መንደፍ
- ብርሃንና ጥላቸውን በሚገባ በመለየት በእርሳስ መቀባት
- የነገሮቹን የሸካራነትና የልስላሴ ደረጃ (ቴክስቸር) በእርሳስ ቅብ በሚገባ ማሳየት

የተግባር ስራ

- ላልይበላ ከሰራቸው ውቅር አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱን በመምረጥ በወፍራም ወረቀት ላይ ስዕል ሰርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አሳዩ።
- በቡድን በመሆን የሀገራችን ታሪካዊ የስነ ጥበብ ስራዎች መካከል አንዱን መርጣችሁ በመስራት በመማሪያ ክፍላችሁ ግድግዳ ላይ በመስቀል አባቶቻችን እንዴት እንደሰሩት እና እንዴት እንዳቆዩት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለጻ እና ማብራሪያ አድርጉላቸው።

4.1.2 ሀገር በቀል የስነ ጥበባት ስራዎችን በወረቀት ሞዛይክ መግለጽ

ሞዛይክ ጥንታዊ ከሚባሉት የእይታዊ ጥበባት አሰራሮች አንዱ ነው። በዋናነት የቤተ መቅደስና የቤተ መንግስት ወለልና ግድግዳዎችን ለማሳመር፣ ለማስጌጥ ባለቀለም ድንጋዮችን እና የሸክላ ስብርባሪዎችን አጠቃግቶ በመለጠፍ ይጠቀሙበት ነበር። ይህ ልምድ ዛሬም ድረስ ሞዛይክን በኪነ ህንጻ ስራ ላይ ተወዳጅ እና የተለመደ የዲዛይን አካል አድርጎታል። ሞዛይክ የተለያየ ቀለም ያላቸው ድንጋዮችን፣ የሸክላ ስብርባሪዎችን እና የመስታወት ቁራጮችን በመለጠፍ ስዕል የመስራት ሂደት ነው። የወረቀት ሞዛይክ ደግሞ በቀላሉ የሚሰራ ሲሆን ልዩ ልዩ ቀለም ያላቸውን ወፍራም ወረቀቶች በማሰባሰብ

እና በመለጠፍ ስዕል የመስራት ሂደት ነው። ወረቀት ቀላል እና ምቹ ሲሆን በቀላሉ በአካባቢያችን ማግኘት እንችላለን። ለማጣበቂያነት ደግሞ ሙጫ፣ ኮላ፣ እና ቅንጭብት በመጠቀም መስራት እንችላለን። ይህን ዘዴ በመጠቀም የሀገራችንን የስነ ጥበብ ስራዎች በወረቀት ሞዛይክ በመስራት አድናቆታችንን እንገልጻለን።



ስዕል 53 ለምሳሌ የቀረበ የወረቀት ሞዛይክ ስራ

የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች

- ወፍራም ወረቀት፣ ካርቶን፣ የወረቀት ማጣበቂያ ሙጫ እርሳስ፣ መቀስ፣ መቅረጫ፣ ላጲስ

የአሰራር ቅደም ተከተል

- መስራት የምንፈልገውን ነገር በወፍራም ወረቀት ወይም ካርቶን ላይ መንደፍ
- ባለ ቀለም ወረቀቶችን በትንንሽ መጠን በመቀስ መቆራረጥ
- ንድፉን ማጣበቂያ በመቀባት ሳይደርቅ ወረቀቶቹን እንደ ተስማሚነታቸው መለጠፍ

የተግባር ስራ

- የጀኅልን ግንብ በወረቀት ሞዛይክ ሰርታችሁ ለመምራችሁ እና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።
- በቡድን በመሆን የጎንደርን ቤተ መንግስት በወረቀት ሞዛይክ ሰርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አሳዩ፣ ቀድሞ የተሰሩበትን መንገድ እና አባቶቻቸን እስካሁን ጠብቀው ለኛ ያደረሱበትን መንገድ አብራርታችሁ ተናገሩ።

4.2 ሀገር በቀል እውቀቶችን በቴያትር፣ በፊልምና ፎቶ ግራፍ መግለጽ

ተማሪዎች ሀገራችን ኢትዮጵያ የበርካታ ባህል፣ ቋንቋ፣ እና ታሪክ ባለቤት ናት። ከጥንታዊ የስልጣኔ ታሪካችን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የሀገር በቀል እውቀትን በመጠቀም ለሚያጋጥማቸው ችግር መፍትሄዎችን በማበጀት ማህበራዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እና አስተዳደራዊ ችግሮችን ለመፍታት ይጠቀሙበት ነበር። የኪነ ጽህፈት፣ የሥነ ጽሁፍ፣ የኪነ ህንፃ፣ የእደ ጥበብ ስራ፣ የእርሻ ስራ፣ የህክምና፣ የእጽዋት ጥናት፣ የዘመን አቆጣጠር፣ እና የሥነ ፈለክ እውቀትን በመጠቀም፣ በመጻፍ እና በማስተማር ለትውልድ እንዲተላለፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።





ስዕል 54 በድንጋይ የተሰራ ቤት፣ በቀርቅሀ የተሰራ፣ የኮንሶ ባህላዊ ቤት

ተማሪዎች፣ እነዚህን እውቀቶች በመጠቀም እና ለቀጣዩ ትውልድ በማቆየት በኩል የእኛ ድርሻ ትልቅ መሆን አለበት። ይህን ለማድረግ ደግሞ በቴያትር በፊልም ጥበብ እና በፎቶ ግራፍ አድናቆታችንን ከመግለጽ እንጀምራለን።

ለሀገር በቀል እውቀቶቻቸን ያለንን አድናቆት በቴያትር እና በፊልም እንዴት መግለጽ እንችላለን? ቴያትር እና ፊልም በርካታ ርዕሰ ጉዳዮችን ትኩረት አድርገው ይሰራሉ። የቴያትርም ይሁን የፊልም ድርሰት ባለሙያዎች የሀገር በቀል እውቀቶቻችንን መሰረት አድርገው የቴያትሩን ታሪክ ይጽፋሉ ወይም ይደርሳሉ። በድርሰቱ መሰረት ቴያትሩን በመድረክ ላይ በመጫወት ለታዳምያን ማስተማር እና ማሳየት ይቻላል። አጫጭር እና ረዥም ዘጋፊ ፊልሞችን ስለ ሀገር በቀል እውቀቶቻችን በመስራት ማስተማር እና ማሳየት እንችላለን።

ተማሪዎች በፎቶ ግራፍ የሀገር በቀል እውቀቶቻችንን ማድነቅ የሚቻል ይመስላችኋል? የሞባይል ካሜራችሁን በመጠቀም እንዴት ማድነቅ እና መግለጽ እንደምትችሉ ለመምህራችሁ ተናገሩ። በአካባቢያችን በመዘዋወር የሀገር በቀል እውቀቶቻችንን የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ፎቶ ግራፎች በማንሳት ለክፍል ጓደኞቻችን እና ለወላጆቻችን የፎቶ ግራፍ ኢግዚቢሽን ማሳየት እንችላለን። በሌላ መንገድ ደግሞ ፎቶ ግራፎቹን በቴምብር፣ በፖስተር፣ በበራሪ ወረቀቶች እና በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ በመለጠፍ አድናቆታችንን መግለጽና ማስተዋወቅ እንችላለን።





ስዕል 55 የኮንሶ ዋካዎች፣ እና ጥንታዊ የሙዚቃ መሳሪያ

የተግባር ስራ

- በአካባቢያችሁ ካሉ የቴያትር ክበባት እና ባለሙያዎችን በመጠየቅ የሀገር በቀል እውቀቶቻችንን እንዴት የቴያትር ርዕሰ ጉዳይ አድርገን ድርሰት ልናዘጋጅ እንደምንችል ማስታወሻ ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
- በመቀጠልም በቡድን በመሆን ከሀገር በቀል እውቀቶቻችን መካከል ባህላዊ የፍርድ ስርዓት፣ እና ባህላዊ እርቅ ስነ ሥርዓትን የሚያሳይ ቴያትር አዘጋጅታችሁ ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።
- የሰራችሁን የቴያትር ስራ መሰረት በማድረግ የቴያትሩ ርዕሰ ጉዳይ ሆነው የተነሱት የሀገር በቀል እውቀቶቻችንን በመጠበቅ እና ለትውልድ ማቆየት ያለውን ጠቀሜታ የቡድን ውይይት አካሂዱ።
- በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ ያሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባለሙያዎችን በማናገር ሀገር በቀል እውቀቶቻችንን የሚያስተዋውቁ ፎቶ ግራፎች ካሏቸው በውሰት እንዲሰጧችሁ በመጠየቅ ስለ ፎቶ ግራፎቹ መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራርታችሁ ተናገሩ።

4.3 ሀገር በቀል እውቀቶችን በሙዚቃ ማድነቅ

ኢትዮጵያ ሀገራችን የበርካታ ሀገር በቀል እውቀቶች ባለቤት ነች። ሆኖም ግን በሀገራችን የሚገኙትን እውቀቶችና ፈጠራዎች የተሰጣቸው ቦታና ክብር አነስተኛ ነው። በዚህ የክፍል ደረጃ ሀገር በቀል እውቀቶችና የእውቀቱ ባለቤቶችን እናደንቃለን።

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ሀገር በቀል እውቀት ማለት ምን ማለት ነው? በአካባቢያችሁ ምን ምን ሀገር በቀል እውቀቶች አሉ? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. ማድነቅ ማለት ምን ማለት ነው? ምን ምን ጉዳዮችን አድንቃችሁ ታውቃላችሁ?
3. በሙዚቃ ሲደነቁ ሰምታችሁ የምታውቋቸውን ነገሮች በደብተራችሁ ፃፉና እየዘፈናችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ሀገር በቀል እውቀቶች የምንላቸው በግል ወይም በጋራ የተፈጠሩ በብዙ ዘመናት ልምድ የዳበሩና በባህል ውስጥ ሰርፀው የገቡ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ በታሪክ በሙዚቃ፣ በአባባል፣ በእምነትና በሌሎች መንገዶች የሚተላለፉ የማህበረሰቡ የጋራ ሀብት ናቸው።

ሀገር በቀል እውቀቶች የምንላቸው፣ የዕደ ጥበብ ስራ፣ የምግብ አዘገጃጀት፣ የሽመና ስራ፣ የህንፃ ጥበብ ስራ፣ የባህል መድሀኒት ቅመማ፣ የግብርና ስራ እውቀትና ሌሎችም ይገኙበታል። እነዚህና ሌሎች እውቀቶች ከሰዎች የዕለት ተዕለት ህይወት ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው። ሀገር በቀል እውቀቶች የሰዎችን የአኗኗር ዘዴ ቀለል የሚያደርጉ ከጥንት ጀምሮ በቅብብሎሽ ሲተላለፉ የመጡ ናቸው። በእስክስታና በሙዚቃ መሳሪያዎች ሀገር በቀል እውቀቶችን ማድነቅ ይቻላል። በዚህ ርዕስ ሙዚቃ እየዘፈናችሁ ግጥም እየገጠማችሁ፣ እስክስ እያላችሁ በአካባቢያችሁና በክልላችሁ የሚገኙ የተለያዩ ሀገር በቀል እውቀቶችን ማድነቅን ትማራላችሁ።

4.3.1 የሽመና ጥበብን በሙዚቃ ማድነቅ



ስዕል 56 ጥንታዊ የሽመና አሰራር

ማድነቅ ለሰው ልጅ የተሰጠ ታላቅ ስጦታ ነው። ማድነቅ ሲባል የተዋበን ነገር ብቻ ሳይሆን እንዲዋብ ያደረገውን ነገር ማስታወስና ማድነቅ ያስፈልጋል። የሚደነቀው የተዋበው አካል ብቻ ሳይሆን እንዲዋብ ያደረገውንም ነው። ለምሳሌ፦ አንዲት ሴት ፀጉሯን ሹርባ ተሰርታ፣ የሚያምር ቀሚስ ለብሳ፣ ያንገት ጌጥ፣ አድርጋ አምሮባት ብትታይ ያማረባት እሷ ብትሆንም እንዲያ እንድታምር ያደረጓትን ጌጣጌጦች የሰራውን ሰው ማድነቅና ሙያውን ለመማር መጓጓት ይገባል። ተማሪዎች የሽመና ስራ ምንድን ነው? በሽመና የተሰሩ አልባሳትን

አይታችሁ ታውቃላችሁ? የሽመና ስራ በአገራችን ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ የልብስ ስራ ጥበብ ነው። እናቶች ቀሚስ፣ ነጠላ፣ መቀነት፣ አባቶች ደግሞ ኩታ፣ ሻሽ፣ ብልኮና ጃኖ የመሳሰሉ አልባሳትን የሚለበሱት በሽመና አሰርተው ነበር። ይህን ጥንታዊና የኢትዮጵያዊያን ማንጫ እውቀት ማድነቅና መማር ያስፈልጋል። በሽመና የተሰሩ ባህላዊ አልባሳት ደግሞ የሰውን ልጅ ቀልብ የሚስቡ ሰው አምሮና ተውቦ እንዲታይ የሚያደርጉ የሀገር በቀል እውቀት ውጤቶች ናቸው።

4.3.2 መዝሙር አለ ባለሙያዎች

አለ ባለሙያዎች በቀበሌ በወረዳ፣

ምርታቸው የሚውል ከአደባባይ እስከጓዳ፣

ውለታቸው ብዙ ስራቸው ጠንካራ፣

ሙያቸው ይታወቅ በየትኛውም ስፍራ፣

አዝማች

ጠረጴዛውም ያምራል ወንበሩም ይመቻል፣

ከአናጺ ውጪ ማን ይህን ይሠራል፣

ጋቢው ነጠላው እንዴት ያስገመጃል፣

ከሸማኔ ውጪ ማን ይህን ይሠራል፣

አዝማች

የወርቁ ጆሮ ጌጥ የመዳቡ ሀብል፣

ከአንጥረኛው በቀር ማን እንዲህ ይሠራል፣

ይህ ሁሉ ጥበብ እንዲህ የተሠራው፣

ከልብ በመነጨ ከስራ ፍቅር ነው፣

አዝማች

ግንበኛውም ይታወቅ በሚሠራው ስራ፣

ሸማኔውም ይታወቅ በሚሠራው ስራ፣

ሁሉም ባለሙያ በስራው እኩል ነው፣

ከነዚህ ሰዎች ውጭ ማነው የሚኖረው።



መልመጃ 4.1

ሀ) ተማሪዎች በሸመና የተሰሩ አልባሳትን በሙዚቃ ለማድነቅ የሚከተሉትን ተግባራት ስሩ።

1. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ የሸመና መስሪያ ቦታ ሂዱና በሸመና ጥበብ ምን ምን አልባሳትን መስራት እንደሚቻል ጠይቃችሁ የተመለከታችሁትን ነገር በግጥም፣ በሙዚቃና በእስክስታ አድናቆታችሁን ግለፁ።
2. በአካባቢያችሁ የሸመና ስራ የሌለ ከሆነ ደግሞ ቤተሰብ ወይም ጎረቤት የሚለብሷቸውን የሸመና ስራ ውጤቶች ጠይቃችሁ እዩና አድናቆታችሁን በግጥም፣ በሙዚቃና በእስክስታ ግለፁ።

4.3.3 ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ማድነቅ

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የምንላቸው ሰዎች በተለያዩ ማህበራዊ ክንዋኔዎች ደስታቸውንና ሀዘናቸውን ለመግለፅ የሚጠቀሙባቸው በአካባቢያቸው በሚገኙ ቁሳቁሶች የሚሰሩ የሙዚቃ መሳሪዎች ናቸው። እነዚህን ጥንታዊና የኢትዮጵያዊያን መገለጫ የሆኑ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አሰራራቸውን፣ አጨዋወታቸውንና ጥቅማቸውን ማወቅ መማርና ማድነቅ ያስፈልጋል።

መልመጃ 4.2

1. በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የምታደንቁትን ምረጡና አድናቆታችሁን በመዝሙር ግለጹ

የምዕራፉ ማጠቃለያ

☑ የሀገር በቀል እውቀቶችን በሙዚቃ፣ በግጥም፣ በእስክስታ፣ እና በመሳሰሉት የክውን ጥበባት ማድነቅ ለሀገራችን እድገት በጣም ጠቃሚ ነው። ከበርካታ ሀገር በቀል እውቀቶች ውስጥ የአስተራረስ ዘዴ እንደየ አካባቢው ባህልና ወግ እየተዘፈነ በግጥም እየተሞካሸ የሚከወን እውቀት ነው። የሸመና

ስራንም በተለያዩ ዘፈኖች እስክስታዎች አምረውና ተውበው ሲያደንቁት ይታያል። ስለዚህ እውቀትና ሙዚቃ አብረው የኖሩ ሀገር በቀል እውቀቶች ናቸው። ከሀገር በቀል እውቀቶች ባህላዊ መድሃኒት ቅመማና ሌሎች የሚገኙበት ሲሆን እነዚህ ሀገር በቀል እውቀቶችም ለሌሎች ዘመናዊ ለሆኑ የህክምና ዘዴዎች መነሻ ሆነው የሚያገለግሉ ስለሆኑ ጥበብን በመጠቀም ማድነቅ ለሙያው እድገትና ተቀባይነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል። እንደማሳያነት በአለም ላይ የሚገኙ በርካታ ሀገሮች ያደጉት ለሀገር በቀል አውቀቶች ትኩረት በመስጠታቸውና በስነ-ጥበብ ስራዎች አማካኝነት ማድነቅ በመቻላቸው መሆኑን መመልከት ይቻላል። ከላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች በተጨማሪ አንድን ሀገር በቀል እውቀት አደነቅን ሲባል የምናደንቀው የስራ ውጤቶችን ብቻ ሳይሆን ያንን ተግባር በባለቤትነት የሚሰሩትን ግለሰቦች ወይም ማህበራትን ጭምር መሆን አለበት።

☑ ሀገር በቀል እውቀቶቻችን ስንል በየዘመናቱ አባቶቻችን የፈጠሯቸውን የፈጠራ ስራዎች የሚያካትት ነው፡ ከእነዚህ የፈጠራ ስራዎች መካከል ቁሳዊ የሆኑት የስነ ጥበብ ስራዎች የኪነ ህንጻ፣ የስዕል፣ የቅርጽ፣ የጌጣጌጥ፣ የአልባሳት፣ እና የእለት ከእለት መገልገያ ቁሳቁሶች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። የህዝብ አስተዳደር፣ የህክምና፣ የስነ ምግብ፣ የግብርና፣ የጊዜ አቆጣጠር፣ የስነ ፈለክ ጥናት እና የሥነ ጽሁፍ ስራዎች ቁሳዊ ከሆኑት በተለየ የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህን ሀገር በቀል እውቀቶች ለማስተዋወቅ ለትውልድ ለማቆየት እና አድናቆትን ለመግለጽ የእይታዊ ጥበባት ስራዎች እና የክውን ጥበባት ስራዎች ትልቅ አስተዋጽኦና ጠቀሜታ አላቸው።

የምዘና ጥያቄ አንድ

ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የቀረቡትን ጥያቄዎች በ✓ምልክት በማድረግ ራሳችሁን መዝኑ።

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	በአካባቢያችን የሚገኙ የሸመና ጥበብ ስራዎችን በሙዚቃ አድንቂያለሁ።		
2	ሙዚቃው በፈጠረው ስሜት የሸመና ስራ ጥበብን ለመስራት የሚያስችል መነሳሳት ተፈጥሮብኛል።		

3	አለን ባለሙያዎች የሚለውን መዝሙር ግጥምና ዜማ በቃሌ ይገ መዘመር ችያለሁ።		
4	የሽመና ጥበብን የሚያደንቁ ዜማና ግጥሞችን ደርሽ ማድነቅ ችያለሁ።		
5	በአካባቢየ በርካታ ሀገር በቀል እውቀቶች በክውን ጥበባት እንደሚደነቁ ተገንዝቢያለሁ።		
6	የሀገር በቀል እውቀቶችን በአካባቢየ በሚገኙ ዜማዎች ማድነቅ ችያለሁ።		
7	በእስክስታ አገር በቀል አውቀቶችን ማድነቅ የሚያስችሉ የተግባር ስራዎችን ሰርቸ ማሳየት ችያለ።		
8	በክልላችን የሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን አሰራርና አጠቃቀም በተግባር ሰርቼ ማሳየት ችያለሁ።		

የምዘና ጥያቄ ሁለት

ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የቀረቡትን ጥያቄዎች በ✓ምልክት በማድረግ ራሳችሁን መዝኑ።

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	ሀገር በቀል እውቀቶችን በእይታዊ ጥበባት ማድነቅ እንደሚቻል ተገንዝቤታለሁ		
2	ንድፍ በመስራት ሀገር በቀል ጥበባዊ ስራዎችን ማድነቅ ችያለሁ		
3	የወረቀት ሞዛይክ በመስራት ሀገር በቀል ጥበባዊ ስራዎችን መስራት ችያለሁ		
4	ሀገር በቀል እውቀቶችን በቴያትር በፊልም እና በፎቶ ግራፍ ማድነቅ እንደሚቻል ተገንዝቤያለሁ		

የማጠቃለያ መልመጃዎች

ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ በማንበብ ትክክል የሆኑትን እውነት ትክክል ያልሆኑትን ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ሀገር በቀል እውቀቶችን በሙዚቃ ስናደንቅ ጥበቡን ብቻ ሳይሆን ጥበበኛውንም ማድነቅ ያስፈልጋል።
2. በመዝሙር ወይም በሙዚቃ ሀገር በቀል እውቀቶችን ስናደንቅ የሰውነት እንቅስቃሴና የፊት ገፅታችንም ስሜቱን አብሮ መግለፅ አለበት።
3. የክራር፣ የመሰንቆ፣ የበገና አጨዋወት ሙዚቃን ለማጀብና ለማድመቅ የሚጠቅሙ እንጂ እራሳቸው ሀገር በቀል እውቀቶች አይደሉም።
4. ያለ ግጥም አገር በቀል እውቀቶችን በዜማ ማድነቅ እንችላለን።
5. እስክስታ አንዱ የሀገር በቀል አውቀቶች ማድነቂያ መንገድ ነው።
6. የተለያዩ ክብረ በዓላት ላይ የሙዚቃ ጨዋታውን መከታተል ሙዚቃን ማድነቅ ነው።
7. እይታዊ ጥበባት ሀገር በቀል እወቀቶችን ለማድነቅ ትልቅ ሚና አላቸው
8. የንድፍ ስራ በመስራት ሀገር በቀል እወቀቶችን ማድነቅ ይቻላል
9. የወረቀት ሞዛይክ ስራ የሀገር በቀል እውቀቶችን ለማድነቅ አያስችልም
10. ቴያትር፣ ፊልምና ፎቶ ግራፍ ሀገር በቀል እውቀቶችን ለማድነቅ ያላቸው ሚና ዝቅተኛ ነው

ለ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ሰርታችሁ አሳዩ።

11. በግላችሁ አንድ የምታደንቁትን የሙያ ዘርፍ ምረጡና ዜማና ግጥም ፈጥራችሁ አድናቆታችሁን ግለፁ።
12. ተማሪዎች በግል ከደረሳችኋቸው ዜማና ግጥሞች መካከል የተሻለውን ስራ በመምረጥ በቡድን አጥንታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ምዕራፍ 5

ሥነ ጥበባት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያላቸው ዝምድና

የምዕራፉ ዓላማዎች፡

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- እይታዊ ጥበባት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ትገነዘባላችሁ፤
- የእይታዊ ጥበባት ስራዎች ቅርሶታችንን ለመጠበቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ትረዳላችሁ፤
- የእይታዊ ጥበባት ስራዎችን ለጠቃሚ ጉደዮች ማስተማሪያነት መጠቀም ትችላላችሁ፤
- ቴያትር ፊልምና ፎቶ ግራፍ ቅርሶታችንን ለመጠበቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ትረዳላችሁ፤
- ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለውን ትስስር ትገነዘባላችሁ፣
- በመዝሙር አማካኝነት ስለ ቅርስ፣ ስለ ጤና፣ ስለ ደን አስፈላጊነት ታውቃላችሁ፣
- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዜማና ግጥም ትደርሳላችሁ፣

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

- ተማሪዎች ሰዎች ከንግግር በተለየ በምን በምን ሊግባቡ ይችላሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?
- “ከሺ ቃላት አንድ ስዕል ይበልጣል” የሚለው አባባል ምን የሚያመለክት ይመስላችኋል?
- አንድ ነጋዴ ምርቶቹን ለተጠቃሚዎች በምን መልኩ ሊያስተዋውቅ ይችላል?
- ተማሪዎች ዲዛይን ለምን ለምን ይጠቅማል ብላችሁ ታስባላችሁ? ዲዛይን የሚያስፈልጋቸው ስራዎች የትኞቹ ናቸው?
- በአካባቢያችን የሚሰሩ የአደባበይ ሀውልቶች እና ስነ ጥበባዊ ስራዎች ያላቸው ጠቀሜታ ምን ይመስላችኋል?

5.1 የእይታዊ ጥበባት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ዝምድና

የእይታዊ ጥበባት በዋናነት የሰው ልጅ ስሜቱን ሀሳቡን እና መልዕክቱን የሚገልጽባቸው የፈጠራ ስራዎች ናቸው። እነዚህ ስራዎች ከሰው ልጅ ጋር ከፍተኛ የሆነ ግንኙነት አላቸው። ሰዎች ከንግግር በተለየ እይታዊ በሆነ መንገድ ይግባባሉ። ለምሳሌ ጥንታዊ ከሚባሉት የመግባቢያ መንገዶች መካከለ ስዕል የመጀመሪያው መግባቢያ ዘዴ ነው። ከሺ ቃለት አንድ ስዕል ይበልጣል የሚባለው አባባል ስዕል በተግባቦታችን ውስጥ እምቅ የሆነ መልዕክትን ለማስተላለፍ የተሻለ አማራጭ እንደሆነ የሚጠቁም ነው።





ስዕል 57 የሻይ ቅጠል ማሸጊያ ማስታወቂያ እና የጥንት ግብጻውያን ስዕላዊ ኪነ ጽሁፍ (ሂሮግራፊ)

የእይታዊ ጥበባት ስራዎች ለማስተማር፣ ለማስተዋወቅ፣ ሰዎችን ለመቀስቀስና ስሜታችንን ለመግለጽ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። የአንድ ሻይ ቅጠል ማሸጊያ ስዕል ዓላማ ሻይ ቅጠሉን ከማሸግ በተጨማሪ የማስታወቂያ ስራም ያከናውናል።



ስዕል 58 የሀገራችን ታላላቅ ተቋማት መለያ አርማዎች ዲዛይን

ከላይ የምንመለከታቸው የሀገራችን ታላላቅ ተቋማት መለያ አርማዎች ናቸው። የእነዚህ አርማዎች ዋነኛ ዓላማ የተቋማቱን ማንነት የሚወክሉ እና መገለጫ የሚሆኑ የግራፊክስ ጥበባዊ ስራዎች ናቸው። ይህም የእይታዊ ጥበባት ስራዎች በእይታ ላይ የተመሰረተ መግባባት እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ያመላክታል።



ስዕል 59 የኪነ ህንጻ ዲዛይን



ስዕል 60 የእንጨት ስራ ዲዛይን

በሌላ መልኩ ደግሞ የእይታዊ ጥበባት ስራዎች በእለት ከእለት አኗኗራችን ውስጥ የምንገለገልባቸውን ቁሳቁሶች ለማዘጋጀት የሚያስችሉን ሲሆን የአልባሳት ዲዛይን፣ የኪነ ህንጻ ዲዛይን፣ የእንጨትና ብረታብረት ስራ ዲዛይነ፣ የጌጣጌጥ ዲዛይን፣ እና ሌሎች በርካታ ቁሳቁሶች በዋናነት የዲዛይን ባለሙያ የሚያስፈልጋቸው ናቸው። የዲዛይን ባለሙያው የተሻለ የስነ ውበት ግንዛቤና የፈጠራ ልምድ ከሌለው ጥሩ ምርት ለማግኘት እንቸገራለን። ዲዛይን ከሳይንስ ጋር ከፍተኛ የሆነ ግንኙነት አለው። ሳይንሳዊ እውቀቶቻችንን ተጠቅመን ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን ለማዘጋጀት የዲዛይን እወቀትና ክህሎት ያስፈልገናል።

እይታዊ ጥበባት አካባቢን ከማስተዋል እና ነገሮችን በጥልቀት ከመመልከት የሚጀምሩ ፈጠራዊ ተግባራት ናቸው። ይህ ደግሞ አካባቢያችንን ደጋግመን እንድንመለከት እና እንድንገነዘብ ያስችለናል።



ስዕል 61 የካቲት 12 መታሰቢያ የአደባባይ ሀውልት

የተግባር ስራ

- በአካባቢያችሁ ያሉ ታሪካዊ የስነ ጥበብ ስራዎችን በምሳሌነት ወስዳችሁ ከሀገራችን ታሪክ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
- በቅርበት የምታገኟቸውን የሳሙና፣ የሻይ ቅጠል እና የብስኩት ማሸጊያዎች ወደ ክፍል በማምጣት በእይታዊ መግባባት ሂደት ውስጥ ያላቸውን ሚና ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
- ዲዛይን በአካባቢያችሁ ካሉ የኪነ ህንጻ ስራዎች፣ ድልድዮች እና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ጋር ያለው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ምሳሌ በመስጠት አብራርታችሁ ተናገሩ።

ይህ ከላይ የምንመለከተው የየካቲት 12 አደባባይ ሀውልት የሀገራችንን ታሪክ እና ማንነት ለትውልድ የሚዘክር የታሪክ ማስታወሻ እና አሻራ ሲሆን በዋናነት በ1928 ዓ/ም የጣልያን ወረራ ወቅት የነበረውን የጀግንነት ኢትዮጵያውያን አስከፊ ጉዳት የሚያስታውስ ነው። በየዘመኑ የሚሰሩ እይታዊ ጥበባት ሥራዎች የስልጣኔያችን እና የታሪካችን ምስክሮች ናቸው።

5.1.1 እይታዊ ጥበባት እና ቅርሶቻችን

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

- በአማራ ክልል የሚገኙ ዋና ዋና ሰው ሰራሽ ቅርሶች የምንላቸውን ለጓደኞቻችሁ መዘርዘር ትችላላችሁ?
- ከዘረዘራችኋቸው ሰው ሰራሽ ቅርሶች መካከል የእይታዊ ጥበባት ዘርፎች የሚባሉትን እነማን ናቸው?
- የእይታዊ ጥበባት ስራዎቻችን የሀገራችን ቅርሶች ናቸው ብላችሁ ታምናላችሁ?

የእይታዊ ጥበባት ስራዎች የሀገራችን ቅርሶች ናቸው። የላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የጎንደር ቤተ መንግስት፣ የጉንዲ ሚካኤል አይጠየፍ አዳራሽ፣ የጎዜ መስጊድ፣ አንኮበር የምኒልክ ቤተ መንግስት፣ ባህላዊ አልባሳት ጌጣጌጦች፣ የሸክላ ስራዎች እና ሌሎች ሰው ሰራሽ የሆኑ መገልገያ ቁሳቁሶቻችን የሀገራችን ቅርሶች ናቸው። እይታዊ ጥበባት ባህላችንን እና ታሪካችንን ለመጠበቅ እና ለማቆየት ትልቅ ስተዋጽኦ አላቸው። ባህላዊ አልባሳቶቻችን፣ የመገልገያ ቁሳቁሶቻችንን በማህበረሰባችን የሚሰሩ እና የእኛን እምነት፣ ቋንቋ እና የአኗኗር ዘይቤ የሚወክሉ ናቸው።



ስዕል 62 ባህላዊ መገልገያ ቁሳቁሶች

ባህላዊ የመገልገያ ቁሳቁሶቻችን የሀገራችን የእደ ጥበብ ውጤቶች ሲሆኑ እለት ከእለት ኑሯችን በእጅጉ የሚያስፈልጉ እና የኛ ማንነት መገለጫዎች ናቸው። የእይታዊ ጥበባት ስራዎች ቅርሶቻችንን እና ባህላችንን እንድናደንቅ እንድንጠብቅ እና ለትውልድ እንድናስተላልፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። ባህላዊና ታሪካዊ እሴቶቻችንን ለማስተዋወቅ ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው።

ተማሪዎች ቅርሶቻችንን ባህላዊ እሴቶቻንን በእይታዊ ጥበባት እንዴት መጠበቅና ማቆየት እንችላለን? በፖስተር፣ በቴምብር እና በሌሎች የማስታወቂያ ስዕሎች ስለ ቅርሶቻችን ማስተማር እንችላለን። በንድፍ፣ በቅርጽ፣ በቀለም ቅብ፣ በጌጣጌጥ፣ እና በተለያዩ የእይታዊ ጥበበ ዘዴዎች ቅርሶቻችንን መስራት መጠገን እና ለትውልድ ማስተላለፍ እንችላለን።

5.1.2 እይታዊ ጥበባት እና አንዳንድ ማህበራዊ ርዕሰ ጉዳዮች

በሀገራችን ለትራፊክ አደጋ፣ ለጤና፣ ለስርዓተ ጾታ እና ሌሎች በርካታ ማህበራዊ ርዕሰ ጉዳዮች ያለን ግንዛቤ እና እውቀት ከፍ እንዲል እይታዊ ጥበባት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። ይህም ስለ ማህበራዊ ርዕሰ ጉዳዮቹ ለማስተማር ለማስተዋወቅ እና የግንዛቤ ስራ ለመስራት ያስችሉናል።

ስለትራፊክ አደጋ፣ ስለስርዓተ ጾታ እና ስለ ማህበረሰብ ጤና ጉዳዮች እይታዊ ጥበባት በማስተማር እና መልእክቶችን በማስተላለፍ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ለምሳሌ የመንገድ ዳር የትራፊክ ምልክቶች፣ ማሰታወቂያ ፖስተሮች እና ይህን ርዕሰ ጉዳይ የሚያስረዱ የቀለም ቅብ፣ የህትመት እና የቅርጽ ስራዎች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።



ስዕል 63 እጅን ስለመታጠብ



ስዕል 64 ከተላላፊ በሽታዎች ራስን ስለመጠበቅ

የተግባር ስራ

- የትራፊክ አደጋን አስከፊነት የሚያስምር የስዕል ስራ በማዘጋጀት ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።
- የጸታን እኩልነት የሚያስረዳ ፖሰተር ስርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።
- ስለ ማህበረሰብ ጤና፣ የግል እና የአካባቢ ንጽህና የሚያስተምር የስዕል ስራ በመስራት ለክፍል ጋደኞቻችሁ አሳዩ።
- ከላይ በሶስቱም ተግባራት የሰራችኋቸውን ስራዎች በማደራጀት ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በኢግዚቢሽን መልክ አሰናድታችሁ አሳዩ።



ስዕል 65 የጸታ እኩልነትን የሚያሳይ ስዕል

5.2 ቴያትር ፊልም፣ ፎቶ ግራፍ እና ማህበራዊ ርዕሰ ጉዳዮች

ቴያትር ፊልምና ፎቶ ግራፍ በዋናነት ሰውን ማዕከል በማድረግ ልዩ ልዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ናቸው። ማህበረሰቡን በቀላሉ እያዝናናን ስለትራፊክ አደጋ፣ ስለስርዓተ ጾታ እና ስለ ማህበረሰብ ጤና ጉዳዮች ከምናስተምርባቸው የስነ ጥበባት ዘዴዎች መካከል ቴያትር ፊልም እና ፎቶ ግራፍ በዋናነት የሚጠቀሱ መንገዶች ናቸው።



ስዕል 66 የቃቄ ውርድወት ከ150 ዓመት በፊት በጉራጌ አካባቢ ስለሴት መብት እና እኩልነት ጥያቄ የምታነሳን “ቃቄ ውርድወት” ታሪክ የሚዳስስ ቴያትር ነው

የተግባር ስራ

- ተማሪዎች፣ በቡድን በመሆን ስለ ትራፊክ አደጋ፣ ስለ ጾታ እኩልነት እንዲሁም ስለ ግልና የአካባቢ ንጽህና የሚያስተምር ቴያትር በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አሳዩ።
- ተማሪዎች፣ በቡድን በመሆን ስለ ትራፊክ አደጋ፣ ስለ ጾታ እኩልነት እንዲሁም ስለ ግልና የአካባቢ ንጽህና የሚያስተምር አጭር ፊልም የሞባይል ካሜራችሁን በመጠቀም አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አሳዩ
- ተማሪዎች በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ ካሉ የጤና፣ የመንገድ ትራንስፖርት እና የሴቶች ጉዳይ ቢሮ በመሄድ ስለ ትራፊክ አደጋ፣ ስለ ጾታ እኩልነት እንዲሁም ስለ ግልና የአካባቢ ንጽህና የሚያስተምሩ ፎቶ ግራፎችን እና ፖስተሮችን ካሏቸው በውሰት በመውሰድ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ በስራዎቹ ዙሪያ አጭር ማብራሪያ አቅርቡ

5.3 ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ትስስር

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች እስኪ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ክፍል ከተማራችኋቸው መዝሙሮች በቡድን በቡድን እየሆናችሁ ሁለት መዝሙሮችን ዘምራችሁ አሰሙ። በምትዘምሩበት ጊዜም ለስለስ ባለ አዛዚያም (ፒያኖ ሲሞ) በመጠቀም ዘምሩ።
2. ከዘመራችሁት መዝሙር ምን ቁም ነገር አገኛችሁበት? እስኪ የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው።

ሳይንስ	ሒሳብ	ህ/ሰብ	ቋንቋ
			
የስሜቱ እዋሳት	10 አረንጓዴ ጠርሙሶች	የዜግነት ክብር	ሀ ሁ ሂ ሃ ሄ ሆ እዘምራለሁ

ሙዚቃ ከቋንቋ፣ ከሂሳብ፣ ከማህበራዊ ሳይንስና ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ከፍተኛ ትስስርና ቁርኝት አለው። ሙዚቃ ከሳይንስ ጋር ቁርኝት አለው ሲባል ከስርዓተ ትንፈሳ ጋር ያለውን መመልከት እንችላለን። የአተነፋፈስ ስርዓቱ ያልተስተካከለ ሰው ጥሩ ዘፋኝ ሊሆን አይችልም። ሌላው የሙዚቃ ትምህርት ከህብረተሰብ ጋር ይገናኛል ስንል ደግሞ የተለያዩ ባህሎችን፣ አለባበሶችንና በጋራ መዝፈንን፣ እስክስ ማለትን፣ በሙዚቃ አማካኝነት ለማህበረሰቡ የተለያዩ ጠቃሚ ልምዶችን ያስተምራል። ሙዚቃ ማዳመጥ ጥሩ ስሜት እንዲሰማን ያደርጋል፣ ያለፈውን ጊዜ ያስታውስልናል፣ ከሰዎች ጋር ጠንካራ ትስስር ይፈጥርልናል፣ አስፈላጊ ባሕርያትን እንድናዳብር ይረዳናል።

ሙዚቃ ማዳመጥ ምግብ ከመብላት ጋር ሊመሳሰል ይችላል። የምንመገበውን ምግብ እንደምንመርጥ ሁሉ የምናዳጠውንም ሙዚቃ መምረጥ አስፈላጊ ነው። ጥቂት ጊዜ የሰማነው ሙዚቃ ለረጅም ጊዜያት ከአእምሯችን ላይወጣ ይችላል። በባህላችን እንደምናውቀው በልጅነታቸው በተለያዩ ክብረ በዓላት አብረው ዘፍነውና ተጫውተው ያደጉ ሰዎች ፍቅራቸውና ትዝታቸው ከፍተኛ ነው። ይህ የሚያሳየው ሙዚቃ በልጆች አዕምሮ ላይ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ነው። ስለዚህ የተለያዩ ትምህርቶችን በሙዚቃ አማካኝነት በቀላሉ መማር እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል። ህፃናት ሙዚቃ በሚያዳምጡበት ጊዜ ከእድሜያቸው ጋር የተገናኙ በመልካም ስብዕና እንዲቀረፁ የሚያስችሉ የህይወት መንገዳቸውን የሚያሳዩ ሊሆኑ ይገባል።



ስዕል 67 ሙዚቃ እንደ መፅሐፍ

ህፃናት ከእድሜያቸው ጋር ሊመጣጠኑ የማይችሉ ሙዚቃዎችን ከማድመጥ መቆጠብ አለባቸው። ህፃናት የሚሰሟቸው የተለያዩ የዘፈን ዓይነቶች ለነገሮች ያሏቸውን አመለካከት የመቀየር ሃይል አላቸው። በሙዚቃ፣ በግጥምና በእንቅስቃሴ የተቀናጁ ትምህርቶችን መማር ለጥሩ የትምህርት አቀባበልና ለማስታወስ ችሎታ ማደግ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።

የቅድመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች በመዝሙር አማካኝነት የተለያዩ ጉዳዮችን ተምራችሁ ታውቃላችሁ?
2. በአምስተኛ ክፍል ከዘመራችኋቸው መዝሙሮች አንድ መዝሙር ዘምራችሁ አሰሙ።

5.3.1 መዝሙር እውቀት ያብብ

እውቀት የሰዎችን ኑሮ ቀለል የሚያደርግ የሰዎች የምርምር ወይም የፈጠራ ውጤት ሲሆን ይችላል። እውቀትን ከምንማርባቸው መንገዶች አንዱ መዝሙር ነው። ተማሪዎች እውቀት ያብብ በሚለው መዝሙር እውቀት የተባሉት ምን ምን ሙያዎች ናቸው? ከዘመራችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

እውቀት ያብብ

እውቀት ጥበብ በሃገራችን፣
ያብብ ያብብ ያብብ፣
ሰላም እድገት ለህዝባችን፣
ይኑር ይኑር ይኑር፣
መምህር ያስተምር ይማር ተማሪው፣
ቤት ይስራ አናፂው ይረስ ገበሬው፣
ደራሲውም ይድረስ ሙዚቀኛው ያዚም፣
ሰዓሊውም ይሳል ሰው ይፈውስ ሀኪም፣



5.3.2 መዝሙር የታሪክ ቅርሳችን

የታሪክ ቅርሳችን መለያ ሃብታችን
ናቸው ሀብቶቻችን እንጠብቅ ሁላችን
ተፈጥሮ ሰው ሰራሽ የቅርሶች ሙዳይ
ሀገራችን አላት መልኳን የሚያሳይ
አክሱም ላሊበላ ሶፉመር ዋሻችን
ጀጎል የፋሲል ግንብ ሌሎች ቅርሶቻችን

የታሪክ አሻራ ብርቅ ሀብቶቻችን

የቱሪስቶች መስህብ ናቸው መለያችን



5.3.3 መዝሙር፡- ጠንቃቃ ተማሪ

ጥንቃቄን ያውቃል ጠንቃቃ ተማሪ

ሀሳቡን ሰብስቦ መንገድ ተሻጋሪ፣

የትራፊክ መብራት ህጎችንም ያውቃል፣

የሰዎችን ምክር ሁሌም ያዳምጣል፣

የትራፊክ መብራት ሲያበራ ቀዩን፣

መኪና ይቆማል ጠብቆ ሀጉን።

ወንዝ ስንሻገር ግራ ቀኝ አይተን፣

መጠንቀቅ አለብን ድልድይ ላይ ስንሆን፣

ጥንቃቄን ያውቃል ጠንቃቃ ተማሪ፣

ሀሳቡን ሰብስቦ መንገድ ተሻጋሪ፣

የትራፊክ መብራት ህጎችንም ያውቃል፣

የሰዎችን ምክር ሁሌም ያዳምጣል።

ግጥም ሰለሞን ገላው / ዜማ እዝራ አባተ

የምዕራፉ ማጠቃለያ

☑ በዚህ ምዕራፍ በዋናነት ሥነ ጥበብ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ግንኙነት እንዳለው እና ሀገራዊ ቅርሶቻችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ እንደሚረዳ ተገንዝበናል። የእይታዊ ጥበባት ስራዎች የመግባቢያ መንገዶች ሲሆኑ በእለት ከእለት ኑሯችን ውስጥ ሰዎች በእይታ እንዲግባቡ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። በኪነ ህንጻ ዲዛይን፣ በአልባሳትና ጌጣጌጦች ዲዛይን፣ በእንጨትና ብረታ ብረት ስራ ዲዛይን እና በሌሎችም ቴክኖሎጂካል የፈጠራ ስራዎች የዲዛይን እውቀትና ክህሎት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ይህም እይታዊ ጥበባት ከሳይንስ ጋር ያላቸውን መሰረታዊ ግንኙነት የሚያሳይ ነው። እይታዊ ጥበባት ከባህል እና ታሪክ ጋር የተገናኙ ናቸው። እይታዊ ጥበባት አሳሳቢና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ማህበረሰባዊ ርዕሰ ጉዳዮችን በማስተዋወቅ፣ በማስተማር እና በማስገንዘብ ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው።

☑ ሙዚቃ ከበርካታ የትምህርት አይነቶች ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው። ሙዚቃ ከሂሳብ ትምህርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው ሲባል የሙዚቃ ኖታዎችን የምንጫወተው የጊዜ ቆይታውን ለምን ያህል ጊዜ እንደምናዜመው፣ ለምን ያህል ጊዜ ደግሞ ዝም እንደምንል የሒሳብ አቆጣጠርን እንጠቀማለን። የቋንቋ ትምህርቶች ጋር ያለው ግንኙነት ደግሞ በጆሯችን የምንሰማቸው ማንኛውም ንግግር ወይም ፊደላት በድምፅ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ሙዚቃ መልካም ዜጋ ለመቅረጽ ዋነኛ መሳሪያ ነው። ስለ ሀገር ፍቅር፣ ስለ ቤተሰብ ፍቅር፣ የመሳሰሉ ጉዳዮችን በመዝሙር አማካኝነት ይማራሉ። ከዚህ በተጨማሪ በግላችሁ ሌሎች መዝሙሮችን እያፈላለጋችሁ ልትዘምሩና በርካታ ቁም ነገሮችን ልትጨብጡ ትችላላችሁ።

ምዘና አንድ

ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የቀረቡትን ጥያቄዎች በ✓ምልክት በማድረግ ራሳችሁን መዝኑ።

ተ.ቁ	ይዘት	አሳክቻለሁ	አላሳካሁም
1	ሙዚቃ ከተለያዩ የትምህርት አይነቶች ጋር እንደሚገናኝ አውቂያለሁ		
2	እውቀት ያብብ የሚለውን መዝሙር በትክክል ዘምሪያለሁ፣		
3	አሉን ባለሙያዎች የሚለውን መዝሙር ግጥምና ዜማ በቃሌ ይዤ መዘመር ችያለሁ		
4	የታሪክ ቅርሳችንና ጠንቃቃ ተማሪ የሚሉትን መዝሙሮች ዘምሪያለሁ ስለ ምን እንደሚያስተምሩ ተገንዝቢያለሁ		
5	የሙዚቃ ምርጫየ የወደፊት ህይወቴ ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ተገንዝቢያለሁ፣		
6	የተለያዩ ትምህርቶችን በመዝሙር አማካኝነት መማር እንደሚቻል አውቂያለሁ።		

ምዘና ሁለት

ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የቀረቡትን ጥያቄዎች በ✓ምልክት በማድረግ ራሳችሁን መዝኑ።

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	በትክክል	አልገባኝም
1	የእይታዊ ጥበባት ቅርሶቻችንን ለመጠበቅና ለማቆየት እንደሚረዱ ተገንዝቤያለሁ		
2	እይታዊ ጥበባት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ተገንዝቤያለሁ		
3	እይታዊ ጥበባት ስለ ትራፊክ አደጋ፣ ስለ ስርዓተ ጾታ እና ስለማህበረሰብ ንጽህና እና ጤና ለማስተማር ያስችላሉ		
4	ቴያትር፣ ፊልም እና ፎቶ ግራፍ ስለ ትራፊክ አደጋ፣ ስለ ስርዓተ ጾታና ስለማህበረሰብ ንጽህና እና ጤና ለማስተማር ያስችላሉ		
5	አስተማሪ የሆኑ የእይታዊ ጥበባት ስራዎችን መስራት ችያሌሁ		

የማጠቃለያ መልመጃዎች

ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትክክል በማንበብ ትክክል የሆኑትን እውነት ትክክል ያልሆኑትን ሀሰት በማለት መልሱ።

1. እይታዊ ጥበባት ከቋንቋ ጋር ግንኙነት ያላቸው የመግባቢያ መንገዶች ናቸው።
2. ዲዛይን ሳይንሳዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመሰራት የሚጠቅመን አይደለም።
3. ቴያትር፣ ፊልምና ፎቶ ግራፍ ስለ ባህል፣ ታሪክና ቅርሶች ለማስተማር እንጠቀማቸዋለን።
4. ባህልና ቅርሶቻችንን ለትውልድ ለማስተላለፍና ለማቆየት እይታዊ ጥበባት ትልቅ ድርሻ አላቸው

ለ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ በማንበብ አጭር መልስ ስጡ

1. ስለ ትራፊክ አደጋ አስከፊነት፣ ስለ ጸታ እኩልነት እና ስለ ጤናና ንጽህና ለማስተማር እና ለማስተዋወቅ ከምንጠቀምባቸው የእይታዊ ጥበባት አሰራሮች መካከል የሶስቱን ስም ዘርዝሩ።

2. በአካባቢያችሁ ከሚከበሩ ሃይማኖታዊ በዓላት ውስጥ ሁለት ምረጡና በቡድን በቡድን በመሆን አዘፋፈኑን፣ እስክስታውን ወይም ውዝዋዜውን አጥንታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ። ካቀረባችሁ በኋላ

   ሀ) ከሀይማኖታዊ ስርዓቱ ምን ትምህርት እንደተማራችሁ አብራሩ።

   ለ) ያቀረባችሁት እስክስታ የእንቅስቃሴ ሂደት ከምን ጋር ግንኙነት እንዳለው ተናገሩ።

   ሐ) ሙዚቃውን ስታቀርቡ የተጠቀማችኋቸው የሙዚቃ መሳሪያዎችን እፅዋቶች ባይኖሩ ከምን መስራት እንደሚቻል የፈጠራ ሀሳብ ጨምራችሁ መፍትሄውን ተናገሩ።

ዋቢ መጽሐፍት

አየለ ገ/ጊዮርጊስ (2008). መሰረታዊ የሙዚቃ ጽንሰ ሀሳብ (mued 211) ለዲፕሎማ ሰልጣኞች የተዘጋጀ በአብክመ ትምህርት ቢሮ

ዳዊት በለጠ (2008). ሶልፌጆና መዝሙር የማስተማር ስነ-ዘዴ ማሰልጠኛ ሞጁል በአብክመ ትምህርት ቢሮ ፍኖተ ሰላም መምህራን ትምህርት ኮሌጅ

(2004). Arts & communication Drawing and Painting University of Wisconsin

Edwin Wilson (2015). The Theatre Experience McGraw-Hill Education NY

L.Fichner Rathus (2017) Understanding art Boston, MA

J.D. HILLBERRY (1999). Drawing Realistic Textures in Pencil N. Light books

J. Wolfrom (2009). Ultimate 3-in-1 Color Tool C&T Publishing. Inc

M. Michael (2011). Art and design a comprehensive guide for creative artists

W.Blake & J.Lawn (1981). The artist's Painting Library Portrait Drawing W.G NY.